*1ተሰ 4፥16-18 "ጌታ ራሱ በታላቅ ትእዛዝ፣ በመላእክት አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔር የመለከት ድምፅ ከሰማይ ይወርዳልና። በክርስቶስ የሞቱትም አስቀድመው ይነሣሉ። ከዚያም በኋላ እኛ የቀረነው፣ በሕይወትም የምንኖረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ በዚህም መሠረት ለዘላለም ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ በዚህ ቃል እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ።"*

---

መነጠቅ በእንግሊዝኛ "ራፕቸር" ነው። "ራፕቸር" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው "ራፕቱ" ከሚለው የላቲን ቃል ሲሆን፣ ይህ የላቲን ቃል "ሀርፓዞ" ከሚለው የግሪክ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው። በ1ተሰ 4፥17 እንደተጠቀሰው ሲተረጐም "መወሰድ"፣ "መለወጥ"፣ "መነጠቅ" ማለት ነው። እዚህ ላይና በ1ቆሮንቶስ 15 ላይ የተጠቀሰው ይህ አስተምህሮው ቤተ ክርስቲያን ጌታን በአየር ለመቀበል ከምድር ወደ ሰማይ እንደምትነጠቅ ያሳያል። ይህም እውን የሚሆነው ታማኝ ለሆኑት ለክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ብቻ ነው።

(1) ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ ከሰማይ ከሚወርድበት ከንጥቀት በፊት "በክርስቶስ የሞቱት አስቀድመው ይነሣሉ (1ተሰ 4፥16)። ይህ ትንሣኤ በራእ 20፥4 ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ አይደለም። የኋለኛው ትንሣኤ የሚፈጸመው ክርስቶስ ወደ ምድር ተመልሶ ክፉዎችን ካጠፋና ሰይጣንን ካሰረ በኋላ ነው (ራእ 19፥11—20፥3)። በራእ 20፥4 የተጠቀሰው ትንሣኤ ግን በታላቁ መከራ ጊዜ ሰማዕት ከሆኑትና ምናልባትም በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሞቱት ቅዱሳን ትንሣኤ ጋር የተያያዘ ነው (ራእ 20፥6 እና ማብ ይመ)።

(2) በክርስቶስ የሞቱት ቅዱሳን ከሞት ሲነሡ፣ በሕይወት ያሉት አማኞች በዚያው በተመሳሳይ ጊዜ ይለወጣሉ፤ አካሎቻቸው የማይሞት አካል ይለብሳሉ (1ቆሮ 15፥51፡53)፤ ይህ የሚሆነውም እጅግ አጭር በሆነ ጊዜ ነው ማለትም "በቅጽበት ዐይን" ነው (1ቆሮ 15፥52)።

(3) ከሞት የሚነሡት ቅዱሳንና በቅጽበት ዐይን የሚለወጡት አማኞች በአንድነት ክርስቶስን በአየር ላይ ለመቀበል ይነጠቃሉ፤ ይህም በሰማይና በምድር መካከል ያለው ስፍራ ነው።

(4) በግልጽ ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ (1ተሰ 4፥16-17)፤ ወደ አባቱ ቤት ወደ ሰማይ ይወሰዳሉ (ዮሐ 14፥2-3) ቀደም ብለው ከሞቱት ወዳጆቻቸውም ጋር ይገናኛሉ (1ተሰ 4፥13-18)።

(5) ከሥቃይ (2ቆሮ 5፥2፡4፤ ፊል 3፥21) ከስደትና ከጭቈና ሁሉ (ራእ 3፥10 እና ማብ)፣ ከኀጢአት ግዛትና ከሞት (1ቆሮ 15፥51-56) ይገላገላሉ፤ መነጠቅ አማኞችን "ከሚመጣው ቍጣ" (1ተሰ 1፥10 እና ማብ፣ 5፥9) ማለትም ከታላቁ መከራ እንዲያመልጡ ያደርጋቸዋል።

(6) ከዓለም ሊያወጣን አዳኛችን በቶሎ እንደሚመጣልን ያለን ተስፋ "ለዘላለም ከጌታ ጋር" እንድንሆን ያበቃናል (1ተሰ 4፥17)፤ ይህም በክርስቶስ ቤዛነትን ላገኙ ሁሉ የተሰጠ የተባረከ ተስፋ ነው (ቲቶ 2፥13)። ዛሬ በሥቃይ ላይ ላሉ አማኞች ይህ ተስፋ የመጽናኛቸው ዋና ምንጭ ነው (1ተሰ 4፥17-18፤ 5፥10)።

(7)ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ተሰ 4፥17 "እኛ" ሲል የጌታ ዳግም ምጽአት እርሱ ራሱ በሕይወት ባለበት ዘመን እንደሚፈጸም በማሰብ ነው፤ ይህንንም እውነት በተሰሎንቄ ላሉ አማኞች ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ የጌታችንን ዳግም ምጽአት ተግተን በንቃትና በናፍቆት መጠባበቅ እንዳለብን ያስተምረናል። ዛሬም አማኞች ክርስቶስ ወደ ራሱ እንዲወስደን የጌታን ምጽአት በተስፋና በንቃት መጠባበቅ ይኖርብናል (ከሮሜ 13፥11፤ ከ1ቆሮ 7፥29፤ 10፥11፤ 15፥51-52፤ ከፊል 4፥5 ጋር ያነጻጽሩ)።

(8) ከክፉት ከመራቅና ለክርስቶስ ታማኝ ከመሆን ወደ ኋላ የምትል ቤተ ክርስቲያን ዕጣ ፈንታ የመነጠቅ በረከት ተካፋይ አለመሆን ይሆናል (ማቴ 25፥1፤ ሉቃ 12፥45)። ምእመኖቿ የከሐዲዋ የታላቂቱ አመንዝራ ወገን በመሆን ለእግዚአብሔር ቍጣ ይዳረጋሉ (ራእ 17፥1 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1913 ላይ፣ "የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(9) ከመነጠቅ በኋላ የሚመጣው ዘመን የጌታ ቀን የተባለው ነው፤ ይህም እግዚአብሔርን በማይፈሩ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ የሚወርድበት ጊዜ ነው (1ተሰ 5፥2-10፤ 5፥2 እና ማብ ይመ)። በዚህ ጊዜ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ሁለተኛው ደረጃ ይከሠታል፤ ይህም በታላቁ መከራ መጨረሻ ላይ በሚሆነው በአርማጌዶን ጦርነት በምድር ባሉ ክፉዎች ላይ ክርስቶስ የመጨረሻ ቍጣ ክንዱን የሚያሳርፍበትና በምድር ላይ ለሺህ ዓመት የሚገዛበት ዘመን ነው (ማቴ 24፥42፡44 እና ማብ ይመ)።

መካከል በትጋት የሚሠሩትን፣ በጌታም
የበላዮቻችሁና መካሪዎቻችሁ የሆኑትን እን
ድታከብሯቸው እንለምናችኋለን፤ 13ስለ
ሥራቸውም በፍቅር እጅግ አክብሯቸው።
እርስ በርሳችሁም በሰላም ኑሩ። 14ወንድሞች
ሆይ፤ ይህን እንመክራችኋለን፤ ሥራ ፈቶችን
ገሥጿቸው፤ ፈሪዎችን አደፋፍሯቸው፤ ደካ
ሞችን እርዷቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።
15ማንም በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ
ተጠንቀቁ፤ ነገር ግን እርስ በርሳችሁም ሆነ
ለሌሎች ሰዎች ሁልጊዜ መልካም የሆነውን
ነገር ለማድረግ ተጣጣሩ።
16ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤ 17ሳታቋርጡ
ጸልዩ፤ 18በማናቸውም ሁኔታ አመስግኑ፤
የእግዚአብሔር ፈቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ
ለእናንተ ይህ ነውና።
19የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ፤
20ትንቢትን አትናቁ። 21ሁሉን ነገር ፈትኑ፤
መልካም የሆነውን ያዙ፤ 22ከማናቸውም
ዐይነት ክፉ ነገር ራቁ።
23የሰላም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን
ይቀድስ፤ መንፈሳችሁ፣ ነፍሳችሁና ሥጋችሁ
ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ
ያለነቀፋ ይጠበቁ። 24የጠራችሁ የታመነ
ነው፤ እርሱም ያደርገዋል።
25ወንድሞች ሆይ፤ ስለ እኛ ደግሞ[a] ጸልዩ።
26ወንድሞችን ሁሉ በተቀደሰ አሳሳም ሰላም
በሏቸው። 27ይህ መልእክት ለወንድሞች
ሁሉ እንዲነበብ በጌታ ዐደራ እላችኋለሁ።
28የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ
ከእናንተ ጋር ይሁን።

5፥13 ማር9፥50
5፥14 ሮሜ14፥1፤ 1ቆሮ8፥7-12፤ 2ተሰ3፥6፡7፡11
5፥15 ሮሜ12፥17፤ ኤፌ4፥32፤ 1ጴጥ3፥9
5፥16 ፊል4፥4
5፥17 ሉቃ18፥1
5፥18 ኤፌ5፥20
5፥19 ኤፌ4፥30
5፥20 1ቆሮ14፥1-40
5፥21 ሮሜ12፥9፤ 1ቆሮ14፥29፤ 1ዮሐ4፥1
5፥23 ሮሜ15፥33፤ 1ተሰ2፥19፤ 3፥13፤ ዕብ14፥12

[a]5፥25 አንዳንድ ትርጒሞች ደግሞ የሚለው ቃል የላቸው

**5፥17 ሳታቋርጡ ጸልዩ፤** መጸለይ ማለት በአብ ሀልዎት ውስጥ መኖር፣ ጸጋውንና በረከቱን እናገኝ ዘንድ ሳያቋርጡ መጮኽ ነው። «ሳታቋርጡ» ማለት የልማድ ጸሎትን ደጋግሞ መጸለይ አይደለም፤ ነገር ግን በቀን ውስጥ በሁሉም ሁኔታ ሁሉንም ዐይነት ጸሎት በመጠቀም በተከታታይ መጸለይ ነው (ሉቃ 18፥1፤ ሮሜ 12፥12፤ ኤፌ 6፥18፤ ቈላ 4፥2)።

**5፥19 የመንፈስን እሳት አታዳፍኑ፤** ከቍ 19-20 ይመልከቱ። (1) ሐዋርያው ጳውሎስ የመንፈስ እሳትን ማዳፈን ትንቢትን የመሳሰለው የመንፈስ ቅዱስን መለኮታዊ ስጦታ እንደ ማጥፋትና እንደ መናቅ ቈጥሮታል። በትክክለኛውና በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እየዋለ ያለውን የትንቢት ስጦታን ወይም ሌሎችን የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎችን ማዳፈን ወይም መቃወም ማናቸውም ዐይነት የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአማኞች መካከል እንዳይኖር ያደርጋል (1ቆሮ 12፥7-10፡28-30)። የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በዮሐ 14፥26፤ 15፥26-27፤ 16፥13-14፤ በሐሥ 1፥8፤ 13፥2፤ በሮሜ 8፥4፡11፡ 16፡26፤ በ1ቆሮ 2፥9-14፤ 12፥1-11፤ በገላ 5፥22-25 ውስጥ ተጠቅሶአል።

(2) እነዚህ ሁለት ጥቅሶች (ቍ 19-20) በቆሮንቶስ ካለችው ቤተ ክርስቲያን ውጭ ሌሎችም አብያተ ክርስቲያናት የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች በጉባኤ አምልኮ እንደሚጠቀሙ በግልጽ ያመለክታሉ። የትንቢት መልእክቶች ሳይናቁ መደመጥ ቢኖርባቸውም በጥንቃቄ ከተፈተኑ በኋላ መቀበል እንደሚገባ ልብ ይበሉ (ቍ 21፤ 1ቆሮ 14፥29 እና ማብ ይመ)።

**5፥23 ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ምእመናን በመጨረሻ የጸለየው ይቀደሱ ዘንድ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መቀደስ የሚናገረውን በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 2000 ላይ፣ «መቀደስ» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

# የሐዋር
# መልእ
# ሰዎች

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-2
I. ጳውሎስ የተሰሎንቄ
(ሀ) ስለ መንፈሳዊ
(ለ) ስለ ጽናታቸው
(ሐ) በመጨረሻ ስለ
(መ) ለእነርሱ የጸለየ
II. ስለ ዳግም ምጽአት
ለተሰሎንቄ ምእመናን
(ሀ) የጌታ ቀን ገና
(ለ) የዐመፅ ሰው በ
(ሐ) በእውነትና በጸ
III. ሐዋርያው ጳውሎስ
እንዲኖሩ ይመክራቸ
(ሀ) ለእርሱ እንዲጸ
(ለ) በጌታ ጸንተው
(ሐ) የእግዚአብሔርን
እንዲኖሩ (3፥6-
የመጨረሻ ሰላምታና ቡራኬ

**ጸሓፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የክርስ*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይህ መልእክት በተጻፈበት
ጳውሎስ የመጀመሪያውን
ተሰሎንቄን መልእክት መ
በቆሮንቶስ ከሲላስና ከጢሞ
ከጥቂት ወራት በኋላ ሳይሆን
በእርግጥም ሐዋርያው የመጀ
ክርስቲያን አንዳንድ አዳዲስ
ሳይነሣ አልቀረም።

*ዐላማ*

ጳውሎስ ይህን መልእክት የ
ዐላማ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ (
ምእመናን ለማጽናናት፤ (2)

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች - ሁለተኛ

*አስተዋፅኦ*

ክርስቲያናዊ ሰላምታ (1፥1-2)

I. ጳውሎስ የተሰሎንቄ ምእመናንን በደረሰባቸው ስደት እንዳጽናናቸው (1፥3-12)
   (ሀ) ስለ መንፈሳዊ እድገታቸው ያቀረበው ምስጋና (1፥3)
   (ለ) ስለ ጽናታቸው በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የቀረበ ምስጋና (1፥4)
   (ሐ) በመጨረሻ ስለሚቀበሉት ምስጋና የሰጠው ዋስትና (1፥5-10)
   (መ) ለእነርሱ የጸለየው ጸሎት (1፥11-12)

II. ስለ ዳግም ምጽአት የነበራቸውን የተሳሳተ መረዳት በተመለከተ ሐዋርያው ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ምእመናን የሰጣቸው ምክር (2፥1-17)
   (ሀ) የጌታ ቀን ገና እንዳልደረሰ (2፥1-2)
   (ለ) የዐመፅ ሰው በመጀመሪያ እንደሚገለጥ (2፥3-12)
   (ሐ) በእውነትና በጸጋ ጸንቶ መቆም እንደሚያስፈልግ (2፥13-17)

III. ሐዋርያው ጳውሎስ የተሰሎንቄ ምእመናን በተግባር የሚገለጽ ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖሩ ይመክራቸዋል (3፥1-15)
   (ሀ) ለእርሱ እንዲጸልዩ (3፥1-2)
   (ለ) በጌታ ጸንተው እንዲቆሙ (3፥3-5)
   (ሐ) የእግዚአብሔርን ሕግ ከማይታዘዙ ሰዎች እንዲርቁና ሥርዐት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ (3፥6-15)

የመጨረሻ ሰላምታና ቡራኬ (3፥16-18)

**ጸሐፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *የክርስቶስ ዳግም ምጽአት*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በግምት 51 ወይም 52 ዓ.ም.*

**ታሪካዊ ዳራ**

ይህ መልእክት በተጻፈበት ጊዜ በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን የነበረው ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ የመጀመሪያውን መልእክት በጻፈበት ጊዜ የነበረው ዐይነት ነበር (የአንደኛ ተሰሎንቄን መልእክት መግቢያ ይመ)። ስለዚህ ይህ መልእክት የተጻፈበት ጊዜ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ከሲላስና ከጢሞቴዎስ ጋር ሲሠራ በነበረበት ወቅት አንደኛ ተሰሎንቄ ከተጻፈበት ከጥቂት ወራት በኋላ ሳይሆን አይቀርም (1፥1 ይመ፤ ከሐሥ 18፥5 ጋር ያነጻጽሩ)። በእርግጥም ሐዋርያው የመጀመሪያው መልእክቱ እንደ ደረሳቸው እንዲሁም በተሰሎንቄ ቤተ ክርስቲያን አንዳንድ አዳዲስ ነገሮች መኖራቸውን ሲሰማ ሁለተኛውን መልእክት ለመጻፍ ሳይነሣሣ አልቀረም።

**ዐላማ**

ጳውሎስ ይህን መልእክት የጻፈበት ዐላማ የመጀመሪያውን የተሰሎንቄ መልእክት ከጻፈበት ዐላማ ጋር ተመሳሳይ ነው፤ (1) አዲስ አማኞች የሆኑትንና ስደትም እየደረሰባቸው ያሉትን ምእመናን ለማጽናናት፤ (2) ሥርዐት ያለው ሕይወት እንዲመሩና ኑሮን ለማሸነፍ እንዲሠሩ

ለመምከር እና (3) ስለ መጨረሻው ዘመን ሁነቶች በተለይም “የጌታን ቀን” በተመለከተ የነበረውን የተሳሳተ አመለካከት ለማስተካከል (2፥2)።

### ቅኝት

ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ የነበረው ስሜት ለልጆችዋ እንክብካቤ እንደምታደርግ እናት ዐይነት ስሜት ሲሆን (1ተሰ 2፥7)፣ በዚህ መልእክቱ ደግሞ ሁኔታው ሥራ ፈት ልጆቹን እንደሚገሥጽና አካሄዳቸውን እንደሚያርም አባት ሆኖ ነበር (3፥7-12 ይመ፤ ከ1ተሰ 2፥11 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለነበራቸው ጽኑ እምነት እያመሰገናቸው በደረሰባቸው ስደት ሁሉ በታማኝነት እንዲጸኑ ያበረታታቸዋል (1፥3-7)።

የዚህ መልእክት ዋና ክፍል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም ስለሚመጣበት ስለ ሥነ ፍጻሜ ቀን የሚናገር ነው (2፥1-12 ይመ፤ ከ1፥6-10 ጋር ያጻጽሩ)። ከ2፥2 እንደምንረዳው በተሰሎንቄ ያሉት አንዳንዶች ወይ “በትንቢት” (በመገለጥ)፣ ወይ “በወሬ” (በቃል መልእክት)፣ ወይ “በመልእክት” (ምናልባትም ከጳውሎስ) የታላቁ መከራ ጊዜና የጌታ ቀን እንደ ጀመረ ዐውቀዋል። ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን የተሳሳተ አመለካከት ለማረም የጌታ ቀን ከመድረሱ በፊት የሚከተሉት ሦስት ሁነቶች መፈጸም እንዳለባቸው አመልክቶአል፤ (1) ታላቅ ክሕደትና ዐመፅ ይሆናል (2፥3)፤ (2) እግዚአብሔር በክፉ ላይ የወሰነው እገዳ ይነሣል (2፥6-7)፤ (3) “የዐመፅ ሰው” ይገለጣል (2፥3-4፡8-12)። ክርስቶስ በቅርብ መምጣቱ አይቀርም በማለ በየቀኑ ሥራ መሥራትን ትተው የሰነፉትን ክርስቲያኖች ሐዋርያው ጳውሎስ ገሥጾአቸዋል። አማኞች ሁሉ ትጋትና ሥርዐት ያለው ሕይወት እንዲኖሩ መክሮአቸዋል (3፥6-12)።

### ልዩ ገጽታዎች

የሁለተኛ ተሰሎንቄ መልእክትን ልዩ የሚያደርጉት ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፡ (1) በታሪክ ፍጻሜ ስለሚኖረው ያለ ገደብ ስለሚሠራው ዐመፅና ማጭበርበር በአዲስ ኪዳን ከተጠቀሱት የተሻለ ምንባብ ያቀርባል (2፥3-12)፤ (2) ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት ጋር ተያይዞ የሚመጣው የእግዚአብሔር ጻድቅ ፍርድ ልክ በዮሐንስ ራእይ እንዳለው አቡቀለምሲሳዊ በሆነ መንገድ በዚህ መልእክት ቀርቦአል (1፥6-10፤ 2፥8)፤ (3) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሌላ ስፍራ ያልተገለጸውን በትምህርተ ሥነ ፍፃሜ የሚታወቀውን ሐሰተኛውን ክርስቶስን የሚያመለክቱ አባባሎችን ያቀርባል (2፥3፡8)።

### የሁለተኛ ተሰሎንቄ መልእክትን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ሁለተኛ ተሰሎንቄ ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ3 ቀን መነበብ ይኖርበታል፤ □ 1 □ 2 □ 3

ማስታወሻ

1 ጳውሎስ፣ ሲላስና[ሀ] ጢሞቴዎስ፤
በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታም በኢየሱስ ክርስቶስ ለሆኑት፣ ለተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤
2 ከእግዚአብሔር አብ፣ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።

## የምስጋናና የልመና ጸሎት

3 ወንድሞች ሆይ፤ እምነታችሁ በየጊዜው እያደገ በመሄዱና የእርስ በርስ ፍቅራችሁም እየጨመረ በመምጣቱ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በሚገባ ማመስገን አለብን።
4 ስለዚህ በደረሰባችሁ ስደትና መከራ ሁሉ በመጽናታችሁ፣ እኛ ራሳችን ስለ ትዕግሥታችሁና ስለ እምነታችሁ በእግዚአብሔር አብ ያት ክርስቲያናት ዘንድ እንመካለን።
5 ይህ ሁሉ የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን መሆኑን የሚያመለክት ነው፤ ከዚህም የተነሣ መከራን ለምትቀበሉለት ለእግዚአብሔር መንግሥት የበቃችሁ ሆናችሁ ትቈጠራላችሁ።
6 እግዚአብሔር ጻድቅ በመሆኑ መከራን ለሚያመጡባችሁ መከራን ይከፍላቸዋል፤
7 መከራን ለተቀበላችሁት ለእናንተም ሆነ ለእኛ ደግሞ ዕረፍት ይሰጠናል። ይህም የሚሆነው ጌታ ኢየሱስ በሚንበለበል እሳት ከኀያላን መላእክት ጋር ከሰማይ በሚገለጥበት ጊዜ ነው።
8 በዚያ ጊዜ እግዚአብሔርን የማያውቁትንና ለጌታችንም ለኢየሱስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል።
9 እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኀይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ፤
10 የሚቀጡትም በቅዱሳኑ ዘንድ ሊከብርና በሚያምኑበትም ሁሉ ዘንድ ሊገረም በሚመጣበት በዚያን ቀን ይሆናል፤ እናንተም ከሚያምኑት መካ ከል ናችሁ፤ ምስክርነታችንን ተቀብላችኋልና።
11 ይህን እያሰብን አምላካችን ለጥሪው የበቃችሁ አድርጎ እንዲቈጥራችሁ፣ መልካም ለማድረግ ያላችሁን ምኞትና ከእምነት የሆነውን ሥራችሁን ሁሉ በኀይሉ እንዲፈጽምላችሁ ዘወትር ስለ እናንተ እንጸልያለን።
12 ደግሞም እንደ አምላካችንና[ለ] እንደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ መጠን የጌታችን የኢየሱስ ስም በእናንተ ዘንድ እንዲከብርና እናንተም በእርሱ እንድትከብሩ ይህን እንጸልያለን።

## የዐመፅ ሰው

2 ወንድሞች ሆይ፤ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱም ስለ መሰብሰባችን ይህን እንለምናችኋለን፤
2 በመንፈስ መገለጥ ወይም በቃል ወይም

1፥1 ሐሥ15፥22፤ 16፥1፤ 17፥1፤ 1ተሰ1፥1
1፥2 ሮሜ1፥7
1፥3 ሮሜ1፥8፤ ኤፌ5፥20፤ 1ተሰ3፥12
1፥4 2ቆሮ7፥14፤ 1ተሰ1፥3፥6፤ 2፥14፤ 3፥3
1፥5 ሉቃ20፥35፤ ፊል1፥28
1፥6 ሉቃ18፥7፥8፤ ሮሜ12፥19፤ ቈላ3፥25፤ ራእ6፥10
1፥7 ሉቃ17፥30፤ ዕብ10፥27፤ 12፥29፤ 2ጴጥ3፥7፤ ይሁ1፥14፤ ራእ1፥14
1፥8 መዝ79፥6፤ ኢሳ66፥15፤ ኤር10፥25፤ ሮሜ2፥8፤ 2ቆሮ2፥12፤ ገላ4፥8
1፥9 2ነገ17፥18፤ ኢሳ2፥10፥19፤ ፊል3፥19፤ 1ተሰ5፥3፤ 2ተሰ2፥8፤ 2ጴጥ3፥7
1፥10 ዮሐ17፥10፤ 1ቆሮ1፥6፤ 3፥13
1፥11 ቍ5፤
1፥11 ሮሜ1፥10፤ 8፥28፤ 15፥14፤ 1ተሰ1፥3 1፥12 ኢሳ24፥15፤ ፊል2፥9-11 2፥1 ማር13፥27፤ 1ተሰ2፥19፤ 4፥15-17 2፥2 ቍ15፤ 1ቆሮ1፥8፤ 2ተሰ3፥17፤ 2ጢሞ2፥18

[ሀ] 1፥1 ግሪኩ ስልዋኖስ ይላል
[ለ] 1፥12 ወይም እንደ አምላካችን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ

**1፥5 የእግዚአብሔር ፍርድ ቅን መሆኑን፤** የተሰሎንቄ ምእመናን በስደትና በመከራ ውስጥ እያሉ በእምነታቸው ጽኑ ነበሩ (ቍ 4)። ሁኔታቸው የእግዚአብሔርን ቅን ፍርድ «የሚያመለክት» ነበር፤ ይኸውም የተሰሎንቄ ምእመናን ለእርሱ ጸጋና ሥቃይ ይቀበሉለት ለነበረው መንግሥት ብቁ ሆነው ይገኙ ዘንድ እግዚአብሔር የሰጠው ፍርድ ነው። ኢፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚቀበሉት ሥቃይ አሳዳጆቻቸው የራሱን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚቃወሙና ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፍርድና የኀጢአት ብድራት እንደሚቀበሉ ያመለክታል (ቍ 5-9)።

**1፥7 ለእናንተም ሆነ ለእኛ … ዕረፍት ይሰጠናል፤** በታላቁ የመከራ ዘመን ጅማሬ ላይ እግዚአብሔር ክፉዎች ለሠሩት ሥራ በበቀል ሊከፍላቸው (ቍ 6) የሚጀምር ቢሆንም (ቍ 6 እንዲሁም በገጽ 1471 ላይ፣ *«ታላቁ መከራ»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) የመጨረሻው የኀጢአት ብድራት የሚከፈለው (ቍ 6-9) በፍጻሜው ዘመን ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻውን ፍርድ ሊሰጥ ወደ ምድር በሚመጣበት ጊዜ ብቻ ነው (ቍ 7-10፤ ራእ 19፥11-21)። በተመሳሳይ ሁኔታም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ከፊል ዕረፍት የሚመጣው፣ ከእርሱ ጋር ሁል ጊዜ አብረውት ይሆኑ ዘንድ ከምድር ነጥቆ ሲወስዳቸው ነው (በገጽ 1907 ላይ፣ *«ንጥቀት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ ነገር ግን ሙሉ ዕረፍት የሚሆነው በክፉ ላይ ሲፈረድና የሰውን ዘር ሊገዛ ጌታ ኢየሱስ ከቅዱሳኑ ጋር ወደ ምድር ሲመለስ ነው። ሙሉ ዕረፍት ማለት በመጨረሻው ቀን ክርስቶስ በእናንተ ሲከብርና እናንተም በእርሱ ክብራችሁ ስታዩ ነው (ቍ 12)። ውጤቱም ሙሉ ድል ነው፤ ይኸውም ጽድቅ ሲገዛ፣ ኀጢአት ሲሸነፍና የክርስቶስ ታማኝ ተከታዮች ሲፈረድላቸው ነው (ራእ 6፥9-11፤ 19፥14-15)።

**1፥9 በዘላለም ጥፋት፤** ይህ ወደፊት ክፉዎች በዘላለም ቅጣት ሥር ስለሚሆኑበት ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ በግልጽ የተናገረው መልእክት ነው (በማቴ 10፥28 እና ስለ ገሃነም የተጠቀሰውን ማብ ይመ)።

**1፥10 ሊከብር … በሚመጣበት፤** ይህ ምንባብ አማኞች ክርስቶስን በአየር ለመቀበል ከምድር ተነጥቀው ስለሚወሰዱበት ጊዜ የሚናገር አይደለም (ዮሐ 14፥2-3፤ 1ተሰ 4፥17)፤ ነገር ግን የሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ የአሁኑን የምድር ሥርዐት ለማጥፋትና ሺህ ዓመት በምድር ላይ የሚገዛበትን ዘመን ለማወጅ በኀይልና በታላቅ ክብር የሚገለጥበትን ጊዜ ነው (ራእ 19፥11—20፥4)።

**2፥1 ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት፤** በአንደኛ ተሰሎንቄ መልእክቱ ሐዋርያው ጳውሎስ እውነተኛ አማኞች ጌታን በአየር ለመቀበል እንደሚነጠቁ እንዲሁም ከአምላካቸው ጋር ለዘላለም እንደሚኖሩ በማስረገጥ ተናግሮአል (1ተሰ 4፥13-18)። ይህም በመሆኑ ከሚመጣው ከእግዚአብሔር ቍጣ ያመልጣሉ (1ተሰ 1፥10፤ 5፥9-10)። ይሁን እንጂ የጌታ ቀን እንደ ጀመረና የእግዚአብሔር የመጨረሻ መዓት በምድር ላይ እየወረደ እንደ ሆነ አሁን በዚህ ጊዜ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ያስተምሩ ነበር (የሚቀጥለውን ማብ ይመ)።

**2፥2 ከአእምሮአችሁ አትናወጡ፤ አትደንግጡም፤** የተሰሎንቄ ምእመናን ስለ ጌታ ቀን የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የሚሉትን በመስማት ደንግጠው ነበር (ያለፈውን ማብ ይመ)። የእግዚአብሔር የቍጣው ቀን ገና ስላልደረሰ መጨነቅ እንደሌለባቸው ይነግራቸዋል። የቍጣው ቀን መድረሱን የሚያመለክቱት

ከእኛ እንደ ተላከ መልእክት የጌታ ቀን
ደርሶአል ብላችሁ ፈጥናችሁ ከአእምሮአ
ችሁ አትናወጡ፤ አትደንግጡም። 3ማንም
ሰው በምንም መንገድ አያታላችሁ፤ እስቀ
ድሞ በመፅ ሳይነሣ፣ ለጥፋት የተመደበ
ውም የዐመፅሖ ሰው ሳይገለጥ ያ ቀን
አይመጣምና። 4እርሱም አምላክ ከተባለና
ከሚመለከው ነገር ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ
ከፍ የሚያደርግ ተቃዋሚ ነው፤ እርሱም
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተቀምጦ፣ "እኔ
አምላክ ነኝ" እያለ ዐዋጅ ያስነግራል።
5ከእናንተ ጋር በነበርሁበት ጊዜ
እነዚህን ነገሮች ነግሬአችሁ እንደ ነበር ትዝ
አይላችሁምን? 6በራሱ ጊዜ ይገለጥ ዘንድ
አሁን ምን እንደሚከለክለው ታውቃላችሁ።
7የዐመፅ ምስጢር አሁንም እንኳ
እየሠራ ነውና፤ ነገር ግን ይህ የሚሆነው
የሚከለክለው ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ
ብቻ ነው 8ከዚያም በኋላ ጌታ ኢየሱስ በአፉ
እስትንፋስ የሚያ ስወግደውና በምጽአቱም
ክብር ፈጽሞ የሚያጠፋው ዐመፀኛ
ይገለጣል። 9የዐመፀኛው አመጣጥ በሰይጣን
አሠራር ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ ይህም
በሐሰተኛ ታምራት በምልክቶችና በድንቅ
ነገሮች ሁሉ ይሆናል፤ 10እንዲሁም ይድኑ
ዘንድ እውነትን ባለ መውደድ የሚጠፉትን
ሰዎች በሚያታልል በተለያየ የክፋት ሥራ
ይመጣል። 11በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር

2፥3 ቍ8፤ ዳን7፥25፤ 8፥25፤ 11፥36፤ ማቴ24፥10-12፤ ማር13፥5፤ ራእ13፥5፡6
2፥4 ኢሳ14፥13፡14፤ ሕዝ28፥2፤ 1ቆሮ8፥5
2፥5 1ተሰ3፥4
2፥6 ቍ7
2፥7 ቍ6
2፥8 ቍ3፤ ኢሳ11፥4፤ ሉቃ17፥30፤ ራእ2፥16፤ 19፥15
2፥9 ማቴ4፥10፤ 24፥24፤ ዮሐ4፥48፤
2፥9 ራእ13፥13 2፥10 ምሳ4፥6፤ የሐ3፥17-19፤ 1ቆሮ1፥18 2፥11 ሮሜ1፥25-28፤ ማቴ24፥5፤ ማር13፥5
1ጢሞ 6፥14-15

ሖ2፥3 አንዳንድ ቅጆች የኃጢአት ይላሉ

የሚከተሉት ሁለት ነገሮች ናቸው፤ (1) አስቀድሞ አንድ ታላቅ ዐመፅ ይነሣል፤ (2) የዐመፅ ሰው ይገለጣል (ቍ 3)። ሐዋርያው ጳውሎስ፣ "የሚከለክለው ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ ብቻ" ይህ እንደማይሆን በመቀጠል ተናግሮአል (ቍ 7)።

"በመንፈስ መገለጥ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደ ተላከ መልእክት" የሚሉት ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገራቸው ቃላት የሐሰት ትምህርት በልሳንና በተተረጐመ ልሳን ወይም በትንቢት አማካይነት ይተላለፍ እንደ ነበር ያመለክታል (1ቆሮ 14፥29 እና ልሳንና ትንቢትን መፈተን በሚለው ላይ የተሰጠውን ማብ ይመ)።

**2፥3 ያ ቀን አይመጣምና፤** ሐዋርያው ጳውሎስ የጌታ ቀን ሲደርስ ምልክት የሚሆኑ ሁኔታዎችን በማመልከት በዘመን መጨረሻ የዐመፅ ሰውና በርከሰት ደስ የሚላቸው የሚያደርሱትን ጥፋት በዝርዝር ይገልጻል፤ የሁነቶቹ ቅደም ተከተል የሚከተለው ነው፤ (1) በመላ የቤተ ክርስቲያን ዘመን "የዐመፅም ምስጢር" እየሠራ መሆኑ (ቍ 7) ፍጻሜው እንደ ደረሰ ያሳስበናል። ታሪክ ወደሚጠቃለያው እየተቃረበ እያለ ክፋትም ያለምንም እገዳ በሚሥጋጤ ላይ ይገኛል። (2) ያ ኀይል የበረታ ሲሄድ ክሕደት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል (ቍ 3 ይመ፤ ከማቴ 24፥12፤ 2ጢሞ 4፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)። (3) "የዐመፅ ምስጢርን" የሚከለክለው ማለትም የሚያግደው ኀይል ከመንገድ ይወገዳል (ቍ 6-7)። (4) ከዚያም የዐመፅ ሰው ይገለጣል (ቍ 3-4፡7፡9-10)። (5) ክሕደት በእግዚአብሔ ርና በቃሉ ላይ በማመፅ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ይደርሳል፤ እግዚአብሔርም እውነትን በማይወዱ ላይ የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል (ቍ 9-11)። (6) ከጥቂት ጊዜ በኋላም የዐመፅ ሰው በክፋት ደስ ከሚላቸው ሁሉ ጋር ይጠፋል (ቍ 12)፤ ይህ የሚሆነው ከታላቁ መከራ በኋላ ክርስቶስ ሲመጣ ማለትም በዘመን ፍጻሜ ላይ ነው (ቍ 8፤ ራእ 19፥20-21)።

**2፥3 ዐመፅ ሳይነሣ ... የዐመፅ ሰው ሳይገለጥ፤** ስለ "ዐመፅ" እና ስለ "ዐመፅ ሰው" ለመረዳት በገጽ 1913 ላይ፣ "*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥6 አሁን ምን እንደሚከለክለው ታውቃላችሁ፤** የዐመፅን ሰው የሚከለክለው አንድ ነገር ወይም አንድ ሰው ነው። ይህ የሚከለክለው ከመንገድ ሲወገድ የጌታ ቀን ያኔ ይጀምራል (ቍ 7 እንዲሁም በገጽ 1913 ላይ፣ "*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥7 የዐመፅ ምስጢር አሁንም እንኳ እየሠራ ነውና፤** የዐመፅ ምስጢር በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሁሉ ካለው የክፋት ኀይላት ድርጊት በስተጀርባ የሚሠራ ሲሆን፣ ለዐመፅና ለዐመፅ ሰውም መንገድን የሚያዘጋጅ ነው። (1) የማያምኑትን በማጥመድ ውስጥ ለውስጥ የሚሠራ ኀይል ሲሆን፣ በቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ብዙዎችን ከእውነተኛው እምነት ፈቀቅ እንዲሉ በማድረግ ክሕደትን በተሳበሰችው ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ያለውን ሐሰት እንዲቀበሉ ያደርጋል። እውነተኛ በሆነው በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነትና በመለኮታዊው ሕግ ላይ ተቃውሞን የሚያስነሣ መንፈስን ወይም እንቅስቃሴን የሚያካትት ነው፤ ከግብረገባዊ እገዳ ነጻ መሆንንና ኀጢአት በማድረግ ደስ መሰኘትንም የሚሻ ነው (ቍ 10-12፤ ቍ 12 እና ማብ ይመ)። (2) ይህ መንፈስ ሐዋርያው ጳውሎስ በነበረበት ዘመን ያለ ቢሆንም በተለይ በዘመን መጨረሻ ላይ በዓለምና በክርስትና ውስጥ ተንሠራፍቶ ይገኛል (ማቴ 24፥11 እና ማብ፤ 2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1913 ላይ፣ "*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥8 ጌታ ኢየሱስ ... የሚያስወግደውና፤** ሰይጣንና የዐመፅ ሰው የማታለልና የክፋት ሥራቸውን ከሠሩ በኋላ (ቍ 9-10) ክርስቶስ በታላቁ መከራ መጨረሻ ላይ ወደ ምድር ሲመጣ ይወገዳሉ (ራእ 19—20 እና ማብ ይመ)።

**2፥9 በሐሰተኛ ታምራት፣ በምልክቶችና በድንቅ ነገሮች ሁሉ፤** ዐመፀኛው ሰው ስለሚያከናውነው ድርጊት በዝርዝር ለመረዳት በገጽ 1913 ላይ፣ "*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥10 እውነትን ባለመውደድ፤** ፍጥረት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ውስጥ ማእከላዊው ጕዳይ ቃሉንና እግዚአብሔርን አለማክበሩን ወይም እነዚህን መውደዱን የሚመለከት ነው። ይህ ምላሽ በዚህ ዘመን መጨረሻም ትኩረት የሚደረግበት ዋና ጕዳይ ነው። ከእግዚአብሔር ድነትን ማግኘት የሚችሉ በክርስቶስ በማመን እውነትን በፍጹም ልባቸው የሚወዱ፣ እግዚአብሔር የተናገረውን ሳይጠራጠሩ የሚያምኑና ከእውነት ጋር የሚቃረነውን ማናቸውንም አዲስ መገለጥ ወይም ትምህርት የሚቃወሙ ብቻ ናቸው (ማቴ 24፥5፡11 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1471 ላይ፣ "*ታላቁ መከራ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**2፥11 የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል፤**

# የሐሰተኛው ክ

*2ተሰ 2፥3-4 "ማንም ሰ*
*ለጥፋት የተመደበውም*
*አምላክ ከተባለና ከሚመ*
*ተቃዋሚ ነው፤ እርሱም*
*እያለ ዐዋጅ ያስነግራል።*

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ክር
በቅዱሳኑ ላይ የሰይጣንን የመጨ
ጋር ያነጻጽሩ)። ሐዋርያው
እና "ለጥፋት የተመደበው"
ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚጠራ
አውሬ" (ራእ 17፥3) እና "አ

የሐሰተኛው ክርስቶስ መምጣ
ድንገት (በገጽ 1907 ላይ፣ "
ማስጠንቀቂያ አይሆንም። የእ
ከመምጣቱ በፊት ቢያንስ ቢያ
ላይ እየሠራ ያለው "የዐመፅ
መነሣት አለበት (2፥3)፤ (3)
(1) በዓለም ከሚገኘው ክክ
(2ተሰ 2፥7 እና ማብ ይመ)፣
እስከሚያደርጋና እስከሚያዋር
የተነሣ የብዙዎች ፍቅር ይቀዘ
ትሩፋን በአዲስ ኪዳን በተገለ
25፥10፤ ሉቃ 18፥7፤ ራእ 2፥7 እ
የመንፈስን ሰይፍ፤ በመያዝ ተ
(2) "ዐመፅ"(ግሪክ፡ "አፖ
"መተው" የሚለው ይከሠታል
ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት
(ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስና ቃ
ከመንፈሳዊውና ከአስተምህሮአ
ስለሚችለው አስከፊ ገጽታ አመ
ጋር ያነጻጽሩ)። በተለይም ሐዋ
እግዚአብሔር በሌለበት ሁኔታ
(ለ) ይህ "ዐመፅ" በቤተ
(1) ሥነ መለኮታዊ ክሕደት
ትምህርት መሉ በሙሉ ወይ
2ጢሞ 4፥3)። ሐሰተኛ መሪዎ
ከኢግብረገባዊነት ለመለየት እ
የሚያቀርበውን ጥሪ ይቃወማሉ
ማድረስ ማእከል ያደረገ የሐሰ
። (2) ግብረገባዊ ክሕደት ይ
ወደ ኀጢአትና ወደ ኢግብረገባ
ሰዎች እግዚአብሔር በቃሉ ው
አስተምህሮና አዲስ ኪዳናዊ ትም
እና በገጽ 1962 ላይ፣ "ክሕደት
ክርስቲያናት የአባላት ቍጥር
ማንኛውንም ኀጢአት በቸልታ

# የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን

*2ተሰ 2፥3-4 "ማንም ሰው በምንም መንገድ አያታላችሁ፤ አስቀድሞ ዐመፅ ሳይነሣ፣ ለጥፋት የተመደበውም የዐመፅ ሰው ሳይገለጥ ያ ቀን አይመጣምና። እርሱም አምላክ ከተባለና ከሚመለከው ሁሉ ነገር በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርግ ተቃዋሚ ነው፤ እርሱም በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ተቀምጦ፣ "እኔ አምላክ ነኝ" እያለ ዐዋጅ ያስነግራል።"*

በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ክርስቶስ መንግሥቱን በምድር ላይ ከመመሥረቱ በፊት፣ በክርስቶስና በቅዱሳኑ ላይ የሰይጣንን የመጨረሻ ጥፋት የሚመራው ሐሰተኛው ክርስቶስ ይመጣል (ከ1ዮሐ 2፥18 ጋር ያነጻጽሩ)። ሐዋርያው ጳውሎስ ሐሰተኛውን ክርስቶስ የሚጠራው፣ "የዐመፅ ሰው" እና "ለጥፋት የተመደበው" (2ተሰ 2፥3) በማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በሌላ ስፍራ ሐሰተኛው ክርስቶስ የሚጠራበት ስም፣ "ከባሕር የወጣው አውሬ" (ራእ 13፥1-10)፣ "ቀይ አውሬ" (ራእ 17፥3) እና "አውሬው" (ራእ 17፥8፡16፤ 19፥19-20፤ 20፥10) የሚል ነው።

**የሐሰተኛው ክርስቶስ መምጣት ምልክቶች፤** የሐሰተኛው ክርስቶስ አመጣጥ እንደ መንጠቅ ድንገት (በገጽ 1907 ላይ፣ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ያለ ማስጠንቀቂያ አይሆንም። የእርሱን መምጣትና መገለጥ አያሌ ምልክቶች ያሳያሉ። ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት ቢያንስ ቢያንስ የሚከተሉት ሦስት ሁነቶች መከሠት አለባቸው፤ (1) በዓለም ላይ እየሠራ ያለው "የዐመፅ ምስጢር" እጅግ መጨመር አለበት (2ተሰ 2፥7)፤ (2) "ዐመፅ" መነሣት አለበት (2፥3)፤ (3) "የሚከለክለው" ከመንገድ መወገድ አለበት (2፥7)።

(1) በዓለም ከሚገኘው ከክፉ ኀይላት እንቅስቃሴ በስተጀርባ የሚሠራው "የዐመፅ ምስጢር" (2ተሰ 2፥7 እና ማብ ይመ)፤ የመጽሐፍ ቅዱስን የተቀደሰ መለኪያና ትእዛዝ ፈጽሞ ለመጣለቂያ እስከሚያደርግና እስከሚያዋርድ ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ይጨምራል። የዐመፅ መንፈስ ከማየሉ የተነሣ የብዙዎች ፍቅር ይቀዘቅዛል (ማቴ 24፥10-12፤ ሉቃ 18፥8)። ይሁን እንጂ ታማኝ የሆኑ ትሩፋን በአዲስ ኪዳን በተገለጠው ሐዋርያዊ እምነት መሠረት ጸንተው ይቆማሉ (ማቴ 24፥13፤ 25፥10፤ ሉቃ 18፥7፤ ራእ 2፥7 እና ማብ ይመ)። በእነዚህም ታማኝ ሰዎች አማካይነት ቤተ ክርስቲያን የመንፈስን ሰይፍ በመያዝ ተዋጊ ቤተ ክርስቲያን ትሆናለች (ኤፌ 6፥11 እና ማብ ይመ)።

(2) "ዐመፅ"(ግሪክ፡ "አፖስታሲያ") ቃል በቃል ሲተረጐም "መለየት"፣ "መክዳት" ወይም "መተው" የሚለው ይከሠታል። በመጨረሻው ዘመን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙዎች ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው እውነት ተለይተው ይሄዳሉ።

(ሀ) ኢየሱስ ክርስቶስና ጳውሎስ ሁለቱም የምትታየው ቤት ክርስቲያን ከግብረገባዊው፣ ከመንፈሳዊውና ከአስተምህሮአዊው ሁኔታ አንጻር ይህ ዘመን በሚያበቃበት ጊዜ ሊኖራት ስለሚችለው አስከፊ ገጽታ አመልክተዋል (ከማቴ 24፥5፡10-13፡24፤ ከ1ጢሞ 4፥1፤ ከ2ጢሞ 4፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ)። በተለይም ሐዋርያው ጳውሎስ በመጨረሻው ዘመን አብያተ ክርስቲያናት ፈሪሀ እግዚአብሔር በሌለበት ሁኔታ ሊወረሩ እንደሚችሉ በአጽንዖት ተናግሯል።

(ለ) ይህ "ዐመፅ" በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚከተሉት ሁለት ገጽታዎች ይኖሩታል፤ (1) ሥነ መለኮታዊ ክሕደት ይታያል፤ ይህም ከመጀመሪያው ከክርስቶስና ከሐዋርያት ትምህርት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መለየትና ይህንንም መቃወም ነው (1ጢሞ 4፥1፤ 2ጢሞ 4፥3)። ሐሰተኛ መሪዎች "ሐሰተኛ ድነትን" እና ርካሽ ጸጋን በማቅረብ ክርስቶስ ለንስሓ ከኢግብረገባዊነት ለመለየት እንዲሁም ለእግዚአብሔርና ለጻድቅ መለኪያዎቹ ታማኝ ለመሆን የሚያቀርበውን ጥሪ ይቃወማሉ (2ጴጥ 2፥1-3፡12-19)። ሥጋዊ ፍላጎትንና የግል ምኞትን ከግብ ማድረስ ማእከል ያደረገ የሐሰት ወንጌል ተወዳጅ ይሆናል (2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ ይመ)። (2) ግብረገባዊ ክሕደት ይከሠታል፤ ይህም በክርስቶስ የተገኘውን የድነት ግንኙነት አቋርጦ ወደ ኀጢአትና ወደ ኢግብረገባዊነት ዘወር ማለት ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እምነት የሚክዱ ሰዎች እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ያስቀመጠውን ግብረገባዊ መለኪያ ትተው ሳለ ትክክለኛውን አስተምህሮና አዲስ ኪዳናዊ ትምህርትን እንደሚሰጡ ሊናገሩ ይችላሉ (ኢሳ 29፥13፤ ማቴ 23፥25-28 እና በገጽ 1962 ላይ፤ "ክሕደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ብዙ አብያተ ክርስቲያናት የአባላት ቍጥር እንዳይቀንስ፣ ገንዘብ፣ ስኬትና ክብር እንዳይታጣ በመፍራት ማንኛውንም ኀጢአት በቸልታ ያልፋሉ (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)። ሥቃይ መቀበልን

(ፊል 1፥29)፣ ኀጢአትን ፊት ለፊት መቃወምን (ሮሜ 8፥13)፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት መሥዋዕትነት መክፈልንና ራስን መካድ የሚጠይቀው የመጽቀሉ ወንጌል እምብዛም ቦታ የለውም (ማቴ 24፥12፤ 2ጢሞ 3፥1-5፤ 4፥3)።

(ሐ) የቤተ ክርስቲያን ታሪክና በመጨረሻው ዘመን እንደሚመጣ የተነገረለት ክሕደት መፈጸም ሁለቱም በዘመናት ሁሉ በሂደት ላይ ያለውን ቀጣዩን የእግዚአብሔርን መንግሥት እንቅስቃሴ አማኞች ሁሉ እስከመጨረሻው በቸልታ እንዳይመለከቱት ማስጠንቀቂያ ይሆናሉ። በቤተ ክርስቲያን ታሪክ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በእግዚአብሔርና በእርሱ ቃል ላይ የሚነሣው ተቃውሞ በሚያስደንቅ ሁኔታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ይደርሳል። ይሁን እንጂ የጌታ ቀን እውነቱን በሚቃወሙ ሁሉ ላይ የእግዚአብሔርን ቍጣ ያወርዳል (1ተሰ 5፥2-9)።

(መ) ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግሥትና ጽድቁ በዓለም ላይ የሚቀዳጁት የመጨረሻ ድል የሚወሰነው ቀስ በቀስ እድገቱ እየጨመረ በሚመጣው በምታምነው ቤተ ክርስቲያን ስኬት ሳይሆን፣ በመጨረሻ እግዚአብሔር ራሱ በጻድቅ ፍርዱ ወደ ዓለም ሰብሮ ጣልቃ ሲገባ ብቻ ነው (ራእ 19-22 ይመ፤ 2ተሰ 2፥7-8 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 2ጴጥ 3፥10-13 እና የይሁዳን መጽሐፍ ይመ)።

(3) ወሳኝ የሆነው ሁነት ሊከሠት የሚችለው "የዐመፅ ሰው" ከመገለጡና የጌታ ቀን ከመጀመሩ በፊት ነው (2ተሰ 2፥2-3)፤ ይኸውም የዐመፅን ሰውና የዐመፅን ምስጢር የሚከለክለው (2፥7) "ከመንገድ ሲወገድ" ነው (2፥3-6)። የሚከለክለው ከመንገድ ሲወገድ የጌታ ቀን ይጀምራል (2፥6-7)።

(ሀ) "የሚከለክለው" የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክፋውን፣ የዐመፅ ሰውንና፣ ሰይጣንን (2ተሰ 2፥9) የማገድ ብቸኛ ኀይል ያለውን መንፈስ ቅዱስን ነው። የሚከለክለው የሚለው ቃል የተጠቀሰው ተባዕታይ ጾታን (2፥7) እና ግዑዝ ጾታን (2፥6) በሚያመለክት መስተአምር ነው። እንደዚሁም መንፈስ ቅዱስ በግሪኩ የተጠቀሰበት ቃል ተባዕታይ ጾታና ግዑዝ ጾታን በሚያመለክት ተውላጠ ስም ነው (ዘፍ 6፥3፤ ዮሐ 16፥8 እና ማብ፤ ሮሜ 8፥13፤ በገላ 5፥17 ላይ መንፈስ ቅዱስ ሥጋን መቃወሙ የተጠቀሰበትን ይመ)።

(ለ) የመጨረሻው የሰባቱ ዓመት ታላቅ መከራ ሲጀመር፣ መንፈስ ቅዱስ ከመንገድ ይወገዳል። ይህም እርሱ ከዓለም ይወሰዳል ማለት ሳይሆን፣ ዐመፅና ሐሰተኛው ክርስቶስ እንዳይገቡ የሚያደርገውን የማገድና የመከልከል ሥራውን ለጊዜው ያቆማል ማለት ነው። በኀጢአት ላይ የነበረው እገዳ ሁሉ ይነሣል፤ በሰይጣን የሚቀሰቀስ ዐመፅም ይጀምራል። ይሁን እንጂ ሰዎች በኀጢአታቸው እንዲወቀሱ፣ በክርስቶስ እንዲያምኑና በእርሱ ኀይል እንዲታጠቁ ያደርግ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ በታላቁ ዘመን በምድር ላይ ይኖራል (ራእይ 7፥9፡14፤ 11፥1-11፤ 14፥6-7)።

(ሐ) መንፈስ ቅዱስ መንገድ ሲለቅ፣ የዐመፅ ሰው ስፍራ ይይዛል (2ተሰ 2፥3-4)። እውነትን በማይወዱ ሁሉ ላይ እግዚአብሔር የስሕተትን አሠራር ይልክባቸዋል (2፥11 እና ማብ ይመ)። የዐመፅ ሰው የሚናገረውን ሁሉ ይቀበላሉ፤ የሰው ዘርም ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ እጅግ አስከፊ ርኩሰት ውስጥ ይገባል።

(መ) የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ በሆነችው በቤተ ክርስቲያን አማካይነት የመንፈስ ቅዱስ ኀጢአትን የማገድ አገልግሎት በስፋት ይከሄዳል (1ቆሮ 3፥16፤ 6፥19)። ስለዚህ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በዚሁ ጊዜ የታማኞች መነጠቅ ለመከሠቱ (1ተሰ 4፥17) የመንፈስ ቅዱስ መንገድ መልቀቅ ጥሩ ማረጋገጫ እንደሆነ ያምናሉ፤ ይኸውም አብያተ ክርስቲያናቱን ወደ ራሱ ለመሰብሰብና ከሚመጣው ፍርድ ሊያድናቸው ክርስቶስ የሚመለስበት ጊዜ (1ተሰ 1፥10) ከጌታ ቀንና የዐመፅ ሰው ከሚገለጥበት ጊዜ በፊት ይሆናል ማለት ነው (በገጽ 1907 ላይ፥ "ንጥቀት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(ሠ) አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁራን በ2ተሰ 2፥6 ላይ በግዑዝ ጾታ የተጠቀሰው "ከልካይ" የሚለው መንፈስ ቅዱስንና የእርሱን የማገድ አገልግሎት ያመለክታል ሲሉ፣ በ2ተሰ 2፥7 ላይ በተባዕታይ ጾታ የተጠቀሰው "የሚከለክለው" የሚለው ደግሞ ወደ ክርስቶስ በመሰብሰብ ከመንገድ የተወገዱትን አማኞችን ማለትም ከጌታ ጋር እንዲሆኑ ክርስቶስን በአየር ለመቀበል የተነጠቁትን (1ተሰ 4፥17) የሚያመለክት ነው ይላሉ።

**የሐሰተኛው ክርስቶስ ሥራዎች፤** የጌታ ቀን ሲጀምር፣ "የዐመፅ ሰው" ይገለጣል። የዘመን መጨረሻ ከመድረሱ ከሰባት ዓመት በፊት ከእስራኤል ጋር ኪዳን ያደርጋል፤ የዓለምም ገዥ ይሆናል (ዳን 9፥27 ይመ)። (1) ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ከእስራኤል ጋር የገባውን ኪዳን ሲያፈርስ፣ የዓለም ገዥ ሲሆን፣ ራሱን አምላክ በማድረግ ሲያውጅ፣ የኢየሩሳሌምን ቤተ መቅደስ ሲያረክስ (በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ እግዚአብሔር እንዳይመለክ ሲያደርግና (2ተሰ 2፥4:8-9)፥ የፖለስቲናን ምድር ሲያጠፋ

(ዳን 9፥27 እና ማብ፤ 11፥36-45 እና ማብ ይመ) የእርሱ ማንነት ይረጋገጣል።

(2) ሐሰተኛው ክርስቶስ ራሱን አምላክ በማድረግ ያውጃል፤ ለክርስቶስ ታማኝ በመሆን የጸኑትንም ክፉኛ ያሳድዳል (ራእ 11፥6-7፤ 13፥7፡15-18፤ ዳን 7፥8፡24-25 እና ማብ ይመ)። ዐዋጁ ከሚነገርበት ከታላቁ ቤተ መቅደስ በመሆን በግልጽ እንዲመለክ ሰዎችን ያስገድዳል (ከዳን 7፥8፡25፤ 8፥4፤ 11፥31፡36 ጋር ያነጻጽሩ)። የሰው ዘር ይህን መለኮታዊ ማዕረግ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ሲሻው ኖሮአል (2ተሰ 2፥8 እና ማብ፤ ራእ 13፥8፡12 እና ማብ እንዲሁም በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(3) "የዐመፅ ሰው" የስሕተት አሠራርን ለማስፋፋት በሰይጣን ኀይል አማካይነት ታላላቅ ምልክቶችን፣ ድንቆችንና ታምራትን ያሳያል (2ተሰ 2፥9)። "ሐሰተኛ ታምራት" የሚለው ሐረግ የሚያመለክተው ሰዎች ሐሰትን እንዲያምኑ የሚያደርግ ተጨባጭ ዲበ ተፈጥሮአዊ ታምራትን ነው፤ (ሀ) እነዚህ ዲበ ተፈጥሮአዊ ታምራት በዓለም ዙሪያ በአንድ ጊዜ በቴሌቪዥን ፕሮግራም ሊታዩ ይችላሉ። በድርጊቱ በሚሊዮን የሚቈጠሩ ሰዎች ይደነቃሉ፤ ለእግዚአብሔር ቃል እውነት ጥልቅ የሆነ እምነት ወይም ፍቅር ስለሌላቸው ጒልቶ በወጣ ዝነኛ መሪ ይታለላሉ፤ በእርሱም ያምናሉ (2፥9-12)፤ (ለ) የሐዋርያው ጳውሎስ (2ተሰ 2፥9) እና የኢየሱስ ክርስቶስ (ማቴ 24፥24) የሁለቱም ቃሎች ታምራዊ የሆነ ማንኛውም ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ አድርገን በመቍጠር ማመን እንደሌለባቸው አማኞችን ያስጠነቅቃሉ። የተገለጡ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች (1ቆሮ 12፥7-10)፣ ከእግዚአብሔር ወይም ከመንፈስ ቅዱስ ተገኙ የሚባሉ መንፈሳዊ ተመክሮዎች ሰውየው ለክርስቶስና ለቅዱሳት መጻሕፍት ባለው ታማኝነት መፈተን አለባቸው።

**የሐሰተኛው ክርስቶስ መሸነፍ፤** በታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ በሐሰተኛው ክርስቶስ መሪነት ሰይጣን ብዙ ሕዝቦችን በአርማጌዶን ይሰበስባል፤ ዓለምንም ሁሉ ለውጊያ አስተባብሮ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ ጦርነትን ያውጃል (ዳን 11፥45 እና ማብ፤ ራእ 16፥16 እና ማብ ይመ)። ይህ ጊዜ ሲደርስ ክርስቶስ ይመለሳል፤ ታምራዊ በሆነ አሠራር ጣልቃ በመግባት ሐሰተኛውን ክርስቶስና ሰራዊቱን እንዲሁም ወንጌልን አልታዘዝ ያሉትን ሁሉ ይደመስሳቸዋል (ራእ 19፥15-21 እና ማብ ይመ)፤ ከዚያም ክርስቶስ ሰይጣንን ያስርና የራሱን መንግሥት በምድር ላይ ይመሠርታል (ራእ 20፥1-6 ይመ)።

በሐሰት እንዲያምኑ የስሕተትን አሠራር
ይልክባቸዋል፤ [12]ይህም የሚሆነው እውነትን
ያላመኑት ነገር ግን በክፋት ደስ ይላቸው
የነበሩ ሁሉ እንዲፈረድባቸው ነው።

### ጸንታችሁ ቁሙ

✝ [13]በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፤
እኛ ግን ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን
ልናመሰግን ይገባናል። ምክንያቱም እግዚአብሔር
እናንተን ከመጀመሪያ አንሥቶ በመ ንፈስ
1ጢሞ 1፥15-16 ተቀድሳችሁና በእውነትም አምናችሁ
እንድትድኑ መርጦአችኋል[ሀ]። [14]የጌታችን
የኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ተካፋዮች
እንድ ትሆኑም በወንጌላችን አማካይነት
ጠርቶአችኋል። [15]እንግዲህ ወንድሞች
ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በአንደበታችንም
ሆነ በመልእክታችን ያስተላለፍንላችሁን
ትምህርት[ለ] አጥብቃችሁ ያዙ።
[16]ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደግ
ሞም እኛን የወደደንና በጸጋው የዘላለም
መጽናናትና መልካም ተስፋን የሰጠን
እግዚአብሔር አባታችን፣ [17]ልባችሁን ያጽናኑት፤
በበጎ ሥራና በቃል ሁሉ ያበርቷችሁ።

2፥12 ሮሜ1፥32፤ 2፥8
2፥13 ሮሜ1፥8፤ ኤፌ1፥4፤ 1ተሰ5፥9፤ 1ጴጥ1፥2
2፥14 ሮሜ8፥28፤ 11፥29፤ 1ተሰ1፥5
2፥15 1ቆሮ11፥2፤ 16፥13
2፥16 ዮሐ3፥16፤ ፊል4፥20
2፥17 1ተሰ3፥2፤ 2ተሰ3፥3
3፥1 1ተሰ1፥8፤ 2፥13፤ 4፥1፤ 5፥25
3፥2 ሮሜ15፥31
3፥3 ማቴ5፥37፤ ሮሜ15፥31፤ 1ቆሮ1፥9
3፥4 2ቆሮ2፥3
3፥5 1ዜና29፥18
3፥6 ሉቃ7፥11፥14፤ ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ5፥4፤ 11፥2

### ለጸሎት የቀረበ ጥያቄ

3 በቀረውስ ወንድሞች ሆይ፤ በእናንተ
ዘንድ እንደ ሆነው የጌታ ቃል በፍጥነት
እንዲሠራጭና እንዲከበር ለእኛ ጸልዩልን፤
[2]ደግሞም ሰው ሁሉ እምነት ያለው ስለማይ
ሆን ከዐመፀኞችና ከክፉ ሰዎች እንድንድን
ጸልዩልን። [3]ጌታ ግን ታማኝ ነው፤ እርሱም
ያበረታችኋል፤ ከክፉውም ይጠብቃችኋል።
[4]እኛ ያዘዝናችሁን አሁን አደረጋችሁ፤ ወደ
ፊትም እንደምታደርጉ በጌታ እንታመናለን።
[5]ጌታ ልባችሁን ወደ እግዚአብሔር ፍቅርና ወደ
ክርስቶስ ጽናት ይምራው።

### ሥራ መፍታት እንደማይገባ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

[6]ወንድሞች ሆይ፤ ሥራ ፈት ከሆነና
ከእኛ በተቀበላችሁት ትምህርት[ሐ] መሠረት
ከማይኖር ወንድም እንድትርቁ በጌታ

[ሀ]2፥13 አንዳንድ ቅጆች እግዚአብሔር በኵራት እንድትሆኑ መርጦአ ችኋል ይላሉ
[ለ]2፥15 ወይም ወግ
[ሐ]3፥6 ወይም ወግ

ከልክዩ ከተወሰደና (በገጽ 1913 ላይ፣ *«የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) የዐመፅ ሰው ከተገለጠ በኋላ ለአንድ ለተወሰነ የሕዝብ ወገን የሚሆን የድነት እድል አይኖርም፤ (1) ይህ የተወሰነ የሕዝብ ወገን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ያሉትን ሁሉ የሚያካትት ሲሆን እነርሱም በበቂ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ከሰሙ በኋላ በፈቃደኝነትና ሆን ብለው እውነትን ባለመውደድ በዓለም ክፉ አሠራር ደስ መሰኘትን የመረጡ ናቸው (ቍ 10፥12 እና ማብ)።

(2) ለመውደድ ያልፈለጉትን እውነት (ቍ 12) እንዲያምኑ የሚያደርግ አጋጣሚ ፈጽሞ እንዳያገኙ እግዚአብሔር በእነዚህ ግለሰቦች ላይ ኀይለኛ የስሕተት አሠራርን ይልክባቸዋል። ለዘላለም «ሐሰትን» እንዲያምኑ ማለትም የዐመፀኛውን ቃል እንዲቀበሉ የተፈረደባቸው ናቸው።

(3) እግዚአብሔር ኀይለኛ የሆነን «የስሕተት አሠራር» የሚልክበት ዐላማ «እንዲፈረድባቸው ነው» (ቍ 12)። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ከተረዱ በኋላ ነገር ግን እውነትን ባለመውደድ በኀጢአት የሚገኝን ደስታ ለመረጡ « ... ለኀጢአት የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይኖርም፤ የሚቀረው ግን የሚያስፈራ ፍርድና የእግዚአብሔርን ጠላቶች የሚበላ ብርቱ እሳት መጠበቅ ብቻ ነው» (ዕብ 10፥26-27 እና በገጽ 1962 ላይ፣ *«ክሕደት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(4) በታላቁ መከራ ጊዜ ድነት የሚሰጠው የእውነትን ዕውቀት ለማግኘት ወይም ወንጌልን ለመስማትና ለመረዳት በቂ አጋጣሚ ላላገኙ ሰዎች ብቻ ነው (ከራእ 7፥14፤ 11፥3፤ 14፥6-7 ጋር ያነጻጽሩ)። በእነዚያ ቀናት ወንጌልን ከሚያውጁት ሰዎች መካከል ከእስራኤል ነገድ የሆኑት 144ሺ000 ዎቹ (ራእ 7፥4 እና ማብ ይመ)፣ ሁለቱ ምስክሮች (ራእ 11፥3 እና ማብ) እና መላእክት (ራእ 14፥6 እና ማብ ይመ) ይገኛሉ።

2፥12 **በክፋት ደስ ይላቸው የነበሩ፤** እውነትን ከመውደድ ይልቅ በክፋት ደስ መሰኘት (ቍ 10) በመጨረሻው ዘመን ለሚመጣው የእግዚአብሔር ፍርድ ወሳኝ ጕዳይ ነው። (1) ለእግዚአብሔር ቀኖና የተጻረጉት እውነትን የማይወዱ እንዲሁም በክፋትና በኢግብረገብነት ውስጥ በመዘፈቅ ደስ የሚሰኙ ናቸው (2ጢሞ 3፥1 እና ማብ ይመ)። እነርሱም ለሚለኮታዊ ፍርድ፣ ለሰይጣን አሳሳች አሠራና ለጨለማ ኀይል አልፈው የተሰጡ ናቸው (ሉቃ 23፥35 እና ማብ፤ ሮሜ 1፥32 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)።

(2) «በጌታ ቀን» ለፍርድ የሚዳረጉት (ቍ 2 እና ማብ ይመ) የማያምኑ ብቻ ሳይሆኑ፣ እውነተኛውን እምነት በመካድ የበደሉትም ጭምር ናቸው። በእግዚአብሔር ደስ ከመሰኘት ይልቅ በኀጢአት ደስ መሰኘትን መርጠዋል፤ የመጨረሻውን ዘመን ኢግብረገብነት የመቃወም በቂ ምንም የላቸውም (ቍ 3፥7 እና ማብ፤ 2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ ይመ)።

3፥1 **ለእኛ ጸልዩልን፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ለክርስቶስ ያደረገውን መፈጸም የቻለው በከፊል የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጸለየለት ጸሎት የተነሣ ነበር። ስለዚህ ሐዋርያው ያለ አማኞች የምልጃ ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ሙሉ በሙሉ እውን እንደማይሆን በመረዳቱ፣ ሁል ጊዜ ያገለገላቸው ሰዎች እንዲጸልዩለት ይፈልጋል (ከሮሜ 15፥30-32፤ ከ2ቆሮ 1፥11፤ ከፊል 1፥19፤ ከቈላ 4፥2፤ ከ1ተሰ 5፥25 ጋር ያነጻጽሩ)። ይህ የእግዚአብሔር መንግሥት መንፈሳዊ መርሕ ዛሬም ይሠራል። እኛ የሌሎች አማኞች ጸሎት ያስፈልገናል፤ እነርሱም የእኛ ጸሎት ያስፈልጋቸዋል። በአብያተ ክርስቲያናት በሚደረግ ጽኑ የምልጃ ጸሎት፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ይፈጸማል፤ የሰይጣን ዕቅድ ይፈርሳል (ቍ 3)፤ የመንፈስ ቅዱስ ሙሉ ኀይል ይገለጣል (ሐሥ 4፥24-33)።

3፥3 **ከክፉውም ይጠብቃችኋል፤** አማኞች ተግተው ቢጸልዩ፣ እግዚአብሔር ከሰይጣን እንደሚጠብቃቸው ርግጠኞች ሊሆኑ ይችላሉ። እነርሱን ሊያጠቃ የሚመጣ ማናቸውንም ፈተና ይቋቋሙ ዘንድ እግዚአብሔር ብርታትን ይሰጣቸዋል (1ቆሮ 10፥13፤ ዕብ 2፥18)፤ እንዲሁም ከአጋንንት ብርቱ ኀይላት ይጠብቃቸዋል (ኤፌ 6፥12 እና ማብ ይመ)።

3፥6 **ሥራ ፈት ከሆነና፤** ሥራ ፈቶች የሚያላግጡና

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እና
[7]የእኛን ምሳሌ እንዴት
እንደሚገባችሁ እናንተ
ታውቃላችሁና። ከእናንተ ጋር በ
ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነበርንም፤
የማንንም እንጀራ በነጻ አልበላ
ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላ
እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደክም
ነበር፤ [9]ይህን ያደረግነው ምሳሌ
እንድትከተሉ ብለን እንጂ የሚያስ
ነገር ከእናንተ ለማግኘት
ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም። [10]
ጋር በነበርንበት ጊዜ፣ "ሊሠራ
አይብላ" ብለን ይህን ትእዛዝ ሰ
ነበርና። [11]ከእናንተ አንዳንዶ
ፈቶች እንደ ሆኑ ሰምተናል፤ እነር
ሥራ እየዞሩ በሰው ጕዳይ ጣል
ናቸው። [12]እንደዚህ ያሉ ሰዎች
ሥራቸውን እንዲሠሩና እንጀ
እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስ

ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች
የቤተ ክርስቲያንን ለጋስነት ማትረፍ
(ከ1ተሰ 4፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በትክ
ሠርተው ኑሮአቸውን ከሚያሸንፉ ወን
ይቀበላሉ (ቍ 6-15)። (1) ከእነርሱ በመ
እንደዚህ ዐይነት ሰዎች መገሠጽ
ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተምራል
(2) በትክክለኛ ችግር ውስጥ ያ
እንደሚያስፈልግ ሐዋርያው ቢያደፋፍ
ኖሮአቸው ኑሮን ለማሸነፍ መሥራትን

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን፤ ⁷የእኛን ምሳሌ እንዴት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁና። ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ሥራ ፈቶች አልነበርንም፤ ⁸ደግሞም የማንንም እንጀራ በነጻ አልበላንም፤ ነገር ግን ከእናንተ በአንዳችሁም ላይ ሸክም እንዳንሆን ሌሊትና ቀን እንደክምና እንሠራ ነበር፤ ⁹ይህን ያደረግነው ምሳሌነታችንን እንድትከተሉ ብለን እንጂ የሚያስፈልገንን ነገር ከእናንተ ለማግኘት ሥልጣን ሳይኖረን ቀርቶ አይደለም። ¹⁰ከእናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ፣ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" ብለን ይህን ትእዛዝ ሰጥተናችሁ ነበርና። ¹¹ከእናንተ አንዳንዶች ሥራ ፈቶች እንደ ሆኑ ሰምተናል፤ እነርሱም ያለ ሥራ እየዞሩ በሰው ጉዳይ ጣልቃ የሚገቡ ናቸው። ¹²እንደዚህ ያሉ ሰዎች ተግተው ሥራቸውን እንዲሠሩና እንጀራቸውን እንዲበሉ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛቸዋለን፤ እንመክራቸዋለንም። ¹³እናንተ ግን ወንድሞች ሆይ፤ መልካም ሥራን ከመሥራት ከቶ አትታክቱ።

¹⁴በዚህ መልእክት ላይ ላለው ቃላችን የማይታዘዝ ማንም ቢኖር፣ እንደዚህ ያለውን ሰው በጥንቃቄ ተከታተሉት፤ በሥራ ውም እንዲያፍር ከእርሱ ጋር አትተባበሩ። ¹⁵ሆኖም እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ ጠላት አትቍጠሩት።

### የመጨረሻ ሰላምታ

¹⁶የሰላም ጌታ ራሱ በሁሉም ነገር ዘወትር ሰላም ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

¹⁷ይህንን ሰላምታ በገዛ እጄ የጻፍሁት እኔ ጳውሎስ ነኝ፤ የመልእክቶቼም ሁሉ መለያ ይህ ነው፤ አጻጻፌም እንደዚሁ ነው።

¹⁸የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

3፥7 ቍ9፤ 1ቆሮ4፥16
3፥8 ሐሥ18፥3፤ ኤፌ4፥28
3፥9 ቍ7፤ 1ቆሮ9፥4-14፥16
3፥10 1ተሰ3፥4፤ 4፥11
3፥11 ቍ6፥7፤ 1ጢሞ5፥13
3፥12 ኤፌ4፥28፤ 1ተሰ4፥1፥11
3፥13 ገላ6፥9
3፥14 ቍ6፤ ሮሜ16፥17፤ 1ቆሮ4፥14
3፥15 ገላ6፥1፤ 1ተሰ5፥14፤ ፊል16
3፥16 ሩት2፥4፤ ሮሜ15፥33
3፥17 1ቆሮ16፥21
3፥18 ሮሜ16፥20

*ለመሥራት ፈቃደኛ ያልሆኑ ሰዎች ናቸው። እነርሱም የቤተ ክርስቲያንን ለጋስነት ማትረፊያቸው ያደርጋሉ (ከ1ተሰ 4፥9-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ በትክክለኛው መንገድ ሠርተው ኑሮአቸውን ከሚያሸንፉ ወንድሞችም ርዳታን ይቀበላሉ (ቍ.6-15)። (1) ከእነርሱ በመራቅና ባለመተባበር እንደዚህ ዐይነት ሰዎች መገሠጽ እንደሚያስፈልግ ሐዋርያው ጳውሎስ ያስተምራል (ቍ. 6፥14)፤ (2) በትክክለኛ ችግር ውስጥ ያሉትን መርዳት እንደሚያስፈልግ ሐዋርያው ቢያደፋፍርም፣ ሙሉ አካል ኖሮአቸው ኑሮን ለማሸነፍ መሥራትን ለማይወዱ ሰዎች ግን ምግብ ወይም ገንዘብ መስጠት ይገባል የሚል ትምህርት በየትኛውም ስፍራ ለአማኞች አልሰጠም (ከቍ 10 ጋር ያነጻጽሩ)።*

**3፥12 ተግተው ሥራቸውን እንዲሠሩና እንጀራቸውን እንዲበሉ፤** *ክርስቲያኖች ሥራ ፈት መሆን የለባቸውም፤ ነገር ግን ለራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚያስፈልገውን ያገኙ ዘንድ እንዲሁም የተቸገሩትን ለመርዳት የሚበቃ ነገር ይኖራቸው ዘንድ ትጉ ሠራተኞች መሆን ይገባቸዋል (1ቆሮ 16፥1፤ 2ቆሮ 8፥1-15፤ ኤፌ. 4፥28)።*

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ - አንደኛ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-20)

I. ስለ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የተሰጠ *መመሪያ* (2፥1—4፥5)
- (ሀ) ጸሎት የቱን ያህል እጅግ አስፈላጊ እንደ ሆነ (2፥1-8)
- (ለ) ተገቢ የሆነው የሴቶች ክርስቲያናዊ አካሄድ ጠባይ (2፥9-15)
- (ሐ) ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን የሚያበቁ ሁኔታዎች (*መንቀሳዎች*) (ሽማግሌዎች) (3፥1-7)
  1. በግል ጠባይ ረገድ
     - (ሀ) ነቀፋ የማይገኝበት (3፥2)
     - (ለ) ልከኛ (3፥2)
     - (ሐ) ራሱን የሚገዛ (3፥2)
     - (መ) በሥርዐት የሚኖር (3፥2)
     - (ሠ) እንግዳ ተቀባይ (3፥2)
     - (ረ) ማስተማር የሚችል (3፥2)
     - (ሰ) የማይሰክር (3፥3)
     - (ሸ) የማይጣላ (3፥3)
     - (ቀ) ጨዋ የሆነ (3፥3)
     - (በ) የማይጨቃጨቅ (3፥3)
     - (ተ) ገንዘብን የማይወድ (3፥3)
     - (ቸ) አዲስ አማኝ ያልሆነ (3፥6)
     - (ኀ) በውጭ ባሉት ዘንድ መልካም ምስክርነት ያው (3፥7)
  2. በቤተ ሰብ ረገድ
     - (ሀ) የአንዲት ሚስት ባል (3፥2)
     - (ለ) የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር (3፥4-5)
     - (ሐ) ታዛዥና ሰው አክባሪ ልጆች ያሉት (3፥8-12)
- (መ) ዲያቆን ለመሆን የሚያበቁ መንቀሻዎች (3፥8-12)
  1. በግል ጠባይ ረገድ
     - (ሀ) የተከበረ (3፥8)
     - (ለ) ቃሉን የማይለዋውጥ (3፥8)
     - (ሐ) ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጐመጅ (3፥8)
     - (መ) ያለ አግባብ የሚገኝን ጥቅም የማያሳድድ (3፥8)
  2. በቤተ ሰብ ረገድ
     - (ሀ) የአንዲት ሚስት ባል (3፥12)
     - (ለ) እግዚአብሔርን የምትፈራና በነገር ሁሉ የታመነች ሚስት ያለው (3፥11)
     - (ሐ) ልጆቹንና ቤተ ሰቡን በሚገባ የሚያስተዳድር (3፥12)
     - (ሠ) ቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ስትመርጥ የላቀ መንቀሻ ነጥብ የምትጠይቅበት ምክንያት (3፥13—4፥5)

II. የጢሞቴዎስን አገልግሎት አስመልክቶ የተሰጡ *መመሪያዎች* (4፥6—6፥19)
- (ሀ) ስለ ግል ሕይወቱ (4፥6-16)
- (ለ) በቤተ ክርስቲያን ካሉ
  1. ከሽማግሌዎችና
  2. ከአሮጊትና ከመ
  3. ባል ከሞተባቸው
  4. ከሽማግሌዎችና
  5. ከአገልጋዮች ጋር
  6. ከሐሰት ትምህርት
     በቅንፍ መልክ
  7. ከሀብታሞች ጋር

*መደምደሚያ* (6፥20-21)

**ጸሓፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በ* አስተም

**የተጻፈበት ዘመን፤** *በ65*

*ታሪካዊ ዳራ*

ለአብያተ ክርስቲያናት መደረግ
አንደኛና ሁለተኛ (በኤፌሶን ሳለ
በተለመደው አገላለጽ፣ "መልክታ
ናቸው። ጳውሎስ እነዚህን መልእ
የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ግ
ውስጥ እነዚሁኑ መልእክቶች መድ
በአገላለጽ ስልትና በቃላት አመራ
ያለ ቢሆንም፣ እነዚህ ልዩነቶች በ
የዕድሜ መግፋትና ለጢሞቴዎስና

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አንደኛን
ሁኔታዎች ከሥተት በኋላ ነው።
(ሐሥ 28)፥ በነጻ ተለቀቀና የተ
ከዚህም በኋላ ጳውሎስ የሮሙ ቀ
(ምናልባት በ170 ዓ.ም) ባሰፈሩት
እስፓንያ በመጓዝ ለዘመናት ሲናፍ
ጋር ያነጻጽሩ)። በመልክታተ ም
ባሕር አጠገብ ወዳው አገር (በተለ
ለሆነ አገልግሎት ተመለሰ። በዚህ
ተወካይ በመሆን በኤፌሶን እንዲ
ስ እንዲያከናውን ጳውሎስ ኃላፊነ
የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈለ
ጳውሎስ ዳግም በሮም እስረኛ ሆነ
ጻፈለት፤ ይኸውም ሰማዕትነትን ከ
(2ጢሞ 4፥6-8፤ እንደዚሁም፣ "ወ
ይመልከቱ)።

**ዐላማ**

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አንደኛን ሲጽ
ግል ሕይወቱ ጢሞቴዎስን ራሱን
ላይ ከሚያካሂዱት ጥመት የወንጌ
ጢሞቴዎስን ለማደፋፈር፤ እና (3)
ችግሮችን አስመልክቶ ለጢሞቴዎስ

**ቅኝት**

ጳውሎስ ለወጣት ረዳቱ ለጢሞቴዎ
ጠበቃ እንዲቆም እንዲሁም የወን

(ለ) በቤተ ክርስቲያን ካሉት ሰዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነት (5፥1—6፥19)
1. ከሽማግሌዎችና ለወጣት ወንዶች ጋር (5፥1)
2. ከአሮጊትና ከወጣት ሴቶች ጋር (5፥2)
3. ባል ከሞተባቸው ሴቶች ጋር (5፥3-16)
4. ከሽማግሌዎችና በሽማግሌነት ለማገልገል ተስፋ ካላቸው ጋር (5፥17-25)
5. ከአገልጋዮች ጋር (6፥1-2)
6. ከሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ጋር (6፥3-10)
በቅንፍ መልክ የሰፈረ ሐሳብ፣ ለጢሞቴዎስ በግሉ የተሰጠ ምክር (6፥11-16)
7. ከሀብታሞች ጋር (6፥3-10)

*መደምደሚያ* (6፥20-21)

**ጸሓፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *በነ አስተምህርና እግዚአብሔርን መፍራት*

**የተጻፈበት ዘመን፤** *በ65 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

**ታሪካዊ ዳራ**

ለአብያተ ክርስቲያናት መደረግ ያለበትን እንክብካቤ አስመልክቶ የተላኩት ወደ ጢሞቴዎስ አንደኛና ሁለተኛ (በኤፌሶን ሳለ የተጻፉ) እንዲሁም ቲቶ (በቀርጤስ ሳ የተጻፈ) በተለመደው አገላለጽ፣ "መልክታተ ምጋቤ" የተባሉ ሲሆን፣ በመሠረቱ መልእክቶች ናቸው:: ጳውሎስ እነዚህን መልእክቶች ስለ መጻፉ አንዳንድ ሐያሲያን ጥርጣሬ አላቸው፤ የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ግን ምንጊዜም እውነት ከሆኑት ከጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ እነዚህኑ መልእክቶች መድባቸዋለች:: ከጳውሎስ ሌሎች መልእክቶች ጋር ሲነጻጸሩ፣ በአገላለጽ ስልትና በቃላት አመራረጥ ረገድ፣ በእነዚሁ፣ "መልክታተ ምጋቤ" ላይ ልዩነት ያለ ቢሆንም፣ እነዚህ ልዩነቶች በብቃትና በሚያሳምን ሁኔታ መታየት ያለባቸው ከጳውሎስ የዕድሜ መግፋትና ለጢሞቴዎስና ለቲቶ አገልግሎት ካለው የግል ተቈርቋሪነት አኳያ ነው::

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አንደኛን የጻፈው በሐዋርያት ሥራ መጨረሻ ላይ ከሰፈሩት ሁኔታዎች ከሥተት በኋላ ነው:: ጳውሎስ በሮም ለመጀመሪያ ጊዜ እንዲታሰር የተደረገው (ሐሥ 28)፣ በነጻ ተለቀቀና የተከሰሰበት ጉዳይ በዚህ ተቋጨ (2ጢሞ 4፥16-17):: ከዚህም በኋላ ጳውሎስ የሮሙ ቀለሚንጦስና (ምናልባት በ96 ዓ.ም) የሙራቶሪያን ቀኖና (ምናልባት በ170 ዓ.ም) ባሰፈሩት መሠረት፣ ከሮም ተነሥቶ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ ወደ እስፓንያ በመጓዝ ለዘመናት ሲናፍቀው የነበረውን አገልግሎት ፈጸመ (ከሮሜ 15፥23-24፡28 ጋር ያነጻጽሩ):: በመልክታተ ምጋቤ ላይ በሰፈረው ሐው መሠረት ጳውሎስ ኤሺያን ባሕር አጠገብ ወዳው አገር (በተለይም ወደ ቀርጤስ፣ መሲዶናያና ግሪክ)፣ መጠን ሰፊ ለሆነ አገልግሎት ተመለሰ:: በዚህ ጊዜ (በግምት 64—65 ዓ.ም) ጢሞቴዎስ ሐዋርያዊ ተወካይ በመሆን በኤፌሶን እንዲያገለግል፣ ቲቶም እንደዚሁ ተመሳሳይ ድርጊት በቀርጤስ እንዲያከናውን ጳውሎስ ኀላፊነትን ሰጣቸው:: ጳውሎስ በመቄዶንያ ሳለ ለጢሞቴዎስ የመጀመሪያውን መልእክት ጻፈለት፤ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ለቲቶ ጻፈለት:: ከዚህም በኋላ ጳውሎስ ዳግም በሮም እስረኛ ሆነ፤ በዚሁ ጊዜም ሁለተኛውን መልእክት ለጢሞቴዎስ ጻፈለት፤ ይኸውም ሰማዕትነትን ከመቀበሉ ጥቂት ቀደም ብሎ በ67/68 ዓ.ም ላይ ነው (2ጢሞ 4፥6-8፤ እንደዚሁም፣ "ወደ ጢሞቴዎስ ሁለተኛ" ላይ የቀረበውን መግቢያ ይመልከቱ)::

**ዐላማ**

ጳውሎስ ጢሞቴዎስ አንደኛን ሲጽፍ ሦስት ዐላማዎች ነበሩት፤ (1) ስለ አገልግሎቱና ስለ ግል ሕይወቱ ጢሞቴዎስን ራሱን ለመምከር፤ (2) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በወንጌል ላይ ከሚያከሂዱት ጥመት የወንጌልን ቅዱስነትና ጻድቅ መመዘኛውን ይከላከል ዘንድ ጢሞቴዎስን ለማደፋፈር፤ እና (3) በኤፌሶን ያሉትን ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችንና ችግሮችን አስመልክቶ ለጢሞቴዎስ መመሪያ ለመስጠት ነው::

**ቅኝት**

ጳውሎስ ለወጣት ረዳቱ ለጢሞቴዎስ ካስተላለፋቸው ጉዳዮች አንዱ ጢሞቴዎስ ለእምነት ጠበቃ እንዲቆም እንዲሁም የወንጌልን የማዳን ኀይል በመፈታተን ላይ የነበረውን የሐሰት

ትምህርት ዋጋቢስነት አጉልቶ እንዲያሳይ ነው (1፥3-7፣ 4፥1-8፤ 6፥3-5፡20-21)። ጳውሎስ የቤተ ክርስቲያን መሪ ለመሆን የሚያበቁትን የመንፈሳዊና የጠባይ ብቃት መመዘኛዎችን አስመልክቶ ለጢሞቴዎስ መመሪያ ሰጠው፤ የአብያተ ክርስቲያናት መሪዎች እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ቅዱሳን ምን ዐይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው በመግለጽም አያሌ ነገሮችን ያካተተ ሥዕላዊ መግለጫ ሰጠው (ዝርዝር የብቃት መለኪያው ምን እንደሚመስል ለማስተዋል ቀደም ሲል በአስተዋጽኦ ሥር የሰፈረውን ሐሳብ ይመ)።

ከዚህም ሁሉ ጋር ጢሞቴዎስ የተለያዩ ከሆኑት የቤት ክርስቲያን አባላት ጋር እንዴት መሥራት እንዳለበት ጳውሎስ መመሪያ ሰጠው፤ እነዚህም የቤተ ክርስቲያን አባላት የሚከተሉት ናቸው፤ ሴቶች (2፥9-15፣ 5፥2)፥ መበለቶች (5፥3-16)፣ ጎልማሶችና ወጣት ወንዶች (5፥1)፣ ሽማግሌዎች (5፥17-25)፣ ባሪያዎች (6፥1-2)፣ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች (6፥3-10)፣ እና ባለጠጎች (6፥17-19)። ጢሞቴዎስ ይፈጽማቸው ዘንድ ጳውሎስ አምስት ግልጽ መመሪያዎችን ሰጠው (1፥18-20፤ 3፥14-16፤ 4፥11-16፣ 5፥21-25፤ 6፥20-21)። ጳውሎስ፣ ጢሞቴዎስን ወደ ክርስትና እምነት እንዲመጣ ያስተማረው መምህሩና እንደ ልጅም ተንከባክቦ ያሳደገው አባት እንደ መሆኑ መጠን፣ ለዚሁ ልጁ ጥልቅ ፍቅርን ይገልጻል፤ ለጢሞቴዎስና ለቤተ ክርስቲያንም የላቀ እግዚአብሔርን የመፍራ (የጽድቅ) አካሄድ ምን መሆን እንዳለበት አስፍሮ ይገኛል።

### ልዩ ገጽታ

የአንደኛ ጢሞቴዎስን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት አራት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) ጢሞቴዎስ በኤፌሶን የጳውሎስ ተወካይ እንደ መሆኑ መጠን መልእክቱ እጅግ ግላዊ ሆኖ በጥልቅ ፍቅርና ስሜት በቀጥታ የተጻፈው ለጢሞቴዎስ ነው፤ (2) ይኸው መልእክት ከጢሞቴዎስ ሁለተኛ መልእክት ጋር አንድ ላይ በመሆን የወንጌልን ንጽሕና ለመጠበቅና የማዳን ኀይሉንም ከሚያዳክም የሐሰት ትምህርት ነጻ ለማድረግ ከመጻፉም በላይ፣ ከማንኛውም የአዲስ ኪዳን መልእክት በላቀ ሁኔታ በመጋቢ ኀላፊነት ላይ አጽንዖት ያደርጋል። (3) በወንጌል ልዕልና ላይ፣ ወንጌልን አጣመው ከሚያቀርቡት በስተጀርባ የአጋንንት ተጽዕኖ ያለ መሆኑን በማስገንዘብ ላይ፣ በቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ጥሪ ላይና የቤተ ክርስቲን መሪዎች ማሟላት ስላለባቸው እግዚአብሔር ስለሚጠይቀው ከፍተኛ መንቀሻዎች ላይ አጽንዖት ያደርጋል። (4) ይኸው መልእክት አንድ መጋቢ (ስተር) ከሁለቱ ጾታዎች ጋር፣ ከትንሽና ከትልቁ ጋር እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙት ከማንኛቸውም ማኅበራዊ ቡድኖች ጋር እንዴት መሥራትና መተባበር እንዳለበት ቊልጭ ያለ ዝርዝር መመሪያን ይሰጣል።

### ወደ ጢሞቴዎስ አንደኛን ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ ወደ ጢሞቴዎስ አንደኛን ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በ6 ቀናት መነበብ ይኖርበታል፤

❑ 1 ❑ 2 ❑ 3 ❑ 4 ❑ 5 ❑ 6

*ማስታወሻ*

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

______ ______ ______ ______ ______

1 በአዳኛችን በእግዚአብሔር፣ ተስ
በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ
የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ
ከጳውሎስ፤
2 በእምነት እውነተኛ ልጄ
ለጢሞቴዎስ፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌ
ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ምሕረት፣
ይሁን።

**ከሐሰተኛ የሕግ መምህራን ስለ**
**በቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ**

3 ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊ
እንዳልሁህ፣ አንዳንድ ሰዎች ከእ
የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ
ዘንድ በዚያው በኤፌሶን ተቀመጥ፤
ለተረትና መጨረሻ ለሌለው የት
ታሪክ ራሳቸውን አሳልፈው እን
እዘዛቸው። እነዚህ ነገሮች
ከሆነው ከእግዚአብሔር ሥራ ይልቅ
ያነሣሣሉ። 5 የዚህ ትእዛዝ ዐላማ ግን
ልብ፣ ከበጎ ኅሊና እንዲሁም ከእ
እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው። 6 አን
ከእነዚህ ነገሮች ዘወር ብለው ወ
ንግግር ተመልሰዋል። 7 የሕግ
ለመሆን ይፈልጋሉ፤ ሆኖም ስለ
ወይም አስረግጠው ስለሚናገሩለ
አያውቁም።
8 ነገር ግን ሰው በአግባቡ ከተጠ
ሕግ መልካም መሆኑን እና
9 ደግሞም ሕግ የተሰጠው ለጻድቃን
ለሕግ ተላላፊዎችና ለዐመፀኞች

**1፥3 የሐሰት ትምህርት እን**
ሰት ትምህርት አስተማሪዎች የክ
መልእክት ለማጣመም ጥረት እንደ
ይህን መልእክት ከመጻፉ ስብት ዓ
የኤፌሶንን ሽማግሌዎች አስጠንቅቆ
እና ማብ ይመ)። አሁን ይደርሳል
ነገር በመከሠት ላይ ነው፤ እነዚህ
ይቋቋማቸው ዘንድ ጳውሎስ ጢሞ
ይህ ወጣት መጋቢ ሕግንና ወንጌል
ከሚገኘው፣ ከሐሰት ትምህርት ጋር ተ
እንዳይኖር መጠንቀቅ ይኖርበታል፤
ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት ያስተ
እምነት በማወጅ (2ጢሞ 1፥13-14)፣
የሆነ የእምነት ጦርነት ማካሄድ አለበ
**1፥5 የዚህ ትእዛዝ ዐላማ፤** ክ
የሆነው ትምህርት ሁሉ ከፍተኛ
ለሰውቀትነቱ ሲባል የሚካሄድ የመ
ሳይሆን፣ በፍቅር፣ በልብ ንጽሕና፣
ፈሪሳዊነት በሌለበት እምነት የሚ
ይህም ግብረገባዊ ተሓድሶ ነው (ሐ
ኅሊና ላይ የቀረበውን ማብራሪ፣ እንዲ
ላይ፣ "*የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱ*
ርእስ የቀረበውን ማ ይመ)፤ ይህን
ሁለት ዐበይት ሐቆች ልብ
(1) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው
መሠረታዊ ዕንስ ሐሳብ ተቀዳሚ
ማካፈል ወይም ራስን ከሊቅነት

1 በአዳኛችን በእግዚአብሔር፣ ተስፋችንም በሆነው በክርስቶስ ኢየሱስ ትእዛዝ የክርስቶስ ኢየሱስ ሐዋርያ ከሆነው ከጳውሎስ፤

2 በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነው ለጢሞቴዎስ፤

ከእግዚአብሔር ከአባታችን፣ ከጌታችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ምሕረት፣ ሰላምም ይሁን።

## ከሐሰተኛ የሕግ መምህራን ስለ መጠበቅ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ

3 ወደ መቄዶንያ በሄድሁ ጊዜ በዚያ እንዳልሁህ፣ አንዳንድ ሰዎች ከእንግዲህ የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ ታዛቸው ዘንድ በዚያው በኤፌሶን ተቀመጥ፤ 4 ደግሞም ለተረትና መጨረሻ ለሌለው የትውልዶች ታሪክ ራሳቸውን አሳልፈው እንዳይሰጡ እዘዛቸው። እነዚህ ነገሮች በእምነት ከሆነው ከእግዚአብሔር ሥራ ይልቅ ክርክርን ያነሣሣሉ። 5 የዚህ ትእዛዝ ዐላማ ግን ከንጹሕ ልብ፣ ከበጎ ኅሊና እንዲሁም ከእውነተኛ እምነት የሚገኝ ፍቅር ነው። 6 አንዳንዶች ከእነዚህ ነገሮች ዘወር ብለው ወደ ከንቱ ንግግር ተመልሰዋል። 7 የሕግ መምህራን ለመሆን ይፈልጋሉ፤ ሆኖም ስለሚናገሩት ወይም አስረግጠው ስለሚናገሩለት ነገር አያውቁም።

8 ነገር ግን ሰው በአግባቡ ከተጠቀመበት፣ ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን። 9 ደግሞም ሕግ[a] የተሰጠው ለጻድቃን ሳይሆን፣ ለሕግ ተላላፊዎችና ለዐመፀኞች፣ ፈሪሃ እግዚአብሔር ለሌላቸውና ለኀጢአተኞች፣ ቅድስና ለሌላቸውና እግዚአብሔርን ለሚንቁ፣ አባትና እናታቸውን ለሚገድሉ፣ ለነፍሰ ገዳዮች መሆኑን እናውቃለን፤ 10 እንዲሁም ለዘማውያን፣ ከወንድ ጋር ለሚተኙ ወንዶች፣ ሰውን ለሚሸጡና ለሚገዙ፣ ለውሸተኞች፣ በሐሰት ለሚምሉ፣ ጤናማ የሆነውን ትምህርት ለሚጻረሩ ሁሉ ነው፤ 11 ይህ ጤናማ ትምህርት ቡሩክ እግዚአብሔር ለእኔ በዐደራ ከሰጠኝ የክብር ወንጌል ጋር የሚስማማ ነው።

## ለጳውሎስ የተሰጠው የጌታ ጸጋ

12 በአገልግሎቱ በመሾም ታማኝ አድርጎ የቈጠረኝን፣ ብርታት የሰጠኝን ጌታችንን ክርስቶስ ኢየሱስን አመሰግናለሁ። 13 ምንም እንኳ ከዚህ በፊት ተሳዳቢ፣ አሳዳጅና ዐመፀኛ የነበርሁ ብሆንም፣ ባለማወቅና ባለማመን ስላደረግሁት ምሕረት ተደርጎልኛል፤ 14 በክርስቶስ ኢየሱስ ከሆኑት እምነትና ፍቅር ጋርም የጌታችን ጸጋ ተትረፈረፈልኝ።

15 [b]ክርስቶስ ኢየሱስ ኀጢአተኞችን ለማዳን ወደ ዓለም መጣ' የሚለው ቃል እውነተኛና ሰው ሁሉ ሊቀበለው የሚገባ ነው፤ ከኀጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ። 16 ነገር ግን ክርስቶስ ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑና

1፥1 ሉቃ1፥47፤ 2ቆሮ1፥1፤ ቈላ1፥27፤ ቲቶ1፥3
1፥2 ቍ18፤ ሐሥ16፥1፤ ሮሜ1፥7፤ 1ቆሮ4፥17፤ 1ተሰ2፥11፤ 2ጢሞ1፥2፤ ቲቶ1፥4
1፥3 ሐሥ16፥9፤ 18፥19፤ ገላ1፥6፡7፤ 1ጢሞ6፥3
1፥4 1ጢሞ4፥7፤ 2ጢሞ2፥14፤ 4፥4፤ ቲቶ1፥14፤ 3፥9
1፥5 ሐሥ23፥1፤ ገላ5፥6፤ 1ጢሞ4፥2፤ 2ጢሞ1፥5፤ 2፥22
1፥7 ኢዮ38፥2፤ ኤፌ4፥11
1፥8 ሮሜ7፥12
1፥9 ገላ3፥19፤ 5፥23
1፥10 1ጢሞ6፥3፤ 2ጢሞ1፥13፤ 4፥3፤ ቲቶ1፥9፤ 2፥1
1፥11 ገላ2፥7፤ 1ተሰ2፥4፤ ቲቶ1፥3
1፥12 ሐሥ9፥15፤ ፊል4፥13
1፥13 ቍ16፤ ሐሥ8፥3፤ 26፥9
1፥14 2ቆሮ4፥15፤ 1ተሰ1፥3፤ 2ጢሞ1፥13
1፥15 ማር2፥17፤ ዮሐ3፥17፤ 1ጢሞ3፥1፤ 4፥9፤ 2ጢሞ2፥11፤ ቲቶ3፥8
1፥16 ቍ13፤ ማቴ25፥46፤ ዮሐ3፥15፤ ሮሜ2፥4

[a] 1፥9 ወይም ሕጉ
[b] ወይም ተመልካች ለባቂዎች

**1፥3 የሐሰት ትምህርት እንዳያስተምሩ፤** የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች የክርስቶስን ትክክለኛ መልእክት ለማጣመም ጥረት እንደሚያደርጉ፣ ጳውሎስ ይህን መልእክት ከመጻፉ ሰባት ዓመት ቀደም ብሎ የኤፌሶንን ሽማግሌዎች አስጠንቅቆአል (ሐሥ 20፥29 እና ማብ ይመ)። አሁን ይደርሳል ተብሎ የተሠጋበት ነገር በመከሠት ላይ ነው፤ እነዚህ ቡድኖች በድፍረት ይቃቋሟቸው ዘንድ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን መከረው። ይህ ወጣት መጋቢ ሕግንና ወንጌልን በመበረዝ ላይ ከሚገኘው፣ ከሐሰት ትምህርት ጋር ተስማምቶ (ተቻችሎ) እንዳይኖር መጠንቀቅ ይኖርበታል፤ ይልቁንስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ሐዋርያት ያስተማሩትን እውነተኛ እምነት በማወጅ (2ጢሞ 1፥13-14)፣ በታማኝነት ወሳኝ የሆነ የእምነት ጦርነት ማካሄድ አለበት።

**1፥5 የዚህ ትእዛዝ ዐላማ፤** ከእግዚአብሔር ቃል የሆነው ትምህርት ሁሉ ከፍተኛ ዐላማ ዕውቀት ለዕውቀትነቱ ሲባል የሚከሄድ የመጽሐፍ ቅዱስ ፍለጋ ሳይሆን፣ በፍቅር፣ በልብ ንጽሕና፣ በንጹሕ ኅሊናና ፈሪሳዊነት በሌለበት እምነት የሚገለጽ ፍለጋ ሲሆን፣ ይህም ግብረገባዊ ተሐድሶ ነው (ሐሥ 24፥16 እና በበጎ ኅሊና ላይ የቀረበውን ማብራሪያ፣ እንዲሁም፣ በገጽ 1937 ላይ፣ "*የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና*" በሚል ርእስ የቀረበውን ማ ይመ)፤ ይህን እውነት አስመልክቶ ሁለት ዐበይት ሐቆች ልብ መባል አለባቸው፤ (1) መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው የመማር ማስተማር መሠረታዊ ዕንስ ሐሳብ ተቀዳሚ ተልእኮው ዕውቀትን ማካፈል ወይም ራስን ከሊቅነት ደረጃ ለማድረስ ጥረት ማድረግ አይደለም፤ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል ቅድስናንና ጻድቅ የሕይወት ዘይቤን እውን ማድረግ ነው እንጂ (ከ2ጢሞ 1፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። (2) የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምር ሰው ሕይወቱ ጽናትን፣ እውነትን፣ እምነትንና ቅዱስነትን የሚያሳይ መሆን አለበት (3፥1-13)።

**1፥8 ሕጉ መልካም መሆኑን፤** ማቴ 5፥17 እና፣ "ሕግና ክርስቲያን" በሚል ርእስ የቀረበውን ማብራሪያ ይመልከቱ፤ ከሮሜ 7፥12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 144 ላይ፣ "*የብሉይ ኪዳን ሕግ*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥13 ተሳዳቢ፣ አሳዳጅና፤** ክርስቲያን ከመሆኑ በፊት ጳውሎስ አማኞችን የሚያሳድድ አደገኛ ሰው ነበር (ከሐሥ 8፥3፡9፥1-2፡4-5፡22፥4-5፡26፥9-11፤ከገላ 1፥13 ጋር ያነጻጽሩ)። በእግዚአብሔር ሕዝብ የፈጸመው አሠቃቂ በደል ራሱን የኀጢአተኞች ኀጢአተኛ ብሎ ለመመደብ በቂ ምክንያት ነበር (ቍ 14-15 ይመ፤ ከ1ቆሮ 15፥9፤ ከኤፌ 3፥8 ጋር ያነጻጽሩ)። ይሁን እንጂ፣ ያን ጊዜ እንኳ እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል ባሪያ ሆኖ ስለ ተሰማው (ሐሥ 23፥1፤ 26፥9)፣ ምሕረት እንዲሁም ታላቅ መታገሥ ተደረገለት፤ ንስሐ እንዲገባና ኢየሱስ ክርስቶስን ጌታ አድርጎ እንዲቀበልም ዕድል ተሰጠው (ሐሥ 9፥1-9)። እግዚአብሔር ለጳውሎስ ያደረገለት ምሕረት፣ የእግዚአብሔር ኀይልና ጸጋ የኀጢአተኞችን ሕይወት መለወጥ እንደሚችል በማመን፣ በልበ ሙሉነት ወንጌልን ለእነርሱ እንድናቀርብ ሊያደፋፍረን ይገባል።

የዘላለምን ሕይወት ለሚቀበሉ ወሰን የሌለው
ትዕግሥቱን ከኀጢአተኞች ዋና በሆንሁት
1ጢሞ በእኔ እንደ ምሳሌ አድርጎ ያሳይ ዘንድ
2፥3-6 ምሕረትን አገኘሁ። [17]እንግዲህ ዘላለማዊ
ለሆነው፣ ለማይሞተው፣ ለማይታየውና
ብቻውን አምላክ ለሆነው ንጉሥ ከዘላለም
እስከ ዘላለም ክብርና ምስጋና ይሁን፤
አሜን።

[18]ልጄ ጢሞቴዎስ ሆይ፤ አስቀድሞ ስለ
አንተ በተነገረው ትንቢት መሠረት ይህን
ትእዛዝ እሰጥሃለሁ፤ ይኸውም እርሱን በመ
ከተል መልካሙን ገድል እንድትጋደል
ነው። [19]እምነትና በጎ ኅሊናም ይኑርህ፤
አንዳንዶች ኅሊናቸውን ጥለው ባሕር ላይ
አደጋ ደርሶበት እንደሚጠፋ መርከብ
እምነታቸውን አጥፍተዋል። [20]ከእነርሱም
መካከል እንዳይሳደቡ ትምህርት ያገኙ
ዘንድ ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው፣
ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ይገኙሉ።

## አምልኮን በሚመለከት የተሰጠ መመሪያ

**2** እንግዲህ ከሁሉ አስቀድሞ ልመናና
ጸሎት፣ ምልጃና ምስጋና ለሰዎች
ሁሉ፣ ለንጉሥታትና ለባለ ሥልጣናት
ሁሉ እንዲ ደረግ ኣሳስባለሁ፤ [2]ይህም
በእውነተኛ መን ፈሳዊ ሕይወትና በቅድስና
ሁሉ፣ በሰላምና በጸጥታ እንድንኖር
ነው። [3]ይህ •በእግዚአብሔር በአዳኛችን
ፊት ደስ የሚያሰኝ ነው፤ [4]እርሱ ሰዎች
ሁሉ እንዲድኑና እውነትን ወደ ማወቅ
እንዲደርሱ ይፈልጋል። [5]አንድ እግዚአብሔር
አለና፤ ደግሞም በእግዚአብሔርና በሰዎች
መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም
ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤
[6]ራሱንም ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ፤
ይህም በትክክለኛው ጊዜ ተመስክሮለታል። 2ጢሞ 3፥15
[7]እኔም ለዚህ ነገር የምሥራች አብሣሪና
ሐዋርያ እንዲሁም ለአሕዛብ የእውነተኛ
እምነት አስተማሪ ሆኜ ተሾምሁ፤ እውነቱን
እናገራለሁ፤ አልዋሽም።

[8]እንግዲህ ወንዶች በሁሉም ቦታ
ያለቍጣና ያለ ክርክር የተቀደሱ
እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት እንዲጸልዩ
እፈልጋለሁ።

[9]እንዲሁም ሴቶች በጨዋንትና ራስን

1፥17 ሮሜ11፥36፤ ቈላ1፥15፤ 1ጢሞ6፥16፤ ይሁ1፥25፤ ራእ15፥3
1፥18 ቍ2፤ 1ጢሞ4፥14፤ 6፥12፤ 2ጢሞ2፥3፤ 4፥7
1፥19 ቍ5፤ ሐሥ23፥1፤ 1ጢሞ6፥21፤ 2ጢሞ2፥18
1፥20 1ቆሮ5፥5፤ 2ጢሞ2፥17፤ 2ጢሞ4፥14
2፥1 ኤፌ6፥18
2፥2 ዕዝ6፥10፤ ሮሜ13፥1፤ 1ጢሞ3፥16፤ 4፥7፡8፤ 6፥3፡5፡6፡11፤ 2ጢሞ3፥5፤ ቲቶ1፥1
2፥3 ሉቃ1፥47፤ 1ጢሞ5፥4
2፥4 ሕዝ18፥23፡32፤ 33፥11፤ ዮሐ3፥17፤ ሮሜ11፥14፤ 1ጢሞ4፥10፤ 2ጢሞ2፥25 ቲቶ1፥1፤ 3፥11፤ ዕብ10፥26፤ 2ጴጥ3፥9
2፥5፤ ዘዳ6፥4፤ ሮሜ1፥3፤ 3፥29-30፤ 10፥12፤ ገላ3፥20
2፥6 ማቴ20፥28፤ 1ቆሮ1፥6፤ 1ጢሞ6፥15፤ ቲቶ1፥3
2፥7 ሐሥ9፥15፤ ሮሜ9፥1፤ 2ጢሞ1፥11
2፥8 መዝ24፥4፤ 63፥4፤ 134፥2፤ 141፥2፤ ሉቃ24፥50
2፥9 1ጴጥ3፥3

1፥18 **አስቀድሞ ... በተነገረው ትንቢት መሠረት**፤ በቤተ ክርስቲያን ስለ ጢሞቴዎስ አገልግሎት፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምን እንደ ሆነ በተመለከተ ትንቢት ተነግሮ ነበር፤ ይኸውም ጢሞቴዎስ በትንቢት የጸጋ ስጦታን ያገኘው ሽማግሌዎች በእርሱ ላይ እጃቸውን ለጫኑ ጊዜ ነው (1ጢሞ 4፥14፤ በገጽ 1800 ላይ፣ *"ለአማኞች የሚሰጡ መንፈሳዊ ስጦታዎች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ጢሞቴዎስ ስለ ሕይወቱ ለተገለጠው ፈቃድ ታማኝ ሆኖ እንዲጸና ጳውሎስ ይመክረዋል። የቤተ ክርስቲያን መጋቢና ሽማግሌ እንደ መሆኑ መጠን ለሐዋርያዊ እምነት ታማኝ ሆኖ በመጽናት ወደ ቤተ ክርስቲያን እያዘገመ በመምጣት ላይ የሚገኘውን የሐሰት አስተምህሮ መዋጋት ይኖርበታል።

1፥19 **ባሕር ላይ አደጋ ደርሶበት እንደሚጠፋ መርከብ እምነታቸውን አጥፍተዋል**፤ ጳውሎስ አስከፊ የሆነ አጋጣሚ ማለትም ተጠንቅቆ በማይኖር ሰው ዘንድ ክሕደት ሊደርስ እንደሚችል ብዙ ጊዜ ጢሞቴዎስን አስጠንቅቆታል (4፥1፤ 5፥11-15፤ 6፥9-10፤ በገጽ 1962 ላይ፤ *"ክሕደት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

1፥20 **ለሰይጣን አሳልፌ የሰጠኋቸው**፤ ከዚህ ላይ የጳውሎስ ውሳኔ (የወሰደው እርምጃ) እነዚህ ሁለት ሰዎች ከቤተ ክርስቲያን መወገዳቸውን ሊያመለክት ይችላል። በጸጋው ያገኘነው ድነትና ከክርስቶስ አካል ከቤተ ክርስቲያን ጋር የምናደርገው ኅብረት፣ የሰይጣን ኀይል ሊያደርስብን ከሚችል ጥቃት ይከላከልልናል (ኢዮ 2፥6-7፤ 1ቆሮ 5፥5፤ ራእ 2፥22 ይመ)። በአንጻሩ ግን አንድ አማኝ ከቤ ተ ክርስቲያን እንዲወገድ ሲሆን፣ የዚያ ሰው ሕይወት ለጥፋትና ለሰይጣን ኀይል ይዳረጋል (ከኢዮ 2፥6፤ ከ1ቆሮ 5፥5፤ ከራእ 2፥22 ጋር ያነጻጽሩ)። የቤተ ክርስቲያን ሥነሥርዐት አንድን አማኝ ወደ ንስሓ፣ እውነተኛ እምነትና በክርስቶስ እውን ወደ ሆነው ድነት ያመጣዋል (1ቆሮ 5፥5 እና ማብ ይመ)።

2፥4 **እርሱም ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና**፤ መጽሐፍ ቅዱስ ድነትን አስመልክቶ ለሰው ዘር ያለውን ሁለት የእግዚአብሔር ፈቃድ ገጽታዎች ያሳያል፤ ይኸውም ሁሉም ሰው ይድን ዘንድ የሚፈልገውን ፍጹም ፈቃድና ከጠቀመህ እንዳሻህ ተጓዝ የሚለው የይሁንታ ፈቃድ ናቸው፤ እንግዲህ ብዙዎች ወደ ክርስቶስ ለመምጣትና ድነትን ለመቀበል እምቢተኞች ሆነው መቅረትን ሲመርጡ እግዚብሔ እንደምርጫቸው እንዲጓዙ ይፈቅድላቸዋል ማለት ነው (ማቴ 7፥21፤ ሉቃ 7፥30፤ 13፥34፤ ዮሐ 7፥17፤ ሐሥ 7፥51 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1075 ላይ፣ *"የእግዚአብሔር ፈቃድ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

2፥5 **አንድ አስታራቂ ... ክርስቶስ ኢየሱስ**፤ የመሥዋዕት ሞቱ ኀጢአታችንን እንደሚሸፍን በመተማመን ለሚያስፈልገን ሁሉ ብርታትንና ምሕረትን እንድናገኝ በእምነት በመጸለይ (4፥14-16)፣ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ያለብን በክርስቶስ ኢየሱስ ብቻ ነው (ዕብ 7፥15)። የትኛውም ዐይነት ፍጡር የክርስቶስን የማስታረቅ ሥራ ሊፈጽም ይችላል በማለት መታለል የለብንም (ዕብ 8፥6፤ 9፥15፤ 12፥24 ይመ)።

2፥6 **ለሰዎች ሁሉ ቤዛ አድርጎ ሰጠ**፤ ማቴ 20፥28 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

2፥8 **በሁሉም ቦታ ... የተቀደሱ እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት**፤ የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን በተጀመረችበት ዘመን በማኅበር በማምለክ ላይ የነበሩት አማኞች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው መጸለያቸው የተለመደ ነበር (ሐሥ 4፥24-31 ይመ፤ ከዕዝ 3፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ)። ጸሎት ተቀባይነትን ያገኝ ዘንድ በጽድቅ መንገድ በሚመላለሱና ጻድቅ ሕይወት ባላቸው ቅዱሳን ይኸውም "የተቀደሰ እጆቻቸውን ወደ ላይ በማንሣት" ለመጸለይ በሚችሉ ወገኖች መቅረብ ነበረበት።

2፥9 **ሴቶች በጨዋንትና ... ተገቢ የሆነ ልብስ ይልበሱ**፤ ክርስቲያን ሴቶች ጥንቃቄ ያለበትና ተገቢ

በመ ግባት ተገቢ የሆነ ልብስ ይልበሱ እንጂ በሹሩባ ወይም በዕንቊ ወይም ዋጋቸው ውድ በሆነ ልብሶች አይሸቀርቀሩ፤ [10]ነገር ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን የሚሉ ሴቶች ሊያደርጉት እንደሚገባ በመልካም ተግባር ይዋቡ።

[11]ሴት በጸጥታና በሙሉ መገዛት ትማር። [12]ሴት ዝም እንድትል እንጂ እንድታስተምር ወይም በወንድ ላይ ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም። [13]ምክንያቱም አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአል፤ ከዚያም ሔዋን ተፈጠረች። [14]ደግሞም የተታለለው አዳም አይደለም፤ የተታለለችውና ኀጢአተኛ የሆነችው ሴቷ ናት፤ [15]ይሁን እንጂ ሴት[a] በእምነትና በፍቅር፣ በቅድስናም ራሷን እየገዛች ብትጸና ልጅ በመውለድ ትድናለች[b]።

## እረኞችና ዲያቆናት

3 [1]"ማንም ኤጲስቆጶስነትን* ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል" የሚለው ቃል የታመነ ነው። [2]እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት

2፥10 ምሳ31፥13
2፥11 1ጴጥ3፥3-4
2፥12 ኤፌ5፥22
2፥13 ዘፍ2፥7፡22፤ 1ቆሮ11፥8
2፥14 ዘፍ3፥1-6፡13፤ 2ቆሮ11፥3
2፥15 1ጢሞ1፥14
3፥1 ሐሥ20፥28፤ ፊል1፥1፤ 1ጢሞ1፥15፤ ቲቶ1፥7
3፥2 ቍ11፡12፤ ሮሜ12፥13፤ 2ጢሞ2፥24፤ ቲቶ1፥6-8፤ 2፥2

[a] 2፥15 ግሪኩ እርሷ ይላል
[b] 2፥15 ወይም ትታደሳለች

---

የሆነ ልብስ እንዲለብሱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው፤ (1) "በጨዋነት" የሚለው ሐረግ (በግሪክ፡ "ኤደስ") ማገለጥ የሌለበት የሰውነት ክፍል እንዲጋለጥ ማድረግ አሳፋሪ መሆኑን ያመለክታል። ይኸውም ሰዎችን ለማማለል ሲባል ሰውነትን ማጋለጥ ተገቢ አለመሆኑን፣ በልብስ መከለል ያለበትን የሰውነት ክፍልም ነውርን ንቆ ማጋለጥ ትክክል አለመሆኑን ያሳያል። የአንድ ሰው የጨዋነት ምንጩ የልቡ ሁኔታ ወይም ውስጣዊ ባሕርይ ነው። በሌላም አገላለጽ ጨዋነት የውስጣዊ ንጽሕና የይፋ መግለጫ ነው።

(2) በሌሎች ላይ አጉል ምኞት በሚያሳድር ሁኔታ ተገቢ ባልሆነ አለባበስ መታየት፣ ሊያነሣሣ የሚችለውን ያህል ኢግብረገባዊ ምኞት አስጸያፊ ነው። በሌሎች ላይ የወሲብ (የሥጋ) ፍላጎት ለማነሣሣት ሲባል የሚለበስ ተገቢ ያልሆነ ልብስ ምንም ዐይነት ክንዋኔ ወይም ይበጅ (ይበል) ሊያሰኘው አይችልም (ከገላ 5፥13፤ ከኤፌ 4፥27፤ ከቲቶ 2፥11-12 ጋር ያነጻጽሩ፤ ማቴ 5፥28 እና ማብ ይመ)።

(3) መጽሐፍ ቅዱስ የፈቀደው ተገቢ የሆነ አለባበስ ተንቆ፣ የዓለም አለባበስ በክርስቲያኖች ዘንድ በቀስታ እንዲሁ ባህል ሲደረግ፣ ይህንኑ አስመልክቶ በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚሰነዘረው አስተያየት አሳዛኝ ነው። ልቅ የግብረ ሥጋ ግንኙነት በነገሠበት ዘመን፣ ቤተ ክርስቲያን ለጨዋነት፣ ለንጽሕናና ፈሪሀ እግዚአብሔር ላለበት መታቀብ መንፈስ ቅዱስ ያውን ፈቃድ ወደ ጐን በሚልና በሚያጣጥል ኅብረተሰብ ላይ እርምጃ መውሰድ ይኖርባታል፤ ከዓለም አለባበስ በተለየ መልክም መልበስ ይኖርባታል (ከሮሜ 12፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥9 በሹሩባ ወይም በዕንቊ፤** ይህ ምናልባት ጸጉርን በወርቅ ወይም ውድ በሆነ ጌጥ ሹሩባ መሠራት ሊሆን ይችላል።

**2፥13 አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአል፤** ወንድ በቤት ውስጥና በቤተ ክርስቲያን የበላይና መንፈሳዊ መሪ መሆን ያለበት ለምን የቶኑ እንደ ሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ የመከራከሪያ ሐሳብ ያቀረበበት ሁለት መሠረት አለው (ኤፌ 5፥23 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1894 ላይ፣ "*ወላጆችና ልጆች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ (1) እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ባለው ዐላማ ላይ ተየመሠረተ ነው፤ እግዚአብሔር ወንድን አስቀድሞ ፈጠረ፤ ይኸውም ወንድ ለሴቷና ለቤተ ሰብ አቅጣጫና አመራር እንዲሰጥ መደረጉ የእግዚአብሔር ዐላማ መሆኑን ይገልጻል (ዘፍ 2፥18፤ 1ቆሮ 11፥8-9፤ 14፥34)፤ (2) ሴቷና ወንዱ በዔደን ገነት እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕግ በተላለፉ ጊዜ በተፈጠረው አሳዛኝ ሁኔታም ላይ የተመሠረተ ነው። ሔዋን የበላይዋ ከሆነው ከባሏ ተለይታ ለብቻዋ መወሰን ሳይገባት ብቻዋን በመወሰን የተከለከለውን ፍሬ በላች። አዳም በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር የተሰጠውን ኀላፊነት ችላ በማለት ከሔዋን አለመታዘዝ ጋር ተባበረ። ከዚ የተነሣ እርሱም ወደቀ፤ በሰውም ዘር ላይ ኀጢአትንና ሞትን አመጣ (ቍ 14፤ ዘፍ 3፥6፡12፤ ሮሜ 5፥12)።

**2፥15 ሴት ... ልጅ በመውለድ ትድናለች፤** ሴት የተባች ሁሉ በእግዚአብሔር በማመንና እግዚአብሔር በሰጣት የሥራ ኀላፊነት በመሰማራት እንደምትድን ጳውሎስ ይናገራል፤ (1) የሴት እጅግ ከፍተኛ የሆነው ኀላፊነትና እውነተኛ ክብሯ በቤት ውስጥ ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላት ሚስትና እናት ሆና ስትገኝ ነው። አንዲት ሴት የላቀ ደስታ፣ ውስጣዊ ሐሤት፣ በረከት ወይም ክብር የምታገኘው በሌላ ሳይሆን ክርስቲያን ሚስትና እናት በመሆን ልጆች ስትወልድ (5፥14)፤ በፍቅር ስንትከባከባቸው (ቲቶ 2፥4)፣ ለእግዚአብሔር ክብር ክርስቶስን እንዲመስሉ አድርጋ ስታሳድጋቸውና ለአዳኟ ምንጊዜም ታማኝ ሆና ስትኖር ነው (ከ2ጢሞ 1፥5፤ 3፥14-15 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1894 ላይ፣ "*ወላጆችና ልጆች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ልጅ የመውለድ ክብርና ሞገስ በክርስቲያን ዘንድ እንደ ተራ ነገር ሆኖ መቈጠር የለበትም፤ ለዓለም ድነት ምክንያት በመሆን፣ ልጅ ያረገዘችው ማርያም ነበረች (ዘፍ 3፥15፤ ማቴ 1፥18-25)።

(3) እግዚአብሔር ለሴት በቸርነቱ የሰጠውን ዐላማ ለድርድር የሚያቀርቡ ወይም የሚንቁ ብሎም የክርስቲያናዊ ቤተ ሰብን፣ የቤትና የእናትነትን ሚና ችላ የሚሉ (የሚዋርዱ) ኅብረተሰቦች፣ ባህሎችና አብያተ ክርስቲያናት ቢገኙቻቸው፣ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰባቸው ላይ ውድቀትን ይቀምሳሉ (2ጢሞ 3፥3 እና ማብ ይመ)።

(4) ጳውሎስ ስለ ክርስቲያን ሴቶች ሲጽፍ ያላገቡ ሴቶችን ወይም ልጅ መውለድ የማይችሉትን ሴቶች ለማዋረድ ብሎ አይደለም። የእንደነዚህ ዐይነት ሴቶች እምነት፣ ፍቅርና ቅድስና ቤተ ሰብ ያላቸውን ሴቶች ያህል የላቀ ሊሆን ይችላል (1ቆሮ 7፥34 እና ማብ ይመ)።

**3፥1 ማንም የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጳስ ለመሆን ቢፈልግ፤** ኤጲስ ቆጳስ ወይም መጋቢ ለመሆን ዋና ዋናዎቹ የብቃት መለኪያዎች ምን እንደ ሆኑ ለመረዳት፣ በገጽ 1925 ላይ፣ "*የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**3፥2 የማይነቀፍ፤** ኤጲስ ቆጳስ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ነቀፋ የማይቀርብበት ሰው መሆን አለበት (በግሪክ፤ "አኔጲለምፕቶስ" ማለት ሲሆን፣ ቃል በቃል ሲተረጐም በደል የሌለበት ማት ነው)። ይህም በገኸድ የሚታይ

ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት
የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር
የሚችል፣ [3]የማይሰክር፣ የማይጣላ ግን ጨዋ
የሆነ፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገንዘብንም የማይ
ወድ ሊሆን ይገባዋል። [4]ልጆቹን ታዛዥና
አክባሪ አድርጎ በማሳደግ የገዛ ቤቱ ሰቡን
በአግባቡ የሚያስተዳድር ሊሆን ይገባል።
[5]አንድ ሰው የራሱን ቤት ማስተዳደር
ካላወቀበት፣ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን
እንዴት ሊጠብቅ ይችላል? [6]በትዕቢት ተነፍቶ
ዲያብሎስ በወደቀበት ፍርድ እንዳይወድቅ
አዲስ ክርስቲያን አይሁን። [7]ደግሞም
ሰው እንዳይነቀፍና በዲያብሎስ ወጥመድ
ውስጥ እንዳይወድቅ፣ በውጭ ባሉት ዘንድ
መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል።
[8]ዲያቆናትም እንደዚሁ የተከበሩ፣

3፥3 ሉቃ16፥14፤ 1ጢሞ6፥10፤ 2ጢሞ2፥24፤ 3፥2፤ ቲቶ1፥7፤ ዕብ13፥5፤ 1ጴጥ5፥2 3፥4 ቍ12፤ ቲቶ1፥6 3፥5 1ቆሮ10፥32 3፥6 1ጢሞ6፥4፤

3፥6 2ጢሞ3፥4፤ 2ጴጥ2፥4 3፥7 ማር4፥11፤ 2ጢሞ2፥26 3፥8 ፊል1፥1፤ 1ጢሞ5፥23፤ ቲቶ1፥7፤ 2፥3

ጠባይ ማለት ነው፡ ይኸውም በጋብቻ ሕይወቱ፣ በቤተ ሰብ፣ በማኅበራዊና በሥራ ሕይወቱ ነውር የማይቀርብበት ማለት ነው። ማንም ኤጲስ ቆጶስ በማስረጃ የተረጋገጠ ኢግብረገባዊነት ወይም ግድፈት ሊታይበት ወይም ሊቀርብበት አይገባም። ይልቁንስ በቤተ ክርስቲያንም ሆነ ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ነቀፋ የሌለበት ዝና እንዲኖረው ያስፈልጋል (ቍ 7 እና ማብ ይመ)፤ ምክንያቱም ክርስቲያናዊ ሕይወቱን እንደ ልማድ በሆነ ወይም በአጋጣሚ በተፈጸመ ዘማናኝ ኀጢአት ወይም ኢግብረገባዊነት አልበከለምና። ስለዚህ እርሱ ማንም አማኝ ሊከተለው የሚገባን ምሳሌ ማሳየት ይችላል።

**3፥3 የማይሰክር፤** ይህ ሐረግ በቃል ሲተረጎም፣ “ጐን ለጐን፥ አጠገብ ወይም ከወይን ጠጅ ጋር” ወይም “ከወይን ጠጅ ጐን” የማይገኝ ማለት ነው። ማንም ኤጲስ ቆጳስ፡ “ከወይን ጠጅ አጠገብ” ወይም፣ “ከወይን ጠጅ ጋር” መገኘት እንደሌለበት መጽሐፍ ቅዱስ ይጠይቃል። በሌላም አገላለጽ የሚያሰክር የወይን ጠጅ መጠጣት የለበትም” ወይም ለመጠጣት መፈተን የለበትም ወይም መሣሪክ የለበትም፥ ወይም ከሰካራሞች ጋር መብላትና መጠጣት የለበትም (ማቴ 24፥49)።

(1) በብሉይ ኪዳን ዘመን ነገሥታትና መሳፍንት ከሚያሰክር መጠጥ ፈጽሞ ይርቁ ዘንድ ደንብ ነበር (ምሳ 31፥4-7)። ለእግዚአብሔር በከፍተኛ ደረጃ ለመቀደስ ለሚፈልጉትም ሁሉ ከሚያሰክር መጠጥ መራቅ እንደዚሁ ደንብ ነበር (ዘሌ 10፥8-11፤ ዘኍ 6፥1-5፤ መሳ 13፥4-7፤ 1ሳሙ 1፥14-15፤ ኤር 35፥2-6 ይመ፤ እንዲሁም ምሳ 23፥31 እና ማብ ይመ፤ በገጽ 232 ላይ፣ “*የወይን ጠጅ በብሉይ ኪዳን*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ሹም በመሆን የሚያገለግሉትም ከዚህ ያነሰ ደንብ ሊኖራቸው አይገባም። በተጨማሪም በቤተ ክርስቲያን የሚገኙ አማኞች ሁሉ ካህናትና ነገሥታት ተብለዋል (1ጴጥ 2፥9፤ ራእ 1፥6)፤ በመሆኑም እግዚአብሔር በሰጠው ሉዐላዊ ሕግ መሠረት መኖር አለባቸው (ዮሐ 2፥3 እና ማብ፤ ኤፌ 5፥18 እና ማብ፤ 1ተሰ 5፥6 እና ማብ፤ ቲቶ 2፥2 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 232 ላይ፣ “*የወይን ጠጅ በብሉይ ኪዳን*” (ቍ 1) እና (ቍ 2) በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥4 የገዛ ቤተ ሰቡን በአግባቡ የሚያስተዳድር፤** የኤጲስ ቆጳስነትን ሹመት ለሚፈልግ ሰው ዋና የሆነው የብቃት መለኪያ ለቃል ኪዳን ጋብቻና ለቤተሰባዊ ግንኙነት ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው። በዚህ ረገድ ይበልጥ ለመረዳት፥ (በገጽ 1925 ላይ፣ “*የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥7 መልካም ምስክርነት ሊኖረው ይገባል፤** አንድ መሪ ወይም መሪ ለመሆን የሚችል አማኝ ከሁለት አቅጣጫ፣ “*መልካም ምስክርነት*” እንዲኖረው ያስፈልጋል፤ (ሀ) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ይኸውም በቤተ ክርስቲያን አባላት ዘንድ ነው (ቍ 1-6)፤ እንዲሁም (ለ) በውጭ ባሉት ዘንድ ይኸውም ከቤተ ክርስቲያን ውጭ ባሉት ማለት ነው (ቍ 7)። ከክርስቶስ ወንጌል ጋር ጐን ለጐን የሚጓዝ ቀደም ያለና አሁንም እውን በመሆን ላይ ያለ የጽድቅ የሕይወት ዘይቤ እንዲኖረው ያስፈልጋል።

**3፥8 ዲያቆናትም፤** (በግሪክ፥ “ዲያኮኖስ”) ማለት፣ “አገልጋዮች” ማለት ነው። በአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ከአገልግሎታቸው ውስጥ አንዱ የሆነው በሐሥ 6፥1-6 ላይ ተመልክቶአል። መጋቢዎች ወይም ፓስተሮች ራሳቸውን ለጸሎትና ለቃሉ አገልግሎት እንዲሰጡ፣ ዲያቆናት ጊዜያዊና የኑሮ ጣጣ የሆኑትን ነገሮች በሥርዐት በማስተዳደር መጋቢዎችን ማገዝ ነበረባቸው (ሐሥ 6፥2)። የዲያቆናት መንፈሳዊ የብቃት መለኪያ በመሠረቱ ከመጋቢዎች ወይም ከፓስተሮች ጋር ተመሳሳይ ነው (ቍ 1-7ን ከቍ 8-13 ጋር ያነጻጽሩ፤ ሐሥ 6፥3 ይመ)።

**3፥8 ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፤** የቃሉን ማለትም፣ “የማይጐመጁ” የሚለውን ቃል አጐላማሽ ሐረግ አስመልክቶ የሚከተለውን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው (እንደዚሁም ቍ 3 እና ማብ ይመ)፤ (ከ) ሐዋርያው በልክ እስከ ሆነ ድረስ በዘመኑ የነበረውን ማንኛውንም ዐይነት መጠጥ እንዲጠጣ ፈቅዶአል ማለት ከግብረገብ አኳያ ሲታይ ከቶ የማይታሰብ ነው። አብዛኛው የወይን ጠጅ ብርቱ መጠጥ ከሚያደርገው ጋር የተደባለቀና አደገኛ ነበር (ከምሳ 23፥29-35 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) አንዳንድ ተርጓሚዎች ጳውሎስ ሱስ በሚያሲዝ መልኩ ዲያቆናት መጠጥ መጠጣት የለባቸውም ብሏል ይላሉ፡ እንዲህም ሲሉ በልክ መጠጣትን አልነቀፈም ማለታቸው ነው። ይሁን እንጂ ሰካራምነት አስከፊ ኀጢአት በመሆኑ፣ በዚህ የተለከፈ ሰው ከእግዚአብሔር መንግሥት እንደሚለይ ጳውሎስ ይናገራል (1ቆሮ 6፥10)። ጳውሎስ ለዲያቆናት ከፍተኛውን ደንብ ሲሰጣ፣ “ዲያቆን አዘውታሪ ጠጭ መሆን የለበትም” (ይኸውም ድኅነትን እንዳላገኘ ሰው ማለት ነው) ብሎ ሲጽፍ በልክ የሚጠጣን መጠጥ ይደግፋል ብሎ አንድምታ መስንዘር ከቂልነትም ያለፈ ቂልነት ነው (ከቍ 2 ጋር ያነጻጽሩ)። ጳውሎስ ለወይን ጠጅ የሰጠው አሳቤ ከሚያሰክር የወይን ጠጅ የተለየ መሆን አለበት።

(3) ጳውሎስ በልክ የሚጠጣን የአልኮል መጠጥ ከሚፈቅድ ይልቅ፣ በጣዖት አምላኪ ኅብረተሰብ ዘንድ የተፈቀደውና ይጠጣ የነበረው የማያሰክር የወይን ጠጅ ከልክ በላይ እንዳይጠጣ ሳያስጠነቅቅ አልቀረም (በገጽ 1547 ላይ፣ “*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ለማያሰክር መጠጥ ሱሰኛ ሆኖ መገኘት እንኳ በጣዖት አምላኪ ኅብረተሰብ ዘንድ ተስፋፍቶ ይገኝ የነበረና ከስግብግብነት ጋር እኩል የሚታይ ጉድለት ነበር (ፕሊኒ የተባለ ጸሐፊ የጻፈውን፥ “ናቹራል ሂስትሪ” 14፣ 28፣ 139 ይመ)። ጳውሎስ በጎ በሆነው ነገር ላይ እንኳ በማንኛውም የሕይወት ፈርጅ ረገድ ራስን መግዛት አስፈላጊ መሆኑን አጽንዖት ያደርጋል፥ በምሳ 25፥27 ላይ፣ “ከመጠን በላይ ማር መብላት ጥሩ አይደለም” የሚለውን ያስተውሉ።

# የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት

*1ጢሞ 3፥1-3 "'ማንም የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ቢፈልግ፣ መልካም ሥራን ይመኛል' የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል ... ሊሆን ይገባዋል።"*

---

ማንም ሰው ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ቢፈልግ (ግሪክ፣ "ኤጲስ ቆጶስ" ይኸውም የመጋቢ ራእይ ያለው ወይም ስተር ማለት ነው)፣ መልካም ሥራን ይመኛል ማት ነው (1ጢሞ 3፥1)። ይሁን እንጂ እንደነዚ ያሉ ሰዎች ያ ፍላጎታቸው በእግዚአብሔር ቃልና (3፥1-10፤ 4፥12) ቆጶስ ክርስቲያን (3፥10) መረጋገጥ አለበት፤ እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን የተለየን የብቃት መለኪያን መሥርቶአልና። የኤጲስ ቆጶስን ሥራ ለመሥራት የእግዚአብሔር ጥሪ ነው የተባው ሁሉ በ1ጢሞ 3፥1-13፤ 4፥12፤ ቲቶ 1፥5-9 መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው መለኪያ መሠረት በቤተ ክርስቲያን አባላት መፈተን ይኖርበታል (በገጽ 1866 ላይ፣ "የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ቤተ ክርስቲያን ማንንም ሰው ፍላጎቱን፣ ዕውቀቱን፣ ሽክሙን ወይም አለኝ የሚለውን ራእይ ወይም ጥሪ መሠረት በማድረግ ለአገልግሎት ሥራ ድጋፍ መስጠት የለበትም። ዛሬም ቢሆን ቤተ ክርስቲያን እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ የሰጠውን የብቃት መለኪያን የመቀነስ መብት የላትም። ለእግዚአብሔር ስም፣ ለመንግሥቱ፣ ለኤጲስ ቆጶስ ከፍተኛ የኀላፊነት ቢሮ ሲባል እነዚህ መለኪያዎች ፍጹም እንደ ሆኑ መጠበቅ አለባቸው፤ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸውም ግድ ነው።

(1) ኤጲስ ቆጶሶችን በተመለከተ የተዘረዘረው መለኪያ በመሠረቱ ግብረገባዊና መንፈሳዊ ነው። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መሪነትን የሚፈልጉት ሰዎች የተፈተነ ጠባዩ ከተክለ ሰብእና፥ ከስብከት ስጦታ ከአስተዳደር ችሎታ ወይም ከላቀ ትምህርት እጅግ አስፈላጊ ነው። የዚህ የብቃት መለኪያ እምብርት እውን ሆኖ የሚገኘው ፈሪሀ እግዚአብሔር ባለው ጥበብ፥ ትክክል ከሆነ ምርጫና በግል ቅድስና ላይ ነው። የኤጲስ ቆጶስነትን ኀላፊነት የሚፈልገው ሰው መንፈሳዊ ታሪክ፣ "አስቀድሞ" መፈተን ይኖርበታል (ከ1ጢሞ 3፥10 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ ከፍተኛውን የብቃት መለኪያ ሰጥቶአል፤ ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን የታጨ ሰው በጽኑ መንፈስ ክርስቶስንና የጽድቅ መርሕዎውን የተከተለ፣ የታማኝነት፣ የእውነት፣ የሐቅና የንጽሕና አርአያ ሆኖ የሚታይ አማኝ መሆን አለበት። በሌላም አባባል ጠባዩ የክርስቶስን ትምህርት በማንጸባረቅ፣ በማቴ 25፥21 ላይ፥ "በትንሽ ነገር ላይ ታማኝ" መሆን፣ "በብዙ ነገር ላይ" ወደ መሾም ያደርሳል የሚለውን የሚያሳይ መሆን አለበት።

(2) ከሁሉም በላይ ክርስቲያን መሪዎች፣ "ለሚያምኑት ... አርአያ" መሆን አለባቸው (1ጢሞ 4፥12 ይመ፤ ከ1ጴጥ 5፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውና ጽኑ እምነታቸው በማኅበረ ምእመናኑ ዘንድ ከሁሉ የላቀ ለአርአያነት የሚበቃ ሆኖ መታየት አለበት፤ (ሀ) ኤጲስ ቆጶሶች ፈተና በሚያገጥም ጊዜ ለክርስቶስና ለወንጌል ታማኝነትንና ፍቅርን በመግለጽ ረገድ በፈሪሀ እግዚአብሔር፣ በታማኝነትና በንጽሕና ረገድ ከፍተኛውን አርአያነት ማሳየት አለባቸው (1ጢሞ 4፥12፡15)። (ለ) የእግዚአብሔር ሕዝብ ክርስቲያናዊ ሥነምግባርንና እውነተኛውን ፈሪሀ እግዚአብሔር ሊማር ያለባቸው ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ሳይሆን፣ በሐዋርያዊ የብቃት መለኪያ መሠረት ከሚኖሩት ከመጋቢዎች አርአያነት ጭምር ነው። የሕይወት አካሄዳቸው የእምነት መግለጫ የሆኑ መጋቢዎች እግዚአብሔር ለመሪነት ላለው ዕቅድ እጅግ አስፈላጊዎች ናቸው። በቤተ ክርስቲያን ያሉት ይከተሉት ዘንድ ነቀፋ የሌለበትን አካሄድ ዘርግቶ ለመሪነት የፈሪሀ እግዚአብሔር መርሕ አስፈላጊ ነው የሚለውን ወደ ጐን ማለት የቅዱሳ መጻሕፍትን ግልጽ ትምህርት ችላ ማለት ነው። መጋቢዎች ለክርስቶስ ያላቸው ታማኝነት አርአያ ወይም ምሳ ሆኖ የሚታይባቸው ሰዎች መሆን አለባቸው (ከ1ቆሮ 11፥1፤ ከፊል 3፥17፤ ከ1ተሰ 1፥6፤ ከ2ተሰ 3፥7-9፤ ከ2ጢሞ 1፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) መንፈስ ቅዱስ አማኝ በቤት፣ በጋብቻና በቤተ ሰብ ውስጥ ያለውን ግንኙነት ከፍተኛ ጉዳይ አድርጎ ይቈጥረዋል (1ጢሞ 3፥2፡4-5፤ ቲቶ 1፥6)። ኤጲስ ቆጶስ በተለይ ለሚስቱና ለልጆቹ ባው ታማኝነት ረገድ ለቤተ ሰቡ አርአያ መሆን አለበት። እንግዲያውስ በዚህ በኩል ደክሞ ከተገኘ፣ "የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ሊጠብቅ ይችላል?" (1ጢሞ 3፥5)። "የአንዲት ሚስት ባል ... ሊሆን ይገባዋል" (1ጢሞ 3፥2-3)። ለኤጲስ ቆጶስነት የታጨ

ሰው ግብረጋዊ በሆነ መልኩ ለሚስቱ ታማኝ የሆነ አማኝ መሆን እንዳለበት የሐረጉ ቅንብር ጉልሕ ያደርጋል። የግሪኩ ሐረግ ቃል በቃል ሲተረጐም፣ ("ማያስጎና ይክስ" ባለቤትነትን የሚያመለክት ሐረግ ነው) "የአንዲት ሴት ባል" የሚል ሲሆን፣ ይኸውም የሚስቱ ታማኝ ባል ማለት ነው። ይህም ማለት ለኤጲስ ቆጶስነት የታጨ ሰው በዚህ ዐቢይ በሆነ የሕይወት ዘርፍ ሁሉ ታማኝ ለመሆኑ ማረጋገጫ ማሳየት አለበት። መሪ ለመሆንና ለቤተ ክርስቲያንም ምሳ ለመሆን የሚፈልግ ሰው፣ ለሚስቱና ለቤተ ሰቡ ግብረገባዊ ታማኝነቱን በጽናት መጠበቅ አለበት።

(4) ከዚህም የተነሣ በአስከፊ ኀጢአት ወይም በግብረገባዊ መተላለፍ በደለኞች የሆኑ ሰዎች ከመጋቢነትና በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኝ ከከፍተኛ የመሪነት ኀላፊነት ራሳቸውን ብቃተ ቢስ አድርገዋል (ከ1ጢሞ 3፥8-12 ጋር ያነጻጽሩ)። እንደዚህ ያሉ ሰዎች በእግዚአብሔር ጸጋ አብዝቶ ይቅር ሊባሉ ይችላሉ፤ ነገር ግን በእምነት፣ በንጽሕናና በበጎ አስተምህሮ ረገድ የማይናወጥ ጽናት ያላቸው ሆነው መታየት አይችሉም (4፥11-16፤ ቲቶ 1፥9)። ከዚህ ቀደምም በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ መሪዎች ከፍተኛ ግብረገባዊና መንፈሳዊ የብቃት መለኪያን ማክበር እንዳለባቸው እግዚአብሔር ግልጽ አድርጎአል፤ እነርሱ ማክበር ካልቻሉ ሌሎች ተተኪዎች ኀላፊ ይሆናሉ (ዘፍ 49፥4 እና ማብ፤ ዘሌ 10፥2 እና ማብ፤ 21፥7፡17 እና ማብ፤ ዘኍ 20፥12 እና ማብ፤ 1ሳሙ 2፥23 እና ማብ፤ ኤር 23፥14 እና ማብ፤ 29፥23 እና ማብ ይመ)።

(5) ከዚህም በተጨማሪ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለውን ታዛዥነት እንዲሁም ለሚስቱና ለቤተ ሰቡ ያውን ታማኝነት ችላ ያለ ኤጲስ ቆጶስ ከኀላፊነት ቦታው መወገድ እንዳለበት በ1ጢሞ 3፥2፡7 ላይ መርሕ ቍልጭ ብሎ ሰፍሮአል። ከዚህ በኋላ፥ "የማይነቀፍ" ሰው ነው ሊባል አይችልም። ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ዝሙትን የሚፈጽም ሰው፣ የእግዚአብሔር ቃል፣ "ኀፍረቱ ከቶ አይወገድም" ይለዋል (ምሳ 6፥33፤ 6፥32 እና ማብ ይመ)።

(6) እንዲህ ሲባልም እግዚአብሔር ወይም ቤተ ክርስቲያን ይቅርታ አያደርጉም ማለት አይደለም። ለተፈጸመ ኀጢአት ፈሪሀ እግዚአብሔር ያለበት ሐዘን ከተደረገና ንስሓ ከተገባ እግዚአብሔር በ1ጢሞ 3፥1-13 ላይ የተዘረዘረውን ማንኛውንም ኀጢአት ይቅር ይላል። እንዲህ ያለ ሰው ከእግዚአብሔር ምሕረት የተነሣ ይቅር እንደሚባል፣ ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያን ጋር ያለው ግንኙነትም ወደ ቀድሞው ሁኔታ ሊመለስለት እንደሚችል ግልጽ ሊሆን ይገባል። ይሁን እንጂ አንዳንድ ኀጢአት የሚያስጠው ሞገስና የሚያስድረው ኀፍረት (ይኸውም ነቀፌታ) ከፍተኛ በመሆኑ፣ ሰውየው ይቅርታን ካገኘ በኋላ እንኳን ያ የኀጢአት ጠባሳ እስከ ዕድሜ ልክ እንደሚቆይ መንፈስ ቅዱስ ተናግሮአል (ከ2ሳሙ 12፥9-14 ጋር ያነጻጽሩ)።

(7) ታዲያ ከዚህ መርሕ አኳያ ንጉሥ ዳዊት እንደምን ይታያል? ዳዊት ዝሙት ፈጽሞና ነፍስ አጥፍቶ እያለ (2ሳሙ 11፥1-21፤ 12፥9-15)፥ የእስራኤል ንጉሥ ሆኖ እስከ መጨረሻው መዝለቁ አንድ ኤጲስ ቆጶስ ከላይ የተጠቀሱትን በደሎች ቢፈጽምም በኀላፊነቱ መቀጠል አለበት ለሚለው ሐሳብ፣ የዳዊት ቀጣይ ኀላፊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያት ሆኖ ይቀርባል። ይህ ንጽጽር ግን ልዩ ልዩ በሆኑ ምክንያቶች መሠረተ ቢስ ነው። (ሀ) በብሉይ ኪዳን የእስራኤል ንጉሥ ኀላፊነትና በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ መንፈሳዊ መሪ የሆነ ሰው ሁለቱ ፈጽሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። እግዚአብሔር ንጉሥ ዳዊትን ብቻ ሳይሆን ወደር የማይገኝላቸው ጨካኝ ነገሥታትም የእስራኤል ነገሥታት ሆነው እንዲቀጥሉ ፈቅዶአል። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተገዛች ቤተ ክርስቲያን መሪነት እጅግ ከፍተኛ የሆነ የብቃት መለኪያን ይጠይቃል። (ለ) እግዚአብሔር በቸርነቱ በሰጠው መገለጥና በአዲስ ኪዳን የብቃት መለኪያ መሠረት፣ ዳዊት የአዲስ ኪዳን ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶስ ለመሆን ብቃት አይኖረውም ነበር፤ ብዙ ሚስቶች ነበሩት፤ ለጋብቻው ታማኝ አልነበረም፤ በሚያሳዝን ሁኔታ የራሱን ቤት ማስተዳደር አልቻለም፤ ነፍስ የጠፋበትና ደም ያፈሰሰ ዐመፀኛ ሰው ነበር። ዳዊት ከኀጢአቱ የተነሣ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ በእግዚአብሔር ቅጣት ሥር እንደ ነበር ማስታወሱ ተገቢ ነው (2ሳሙ 12፥9-12 እና ማብ ይመ)።

(8) የዛሬዎቹ አብያተ ክርስቲያናት የኤጲስ ቆጶስን ጸድቅ መለኪያ አስመልክቶ እግዚአብሔር በሐዋርያት በኩል ከሰጠው የመጀመሪያ መገለጥ ገሸሽ ማለት የለባቸውም። ይልቁንስ ቤተ ክርስቲያን መሪዎቿን አስመልክቶ በከፍተኛው የቅድስና መለኪያ፣ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ እንዲሁም ለቅድስና ባላቸው ጽናት ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት። "ለሚያምኑት በንግግርና በኑሮ፣ በፍቅር፣ በእምነትና በንጽሕና አርአያ" ሲሆኑ (1ጢሞ 4፥12)፣ እንዲጸለይላቸው፥ እንዲበረታቱና እንዲደገፉ ያስፈልጋል።

ቃላቸውን የማይለዋውጡ፣ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጐመጁ፣ ያለ አግባብ የሚገኝ ጥቅምንም የማያሳድዱ ሰዎች መሆን ይገባቸዋል፤ 9የእምነትንም ጥልቅ ምስጢር በንጹሕ ኅሊና መጠበቅ አለባቸው። 10እነርሱም አስቀድመው ይፈተኑ፤ ከዚያም፣ አንዳች ነቀፋ ካልተገኘባቸው በዲቁና ያገልግሉ።

11እንዲሁ ሴቶችምa የተከበሩ፣ ሐሜተኞች ያልሆኑ ነገር ግን ልከኞችና በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባል።

12ዲያቆናት የአንዲት ሚስት ባል መሆን ይገባቸዋል፤ ደግሞም ልጆቻቸውንና ቤተ ሰቦቻቸውን በአግባቡ የሚያስተዳድሩ መሆን አለባቸው። 13በአግባቡ ያገለገሉ ለራሳቸው ትልቅ ክብርን፣ በክርስቶስ ኢየሱስም ባላቸው እምነት ብዙ ድፍረትን ያገኛሉ።

14ወደ አንተ ቶሎ ለመምጣት ተስፋ ባደርግም ይህን ትእዛዝ እጽፍልሃለሁ፤ 15ይህንም የምጽፍልህ ብዘገይ እንኳ ሰዎች በእግዚአብሔር ቤት እንዴት መኖር እንዳለባቸው እንድታውቅ ነው፤ ቤቱም የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ይኸውም የእውነት ዐምድና መሠረት ነው። 16የእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ምስጢር ያለ ጥርጥር ታላቅ ነው፤

እርሱb በሥጋc ተገለጠ፤
በመንፈስ ጸደቀ፤
  በመላእክት ታየ፤
  በአሕዛብ ዘንድ ተሰበከ፤
በዓለም ባሉት ታመነ፤
  በክብር ዐረገ።

## ለጢሞቴዎስ የተሰጠ መመሪያ

4 በኋለኞች ዘመናት አንዳንዶች እምነትን ክደው አታላይ መናፍስትንና የአጋንንትን

3፥9 ሐሥ23፥1
3፥10 1ጢሞ5፥22
3፥11 ቲቶ2፥3; 2ጢሞ3፥3; ቲቶ2፥3
3፥12 ቲቶ2፥4
3፥15 ቲቶ5፥; ማቴ16፥16፤ 1ቆሮ10፥32
3፥16 መዝ9፥11፤ ማር16፥19፤ ዮሐ1፥14፤ ሮሜ6፥25፤ ቆላ1፥23፤ 1ጢሞ2፥2
4፥1 ማር13፥5፤ ዮሐ16፥13፤ ሐሥ8፥29፤ 1ቆሮ2፥10፤ 2ጢሞ3፥1፤ 2ጴጥ3፥3

a3፥11 ወይም ሚስቶቻቸው ወይም ዲያቆናውያት
b3፥16 አንዳንድ ቅጆች እግዚአብሔር ይላሉ።
c3፥16 ወይም በአካል

(4) በዚህ ዐይነቱ ምክር ሐዋርያው ጳውሎስ ብቻውን አልነበረም፤ ጣፋጭና አልኮልነት የሌለውን የወይን ጭማቂ ከልክ በላይ መጠጣት ተገቢ አለመሆኑን የረቢያውያን ጽሑፍ ማስጠንቀቂያን እናገኛለን። ይህ ጽሑፍ ሁሉንም ዐይነት ጣፋጭ ጭማቂ ስለያዘው ግን የሚያሰክር መጠጥ በላዩ ላይ መጨመር ስለሌለበትና የሚሰክር መጠጥ ስለሌለውም፣ "ቲሮሽ" ስለ ተባለው የወይን መጠጥ (ቶሴፍ ዕብዕ3 ኔድ) እንዲህ ይላል፣ "በልክ ከተጠጣ የመሪነትን ብልሃት ይሰጣል፤ ... ከልክ በላይ ከተጠጣ ግን ወደ ድህነት ያመራል (ዮማ 76 ለ)። "አዘውትሮ የሚጠጣው ሰው ደሀ ሊሆን እንደሚችል ጥርጥር የለውም (ዘ፡ ጁዊሽ፡ ኢንሳይክሎፒዲያ 12፡ 533፤ በገጽ 1547 ላይ፣ "የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**3፥15 ቤተ ክርስቲያን ... የእውነት ዐምድና መሠረት ነው፤** ቤተ ክርስቲያን የወንጌል እውነት መሠረት መሆን አለበት፤ በክርስቶስና በሐዋርያት የተገለጠውን እውነት በመቀበልና በመታዘዝ (ማቴ 13፥23)፣ በልብ ውስጥ በመሰወር (መዝ 119፥11)፣ የሕይወት ቃል መሆኑን በማወጅ (ፊል 2፥16)፣ ስለ ወንጌል በመሟገት (ፊል 1፥16)፣ በመንፈስ ቅዱስ ኀይሉን በማሳየትም ቃሉን የሙጥኝ ብላ መያዝና እክብራ መጠበቅ አለባት (ማር 16፥15-20፤ ሐሥ 1፥8፤ 4፥29-33፤ 6፥8)።

**4፥1 አንዳንዶች እምነትን ክደው፤** መንፈስ ቅዱስ በኋላኛው ዘመን በኢየሱስ ክርስቶስ በግል አዳኝነት ከማመንና (በገጽ 1962 ላይ፣ "ክሕደት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ) ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት (ከ2ተሰ 2፥3፤ ከይሁ 1፥3-4 ጋር ያነጻጽሩ) መለየት ሊኖር እንደሚችል ቍልጭ አድርጎ ገልጾአል፤ (1) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከፍተኛ ስጦታና በከፍተኛ ደረጃ በእግዚአብሔር የተቀቡ አገልጋዮች ብቅ ይላሉ። አንዳንዶች ለእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ይሠራሉ፤ የወንጌልንም እውነት ውጤታማ በሆነ መልኩ ይሰብካሉ፤ ነገር ግን ከሙእነተኛው እምነት ይርቃሉ፤ ቀስ በቀስም ወደ አሳች መናፍስትና የስሕተት አስተምህሮ ልባቸውን ያቀናሉ፤ ቀደም ሲል ከነበራቸው መቀባት የተነሣና ለእግዚብሔር ከነበራቸው የላቀ ስሜት የተነሣ ብዙዎችን ያስታሉ (በገጽ 1471 ላይ፣ "ታላቁ መከራ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) ብዙዎች አማኞች እውነትን ሳይወዱ በመቅረታቸው (2ተሰ 2፥10)፣ ዘመን አመጣሽ አዝማሚያንም ሳይቃወሙ በመቅረታቸው (ከማቴ 24፥5፡ 10-12 ጋር ያነጻጽሩ፡ 2ጢሞ 3፥2-3 እና ማብ ይመ)፣ ከእምነት ይርቃሉ። ስለዚህ ተመሳስለው የሚኖሩት አገልጋዮችና መምህራን የተጣመመ ወንጌል፣ በእያሌ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የሚገጥመው ተቃውሞ ቍጥር ውስጥ የሚገባ አይደለም (4፥1፤ 2ጢሞ 3፥5፤ 4፥3 ይመ፡ 2ቆሮ 11፥13 እና ማብ ይመ)።

(3) ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ማስተማር እየገነነ መምጣት የቻለው፣ ሰይጣን በእግዚአብሔር ሥራ ላይ ተቃውሞውን አጠንክሮ አጋንንት ሰራዊቱ በመምራቱ ነው። በክርስቶስ ጳግም ምጻት ዋዜማ የሚከሰቱት ይከሠታሉ፤ እነርሱም ሰይጣናዊ አሠራር፣ መናፍስትን መጥራት፣ ለሙታት ራስን አሳልፎ መስጠት፣ በዓለምና በቤተ ክርስቲያን ውስጥየሰይጣን ማታለል መስፈን ናቸው (ኤፌ 6፥11-12 ይመ፡ እንዲሁም፣ በገጽ 1499 ላይ፣ "በሰይጣንና በአጋንንት ላይ የተሰጠን ሥልጣን" እና፡ በገጽ 1913 ላይ፣ "የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን" በሚል ርእስ የቀረቡትን የትኩረት ጽሑፎች ይመ)።

(4) አማኝ ከእንደዚህ ዐይነቱ መታለል ሊጠበቅ የሚችለው፡ ለእግዚአብሔርና አፊዎት ላለው ቃሉ ታማኝ በመሆንና ታላቅ ምግባርና መቀባት ያላቸው ሰዎች እውነትንና ስሕተትን አደባልቀው በመያዛቸው፡ ሊታለሉና ከዚያም ሊያታልሉ እንደሚችሉ ግንዛቤ በማግኘት ነው። ይኸው ግንዛቤም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ከልብ በሆነ ፍላጎት ለመነሣሣት (ዮሐ 7፥17)፥ በጽድቅ መንገድ ለመመላለስና እግዚአብሔርን ለመፍራትም (መዝ 25፥4-5፡12-15) በተዳረገ ቍርጥ ሐሳብ መታጀብ አለበት።

(5) በክርስትና እምነት ውስጥ ክሕደት እየገነነ በመምጣቱ፣ ታማኝ የሆኑ ክርስቲያኖች በመጨረሻው ዘመን እውነተኛ የሆነ ተሐድሶ ወይም በአዲስ ኪዳን ላይ ቁልጭ ብሎ በሚታየው አሠራር መልኩ ውጤታማየሆነየወንጌል ሥርጭት ሊካሄድ አይችልም ብለው ማሰብ የለባቸውም። በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር ስሙን የሚጠሩትንና ከዚህ ከተበላሸ ትውልድ ራሳቸውን የሚለዩትን ሁሉ እንደሚያድናቸውና

ትምህርት እንደሚከተሉ መንፈስ በግልጥ
ይናገራል። [2]እንዲህ ያለው ትምህርት
የሚመጣው ኅሊናቸው በጋለ ብረት የተጠበሰ
ያህል ከደነዘዘባቸው ግብዝ ውሸተኞች ነው።
[3]እነርሱ፣ ሰዎች እንዳያገቡ ይከለክላሉ፤
የሚያምኑና እውነትን የሚያውቁ ሰዎች
እግዚአብሔር የፈጠረውን በምስጋና
የሚቀበሉትን እንዳይበሉ ያዛሉ፤ [4]እግዚአብሔር
የፈጠረው ማንኛውም ነገር መልካም ነውና፤
በምስጋና ከተቀበሉትም የሚጣል ምንም
ነገር የለም፣ [5]በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት
የተቀደሰ ነውና።
[6]ይህን ትእዛዝ ለወንድሞች ብታሳስብ፣
በእምነት ቃልና በተቀበልኸው መልካም
ትምህርት ታንጸህ የክርስቶስ ኢየሱስ
በጎ አገልጋይ ትሆናለህ። [7]እግዚአብሔርን
ከማያከብር ርባናቢስ እፉ ታሪክና
ከአሮጊቶች ተረታ ተረት ራቅ፤ ይልቁንም
ለእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ራስህን
አሠልጥን። [8]የአካል ብቃት ልምምድ
ለጥቂት ነገር ይጠቅማልና፤ ለእውነተኛ
መንፈሳዊ ሕይወት ራስን ማሠልጠን ግን
ለአሁኑም ሆነ ለሚመጣው ሕይወት ተስፋ
ስላለው ለሁሉቱም ይጠቅማል።
[9]ይህ ቃል የታመነና ሙሉ ለሙሉ ሊቀበሉት
የሚገባ ነው፤ [10]ለዚህ ብለን እንጥራለን፤
እንደክማለንም፤ ይኸውም ለሰዎች ሁሉ
በተለይም ለሚያምኑት አዳኝ በሆነው በሕያው
እግዚአብሔር ተስፋ ስለምናደርግ ነው።
[11]እነዚህን ነገሮች እዘዝ፤ አስተምርም።
[12]ወጣትነትህን ማንም አይናቅ፤ ነገር ግን
ለሚያምኑት በንግግርና በኑሮ፣ በፍቅር፣
በእምነትና በንጽሕና አርአያ ሁንላቸው።
[13]እኔ እስክመጣ ድረስ ለማንበብ፣ ለመምከርና
ለማስተማር ትጋ። [14]ሽማግሌዎች እጃቸውን
በአንተ ላይ ሲጭኑ በትንቢት የተሰጠህን
የጸጋ ስጦታ ቸል አትበል። 2ጢሞ 1፥6
[15]ስለ ሁሉ ማደግህን ያይ ዘንድ በእነ ዚህ
ነገሮች ላይ አትነተር፤ በትጋትም ፈጽማቸው፤
[16]ለሕይወትህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፤
በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፣
ራስህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና።

4፥2 ኤፌ.4፥19 4፥3 ቆላ4፤ ዘፍ1፥29፤ 9፥3፤ ሮሜ14፥6፤ 1ቆሮ10፥30፤ ቈላ2፥16፤ ዕብ13፥4 4፥4 ዘፍ1፥10:12: 18:21:25:31፤ ማር7፥18-19፤ ሮሜ14፥14-18፤ ሐዋ10፥15 4፥5 ዕብ4፥12 4፥6 1ጢሞ1፥10፤ 2ጢሞ3፥15 4፥7 1ጢሞ1፥4፤ 2፥2፤ 2ጢሞ2፥16 4፥8 መዝ37፥9:11፤ ምሳ22፥4፤ ማቴ6፥33፤ ማር10፥29:30፤ 1ጢሞ6፥6 4፥9 1ጢሞ1፥15 4፥10 ማቴ16፥16፤ ሉቃ1፥47፤ 2፥11 4፥11 1ጢሞ5፥7፤ 6፥2 4፥12 ሩል3፥17፤ 1ተሰ1፥7፤ 2ተሰ3፥9፤ 1ጢሞ1፥14፤ 2ጢሞ1፥7፤ ቲቶ2፥7:15፤ 1ጴጥ5፥3 4፥13 ሉቃ4፥16፤ ሐዋ13፥14-16፤ ቈላ4፥16፤ 1ተሰ5፥27፤ 1ጢሞ3፥14 4፥14 ሐዋ6፥6፤ 11፥30፤ 1ጢሞ1፥18፤ 2ጢሞ1፥6 4፥16 ሮሜ11፥14 5፥1 ዘሌ19፥32፤ ቲቶ2፥2:6 5፥3 ቁ5፥16

## ስለ መበለቶች፣ ስለ ሽማግሌዎችና ስለ ባሪያዎች የተሰጠ ምክር

5 አረጋዊውን ሰው እንደ አባትህ ቈጥረህ
ምከረው እንጂ በኀይለ ቃል አትናገረው።
ወጣት ወንዶችን እንደ ወንድሞች
ተቀበላቸው፤ [2]እንዲሁም አሮጊቶችን እንደ
እናቶች፣ ወጣት ሴቶችን ደግሞ እንደ
እኅቶች በፍጹም ንጽሕና አስተናግዳቸው።
[3]በርግጥ ችግረኛ የሆኑትን መበለቶች
ተንከባከባቸው። [4]አንዲት መበለት ግን ልጆች
ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሯት፣ እነዚህ
ልጆች የራሳቸውን ቤተሰብ በመርዳትና
ለወላጆቻቸውም ብድራትን በመመለስ ከሁሉ
በፊት እምነታቸውን በተግባር ለማሳየት መማር
ይገባቸዋል፤ ይህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ
ነውና። [5]በርግጥ መበለት የሆነች፣ ብቻዋንም
የምትኖር ተስፋዋን በእግዚአብሔር ላይ
ታደርጋለች፤ ለጸሎትና የእግዚአብሔርን
ርዳታ ለመለመን ሌሊትና ቀን ትተጋለች።
[6]ምድራዊ ደስታን የምትሻ መበለት ግን
በሕይወት ብትኖርም የሞተች ናት። [7]ማንም
የሚነቀፍበት ነገር እንዳይኖር፣ ይህንም
ትእዛዝ ለሕዝቡ ስጥ። [8]አንድ ሰው ዘመዶቹን፣
በተለይም የቅርብ ቤተ ሰቡን የማይረዳ ከሆነ
ሃይማኖቱን የካደ፣ ከማያምንም ሰው ይልቅ
የባሰ ክፉ ነው። [9]ዕድሜዋ ከሥልሳ ዓመት
ያነሰ መበለት በመዝገብ ላይ አትጻፍ፤

5፥4 ቍ8፤ ሮሜ12፥2፤ ኤፌ5፥10፤ 6፥1፤ 2፤ 1ጢሞ2፥3 5፥5 ቍ3:16፤ ሉቃ2፥37፤ ሮሜ1፥10፤ 1ቆሮ7፥34፤ 1ጴጥ3፥5 5፥6 ሉቃ15፥24፤ 5፥7 1ጢሞ4፥11፤ 6፥2 5፥8 2ጴጥ2፥1፤ ይሁ1፥4

[a]5፥9 ወይም ለባልዋ ታማኝ የነበረች

(ሐዋ 2፥16-21:33:38-40፤ 3፥19)። መንፈሱንም በእነርሱ ላይ እንደሚያወርድ ተስፋ ሰጥቶአል።

**4፥12 አርአያ ሁንላቸው፤** ለአንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ ከሆኑት የብቃት መለኪያዎች አንዱ ይህ ነው፤ "አርአያ" ለሚለው ሐሳብ፣ የግሪክ ቃል ትርጕሙ፣ "ተሳ" የሚል ሲሆን፣ "ሞዴል፣" "አምሳል"፣ "አቻ የለሽ" ወይም "ልክ" ማለት ነው። አንድ መጋቢ ከሁሉም በላይ ፈሪሀ እግዚአብሔርን አስመልክቶ የታማኝነት፣ የንጽሕናና የጽናት አርአያ መሆን አለበት። አንድ መሪ ሊይዘው የሚገባ የሥራ ኀላፊነት ቤተ ክርስቲያን፤ "ይህ መሪ አርአያነት ያለው ፈሪሀ እግዚአብሔር የሚታይበት ሕይወት ኖሮአል" ብላ ልትመሰክርለት የምትችል መሆን አለበት። ይህን ጉዳይ በይበልጥ ለመረዳት፣ በገጽ 1925 ላይ፤ *"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**4፥16 ይህን ብታደርግ፣ ራስህንና የሚሰሙህንም ታድናለህና፤** ለጢሞቴዎስ የሚከተሉት ዝርዝሮች ከራሱ ከአገልግሎት በላይ ከፍ ብለው የሚቈጠሩ ናቸው፤ እነርሱም የቅድስና ሕይወት መኖር (ቍ 12)፣ ለመንፈስ ቅዱስ ሥራና ስጦታ ንቁ መሆን (ቍ 14)፣ ጤናማ አስተምህሮን ማስተማር (ቍ 13፥15-16)፣ ለእምነት ጠበቃ ሆኖ መቆምና (6፥20፤ 2ጢሞ 1፥13-14 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1716 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)፤ የግልን መንፈሳዊ ሕይወት መንከባከብ ናቸው። እነዚህ ጉዳዮች ለግል ድነቱና ለሚያገለግላቸው ሁሉ (ከ2ጢሞ 3፥13-15 ጋር ያነጻጽሩ) አስፈላጊ ናቸው (ይህም ለአሁኑና ለወደፊቱ ነው፤ በገጽ 1735 ላይ፣ *"ድነትን የሚገልጹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**5፥5 መበለት የሆነች ... ለጸሎትና ... ሌሊትና ቀን ትተጋለች፤** ከፍተኛ ለሆነው አገልግሎት ለጸሎት ራሳቸውን አሳልፈው የሰጡ መበለቶች ከቤተ ክርስቲያን (ቍ 3) ዕውቅናንና እርዳታን (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ) ማግኘት አለባቸው። አንድ ሰው ስለ መበለቷ ስለ ሐና፤ "ቀንና ሌሊት ከቤተ መቅደስ ሳትለይ፣ በጾምና በጸሎት የምታገለግል መበለት ሆና" (ሉቃ 2፥37) ስለ ቄየችው ልብ እንዲል ያስፈልጋል። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ ያሉትን በመለቶች፣ "የቤተ ክርስቲያን አማላጆች፣" "በር ጠባቂዎች፣" "የእግዚአብሔር መሰዊያ" ትላቸዋለች።

**5፥9 በመዝገብ ላይ አትጻፍ፤** በአፈሶን ያለች ቤተ

ደግሞም የአንድ ባል ሚስት የነበረች[a] ልትሆን ይገባል፤ [10]ልጆችን በማሳደግ፣ እንግዶችን በመቀበል፣ የቅዱሳንን እግር በማጠብ፣ የተቸገሩትን በመርዳትና ለበጎ ምግባር ሁሉ ራሷን በመስጠት በመልካም ሥራም የተመሰከረላት መሆን አለባት።

[11]ወጣት መበለቶችን ግን እንዲህ ባለው መዝገብ አትጻፋቸው፤ ምክንያቱም ሥጋዊ ፍላጎታቸው ለክርስቶስ በገቡት ቃል ላይ በሚያይልበት ጊዜ ለማግባት ይሻሉና። [12]በዚህም ፍርድን በራሳቸው ላይ ያመጣሉ፤ በመጀመሪያ የገቡትን ቃል ኪዳን አፍርሰዋልና። [13]በተጨማሪም ሥራ መፍታትንና ከቤት ቤት መዞርን ይለምዳሉ፤ ሥራ ፈት መሆን ብቻ ሳይሆን፣ የማይገባውን እየተናገሩ ሐሜተኞችና በሰው ጉዳይም ጣልቃ የሚገቡ ይሆናሉ። [14]ስለዚህ ባል የሞተባቸው ወጣት ሴቶች እንዲያገቡ፣ ልጆች እንዲወልዱ፤ ቤታቸውን እንዲያስተዳድሩ፣ ጠላትም የሚነቅፍባቸውን ነገር እንዳያገኝ እመክራለሁ። [15]በርግጥ ከዚህ በፊት አንዳንዶቹ ሰይጣንን ለመከተል ዘወር ብለዋል።

[16]አማኝ የሆነች ማንኛዋም ሴት በቤተ ሰቧ ውስጥ መበለቶች ቢኖሯት፣ ቤተ ክርስቲያን እውነተኛ መበለቶችን ብቻ መርዳት እንድትችል እርሷው ትርዳቸው እንጂ ለቤተ ክርስቲያን ሸክም እንዲሆኑ አትተዋቸው።

[17]ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ፣ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚተጉ ሽማግሌዎች ዕጥፍ ክብር ይገባቸዋል፤ [18]መጽሐፍም፣ "እያበራየ ያለውን በሬ አፉን አትሠር፤[b]" ደግሞም፣ "ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል[c]" ይላልና። [19]በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ካልተደገፈ በቀር በሽማግሌ ላይ የሚቀርብ ክስ አትቀበል። [20]ሌሎች አይተው እንዲጠነቀቁ ኀጢአት የሚሠሩትን በጉባኤ ፊት ገሥጻቸው።

[21]በእግዚአብሔርና በክርስቶስ ኢየሱስ፣ በተመረጡትም መላእክት ፊት እነዚህን ትእዛዛት ያለ አድልዎ እንድትጠብቅና አንዳች ነገር በማበላለጥ እንዳታደርግ ዐደራ እልሃለሁ።

[22]በማንም ላይ እጅ ለመጫን አትቸኩል፤ ከሌሎችም ጋር በኀጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽሕና ጠብቅ።

5፥10 ቍ16፤ ሉቃ7፥44፤ ሐሥ9፥36፤ ሮሜ12፥13፤ 1ጢሞ6፥18፤ 1ጴጥ2፥12
5፥13 ሮሜ1፥29፤ 2ተሰ3፥11
5፥14 1ቆሮ7፥9፤ 1ጢሞ6፥1
5፥15 ማቴ4፥10
5፥16 ቍ3-5
5፥17 ሐሥ11፥30፤ ፊል2፥29፤ 1ተሰ5፥12
5፥18 ዘሌ19፥13፤ ዘዳ24፥14፡15፤ 25፥4፤ ማቴ10፥10፤ ሉቃ10፥7፤ 1ቆሮ9፥7-9፥14
5፥19 ማቴ18፥16፤ ሐሥ11፥30
5፥20 ዘዳ13፥11፤ 2ጢሞ4፥2፤ ቲቶ1፥13፤ 2፥15
5፥21 1ጢሞ6፥13፤ 2ጢሞ4፥1
5፥22 መዝ18፥26፤ ሐሥ6፥6፤ ኤፌ5፥11

[b] 5፥18 ዘዳ 25፥4
[c] 5፥18 ሉቃ 10፥7

ክርስቲያን፣ ከቤተ ክርስቲያን ለነርሱ አስፈላጊ የሆነ እርዳታ ማግኘት ያለባቸው ግልጽ የሆኑ የመበለቶች ዝርዝር አላት (ዘዳ 24፥17 እና ማብ ይመ)። በአዲስ ኪዳን ዘመን ቤተ ክርስቲያን ይህን መሰል እርዳታ ሰጥታለች፤ ምክንያቱም ቤተ ሰብ ወይም ልጆች ለሌላቸው መበለቶች ርዳታ የሚያደርግ ወይም ጡረታ የሚሰጥ መንግሥት አልነበረም። መበለቶቹም የተወሰኑ መንፈሳዊ የብቃት መለኪያዎችን የሚያሟሉ መሆናቸውን (ቍ 9-10)፣ ከዚህ በተጨማሪም በመልካም ሥራና (ቍ 10) በጸሎት (ቍ 5) የበረቱ መሆናቸውን ማሳየት ነበረባቸው።

**5፥17 ቤተ ክርስቲያንን በሚገባ የሚያስተዳድሩ፣ ሽማግሌዎች፤** ይህ ጥቅስ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በሚገባ ለሚያስተዳድሩና የአማኞችንም ኑሮ ለሚንከባከቡት ሽማግሌዎች ተገቢ የሆነ ክብሬታ ስለ መስጠቱ ግድ አለው (በገጽ 1716 ላይ፡ *«የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። በስብከትና በማስተማር ረገድ ከልብ ከፍተኛ ጥረት ለሚያደርጉት (ከ1ቆሮ 15፥10፤ ከ1ተሰ 5፥12-13 ጋር ያነጻጽሩ) እጥፍ ድርብ ክብሬታ ማግኘት አለባቸው፤ ይህም (1) የገንዘብ እርዳታ በመስጠት (ከ1ቆሮ 9፥7-14 ጋር ያነጻጽሩ) እና ክርስቲያናዊ አካሄድን በተመለከተ ለእነርሱ እሽ ብሎ መገዛትን ያካትታል (ዕብ 13፥7፤ 1ጴጥ 5፥5)።

**5፥20 በጉባኤ ፊት ገሥጻቸው፤** የሽማግሌዎችን ወይም የፓስተሮችን አካሄድ (ሥነ ሥርዐት) አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቃል መርሖችን ወይም መመሪያዎችን ይሰጣል (ቍ 20-22)። ፈሪሀ እግዚአብሔር ያላቸው መሪዎች ለቤተ ክርስቲያን አስፈላጊዎች በመሆናቸው አንድ መጋቢ ፓስተር ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ኀጢአት ሠርቶ ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ የሚከተሉት ድርጊቶች በእርሱ ላይ መፈጸም አለባቸው (ቍ 19)፡ (1) ሽማግሌዎች የሌሎችን ሽማግሌዎች ኀጢአት መሸፈን ወይም ዝም ብለው ማለፍ የለባቸውም። በደል የፈጸመው ሽማግሌ እንዲገሥጽ ወይም የሥነ ሥርዐት እርምጃ እንዲወሰድበት ግዴታ ነው፤ ለተቀሩት ሽማግሌዎች ማስጠንቀቂያ (መቀጣጫ) እንዲሆንና ኀጢአትንም ለመሥራት እንዳይደፋፈር፣ የዚ ሰው በደል በጉባኤ ፊት ይፋ መሆን አለበት። (2) ሁሉም አንድ ቀን በእግዚአብሔር፣ በኢየሱስ ክርስቶስና በተመረጡት መላእክት ፊት መቅረባቸው ስለማይቀር (ቍ 21)፣ ጳውሎስ ከላይ የተጠቀሰው ቅጣት አንዱ ከአንዱ ሳይባል ወይም ያላንዳች አድልዎ መፈጸም እንዳለበት ያስጠነቅቃል።

**5፥22 እጅን ለመጫን አትቸኩል፤** የሽማግሌን መቀባት አስመልክቶ (ከ4፥14፤ ከሐስ 6፥6 ጋር ያነጻጽሩ) ጳውሎስ አንዳንድ ጉዳዮች አሉት፤ (1) ማንም ሰው ቢሆን ለዚህ ኀላፊነት በችኰላ መቀባት የለበትም፤ ይኸውም ተገቢ ጥንቃቄ መደረግና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መመሪያዎች መከበርና መጠበቅ አለባቸው (ቲቶ 1፥5 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1925 ላይ፡ *«የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት»* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። (2) አንድን ሰው ለሽማግሌነት መቀባት ማለት፣ የዚያ ሰው ሕይወት በ3፥1-7 ላይ በተመለከተው መሠረት እግዚአብሔር የደነገገውን የፈሪሀ እግዚአብሔር ጽናት መለኪያ አሟልቶአል ብሎ በጉባኤ ፊት ለቤተ ክርስቲያን ማወጅ ነው። በሌላም አገላለጽ ለመሪነት የሚቀቡት አማኞች በክርስትና የሕይወት ዘመናቸው ውስጥ ለጌታ የቱን ያህል ታማኝ እንደ ሆኑ የሚያመለክት ታሪክ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። (3) አንዲት ቤተ ክርስቲያን አንድን ሰው በቤተ ክርስቲያን ላለው አገልግሎት በችኰላ ለመሪነት ከቀባች ወይም ከሾመች፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን መመሪያ ችላ በማለት ይህን ካደረገች፣ የዚያ ሰው ኀጢአት ተባባሪ ያደርጋታል። ጳውሎስ፣ «ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» ሲል ለመጋቢነት ወይም ለፓስተርነት አገልግሎት የማይመጥነውን ሰው ከመምረጥ ወይም ከመቀባት ራስህን አድን ማለቱ ነው።

[23]ለሆድህና ደጋግሞ ለሚነሣብህ ሕመም፣ ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት እንጂ ከእንግዲህ ውሃ ብቻ አትጠጣ።
[24]የአንዳንድ ሰዎች ኀጢአት ግልጽ ነው፤ ከእነርሱም ቀድሞ ፍርድ ቦታ ይደርሳል፤ ሌሎችን ግን ኀጢአታቸው ይከተላቸዋል። [25]መልካም ሥራም እንደዚሁ ግልጽ ነው፤ ግልጽ ያልሆነ ቢኖርም እንኳ ተሰውሮ አይቀርም።

6 የእግዚአብሔር ስምና ትምህርቱም እንዳይሰደቡ፣ በባርነት ቀንበር ሥር ያሉ ሁሉ፣ ጌቶቻቸው ሙሉ ክብር እንደሚገባቸው አድርገው ይቍጠሩ። [2]የሚያምኑ ጌቶች ያሏቸውም፣ ወንድሞች ስለሆኑ የሚገባቸውን ክብር አይንፈጓቸው፤ ይልቁንም በአገልግሎታቸው የሚጠቀሙ አማኞችና ወዳጆቻቸው ስለ ሆኑ የበለጠ ሊያገለግሏቸው ይገባል። እነዚህን ነገሮች አስተምር፤ ምከርም።

## የገንዘብ ፍቅር

[3]ማንም የሐሰት ትምህርት ቢያስተምር፣ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ቃልና እውነተኛ መንፈሳዊነትን ከሚያጐለብት ትምህርት ጋር የማይስማማ ቢሆን፣ [4]ያ ሰው በትዕቢት ተወጥሮአል፤ አንዳችም አያስተውልም። ስለ ቃላት ለመከራከርና ለመጣላት ክፉ ጕጕት አለው፤ እነዚህም ቅናትን፣ ጥልን፣ ስድብን፣ መጥፎ ጥርጣሬን ያስከትላሉ፤ [5]እውነትን በተቀሙና መንፈሳዊው ነገር ትርፍ ማግኛ በሚመስላቸውና አእምሮ በጐደላቸው ሰዎች መካከል የማያባራ ንትርክ ያመጣሉ።
[6]ነገር ግን እውነተኛ መንፈሳዊነት ባለን ነገር ከመርካት ጋር ትልቅ ትርፍ ነው። [7]ምክንያቱም ወደ ዓለም ያመጣነው ምንም ነገር የለም፤ ምንም ነገር ይዘን መሄድም አንችልም። [8]ነገር ግን ምግብና ልብስ ካለን፣ ያ ይበቃናል። [9]ባለጠጋ ለመሆን የሚፈልጉ ግን ወደ ፈተናና ወደ ወጥመድ፣ እንዲሁም ሰዎችን ወደ መፍረስና ወደ ጥፋት ወደሚያዘቅጠው ወደ ብዙ ከንቱና ክፉ ምኞት ይወድቃሉ። [10]ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው፤ አንዳንዶች ባለጠጋ ለመሆን ካላቸው ጕጕት የተነሣ ከእምነት መንገድ ስተው ሄደዋል፤ ራሳቸውንም በብዙ ሥቃይ ወግተዋል።

## ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ዐደራ

[11]የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፤ አንተ ግን ከዚህ ሁሉ ሽሽ፤ ጽድቅን፣ እውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወትን፣ እምነትን፣ ፍቅርን፣

5፥23 1ጢሞ3፥8
6፥1 ኤፌ6፥5፤ 1ጢሞ5፥14፤ ቲቶ2፥5፡8
6፥2 1ጢሞ4፥11፤ ፊሞ1፥16
6፥3 1ጢሞ1፥3፡10
6፥4 1ጢሞ3፥6፤ 2ጢሞ2፥14፤ 3፥4
6፥5 2ጢሞ3፥8፤ ቲቶ1፥15
6፥6 ፊል4፥11፤ 1ጢሞ4፥8፤ ዕብ13፥5
6፥7 ኢዮ1፥21፤ መዝ49፥17፤ መክ5፥15
6፥8 ምሳ30፥8፤ ዕብ13፥5
6፥9 ምሳ15፥27፤ 28፥20፤ 1ጢሞ3፥7
6፥10 ቍ21፤ ኢሱ7፥21፤ 1ጢሞ3፥3፤ 5፥19
6፥11 ቍ3፡5፡6፤ 1ጢሞ1፥14፤ 2፥2፤ 2ጢሞ2፥22፤ 3፥10፤ 3፥17

**5፥23 ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት፤** (1) ይህ ጥቅስ በአዲስ ኪዳን ዘመን አይሁድ ይጠጡት የነበረውን የወይን ጠጅ፣ ሰውን ልምሰል በማለት ጢሞቴዎስ ያልጠጣ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው (በገጽ 1547 ላይ፣ “*የወይን ጠጅ በአዲስ ኪዳን ዘመን -1*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ):: የወይን ጠጅ መጠጣት የጢሞቴዎስ ልማድ ቢሆን ኖሮ ጳውሎስ፣ “ለጤንነትህ አስፈላጊ ስለሆነ ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣበት” በማለት መምከር ባላስፈለገው ነበር (3፥3 እና ማብ ይመ)::
(2) ጢሞቴዎስ ሆድ ሕመም ያደረበት በኤፌሶን የነበረው ውሃ፣ “አልካሊ” የተባለ ንጥረ ነገር ያለበት በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም:: ስለዚህ በዚያ ውሃ ላይ ለነበረው ንጥረ ነገር ማርከሻ ይሆን ዘንድ ጢሞቴዎስ ጥቂት የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ጳውሎስ መከረው:: በግሪክ የመድኀኒት ጽሑፍ መሠረት ሆድ እንዳያም ሲባል የሚጠጣ የወይን ጠጅ ብዙ ጊዜ የማያሰክር ነበር:: አትናቴዎስ፣ “ውሃ የገባበት ወይም ሊብ ያለ ጣፋጭ የወይን ጠጅ ይጠጣ፤ ለሆድ ተስማሚ ስለሆነ በተለይ፤ “ፓትሮስ” (ወይን ከመጨመቁ በፊት የሚወጣ ነገር ነው) የተባለውን ይጠጣ፤ ጣፋጭ የወይን ጠጅ “አይኖስ” ራስ እንዲከብድ አያደርግምና (አትናቴዎስ፣ “ባንኩዌት፣” 2፥24፤ እንዲሁም የፕሊኒዩን፣ “ናቹራል ሂስትሪ” 14፥18 ይመ)::
(3) ጢሞቴዎስ ሐዋርያው ጳውሎስ ሐሳብ እንዳይገባው በማለትና ለጤንነት ሲል ብቻ ሲያስፈልግ፣ “ጥቂት የወይን ጠጅ” ይጠጣል:: መጠጥ የማይቀምስ መሆኑ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ይህን የሚጠቀመው ለተለየ አጋጣሚ ብቻ ነው:: የመጠጥን ሱስ ለማርካት ሲባል የሚያሰክርን መጠጥ እየጠጡ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠውን ምክር ምክንያት አድርጎ ማቅረብ፣ የምንባቡን ዓላማ ማጣመም ነው::
**6፥1 በባርነት ቀንበር ሥር፤** ቈላ 3፥22 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ::
**6፥3 መንፈሳዊነትን ከሚያጐለብት ትምህርት፤** ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያልመጣ ማንኛውም መልእክት እናም ከልብ በሆነ ጥሩ መንፈሳዊነትንና ቅድስናን የማያጐለብት ከሆነ፣ በአዲስ ኪዳን ላይ ከሚገኘው ወንጌል የተለየ ወንጌል ነው::
**6፥5 አእምሮ በጐደላቸው፤** በእነዚህ ሰዎች ላይ ጢሞቴዎስ ምን ዐይነት ሚዛናዊ ፍርድ ማድረግ እንዳለበት በማሳሰብ፣ ጳውሎስ ስለ ሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ጉዳይ በድጋሚ ይመለሳል (ከምዕ 1 ጋር ያነጻጽሩ):: ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ ውጭ ለሆነው አስተምህሮ በአሁኑ ዘመን ቸልተኛ ሆኖ መገኘት ሐዋርያዊ አይደለም፤ በዚህ መልእክትና በሌሎቹ መልእክቶች የተሰጠውንም ምክር እንደ መናቅ ይቈጠራል (ከገላ 1፥9 ጋር ያነጻጽሩ)::
**6፥6 እውነተኛ መንፈሳዊነት፤** የኤፌሶን የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ብዙ ሀብትን ለማጋበስ ሲሉ ለታይታ ያህል እውነተኛ መንፈሳዊነት ያለባቸው ይመስሉ ነበር:: በስግብግብነት ይኖሩ ስለነበር፣ የሀብታቸው ብዛት እግዚአብሔር የእነርሱን ትምህርት ለመባረኩ አንድ ምልክት መሆኑን ያስተምሩ ነበር::
**6፥8 ያ ይበቃናል፤** አማኞች መሠረታዊ የሆነውን ነገር ማለትም ምግብን፣ ልብስንና መጠለያን በማግኘታቸው፣ እርካታ ይኖራቸው ዘንድ አስፈላጊ ነው:: ገንዘብ የሚጠይቅ የተለየ ነገር ቢከሠት፣ በልግስና በመስጠት እግዚአብሔርን እያገለገልን (2ቆሮ 8፥3፤ 9፥6-7)፤ እግዚአብሔር እንዲሰጠን ወደ እርሱ መመልከት ይኖርብናል (መዝ 50፥15):: ሀብታም ለመሆን መፈለግ የለብንም (ቍ 9-11)::
**6፥9 ወደ ፈተናና ... ይወድቃሉ፤** በገጽ 1577 ላይ፣ “*ብልጽግናና ድህነት*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ::

ትዕግሥትንና ገርነትን ተከታ
[12]መልካሙን የእምነት ገድል ተጋ
በብዙ ምስክሮች ፊት በመልካም መ
የመሰከርህለት ንና የተጠራህበትን የ
ሕይወት አጥብቀህ ያዝ። [13]ለ
ሕይወትን በሚሰጥ በእግዚአብሔር
እንዲሁም በጳንጥዮስ ጲላጦስ ፊት
በመሰከረ በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት
የምልህ፣ [14]ጌታችን ኢየሱስ ክ
እስኪገለጥ ድረስ፣ ይህን ትእዛ
ዕድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ እንድ ት
ነው፤ [15]ያም መገለጥ፣ የተባረከውና
ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ፣ የጌ
ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚ
ነው፤ [16]እርሱ ብቻ ኢመዋቲ ነው፤
በማይቀረብ ብርሃን ውስጥ ይኖራል፤
ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የ
የለም። ለእርሱ ክብርና ኀይል
እስከ ዘላለም ይሁን፤ አሜን።
[17]በዚህ ዓለም ባለጠጎች
እንዳይታበዩ፣ ደስም እንዲለን

1ጢሞ 4፥8

**6፥12 መልካሙን የእምነት ገድ**
“ተጋደል” የሚለው ቃል ከግሪክ
ሲሆን፣ ትርጕሙ፣ “ማውቃየት”
ጳውሎስ በክርስትና ሕይወት ውስጥ፣
አገልጋይ ለመሆን ጽናት እንደሚጠ
ጠላቶችም ጋር ከባድ ጦርነት ማካሄድ
ያለክታል:: እግዚአብሔር በፈለገው ቦታ
ቦታ) ያስቀምጠን፣ ሁላችንም ስለ ወን
ተጠርተናል (ኤፌ 6፥11-12 እና ማብ
**6፥14 እስኪገለጥ ድረስ፤** ጳውሎ
የሰጠው ምክር የክርስቶስ መገለጥ በራሱ
ሊከሠት እንደሚችል ጳውሎስ ያምን እን
ያሳያል:: የአዲስ ኪዳን ሐዋርያት በትው
የነበሩትን አማኞች በዕድሜ ዘመናቸው
ክርስቶስ ሊመጣ እንደሚችል እንዲ
እንዲያደርጉ በተደጋጋሚ አበረታታዋል
1ተሰ 1፥9-10፤ ቲቶ 2፥13፤ ዕብ 9
መውደድ ዳግም ምጻቱንና የቅጽበት
በሕይወት ዘመናችን መሠረታዊ አ
መሆን አለበት (ራእ 21፥1—22፥15 ይ
**6፥16 እርሱ ብቻ ኢመዋቲ ነው፤**
ነገር እግዚአብሔር ዘላለማዊ መሆኑ
እግዚአብሔር ከሰዎች፣ ከመላእክት፣
ወይም ከሚታይ አሊያም አካላዊ ከሆኑ
ለሕልውናው ማንም ሳያስፈልገው በ
ለዘላለም የሚኖር ኀያል አምላክ ነው (
ኢሳ 6፥1-3፤ 40፥12-26፤ 55፥8-9

# የሐዋርያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ጢሞቴዎስ - ሁለተኛ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-4)

I. ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ዐደራ (1፥5-18)
   (ሀ) የእግዚአብሔርን ስጦታ አቀጣጥል (1፥5-7)
   (ለ) ስለ ወንጌል ሥቃይ ለመቀበል ፈቃደኛ ሁን (1፥8-10)
   (ሐ) የጳውሎስ ምሳሌነት (1፥11-12)
   (መ) እውነትን ያዝ፤ ጠብቅም (1፥13-14)
   (ሠ) በሮም ታማኝና ታማኝ ያልሆኑ የጳውሎስ ወዳጆች (1፥15-18)
II. የታማኝ አገልጋይ የብቃት መለኪያዎች (2፥1-26)
   (ሀ) በጸጋ በርታ (2፥1)
   (ለ) ታማኝ ለሆኑ ሰዎች የወንጌልን መልእክት ዐደራ ስጥ (2፥2)
   (ሐ) መከራን ተቀበል (2፥3-7)
      1. እንደ በጎ ወታደር (2፥3-4)
      2. እንደ ሥነ ሥርዐት አክባሪ ሯጭ (2፥5)
      3. እንደ ትጉህ ገበሬ (2፥6-7)
   (መ) ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ሙት፤ ስለ እርሱም ሥቃይ ተቀበል (2፥8-13)
   (ሠ) ዐጕል ከሆነ ክርክር ራቅ፤ ነቀፋ በማያስከትል መልክም ስለ ወንጌል ጥብቅና ቁም (2፥14-26)
III. ድንገት እየመጣ ላይ ያለው የመጨረሻው የከፋ ሞገድ (3፥1-9)
IV. በእውነት መጽናት (3፥10-17)
   (ሀ) ከጳውሎስ በተማረው መሠረት (3፥10-14)
   (ለ) ከቅዱሳት መጻሕፍት በተማረው መሠረት (3፥15-17)
V. ቃሉን ስበክ (4፥1-5)
VI. የጳውሎስ ምስክርነትና ትምህርት (4፥6-18)
   (ሀ) የጳውሎስ የመሰነባበቻ ንግግር (4፥6-8)
   (ለ) ለጢሞቴዎስ በግሉ የተሰጠው ትምህርት (4፥9-13)
   (ሐ) የማስጠንቀቂያ ቃል (4፥14-15)
   (መ) የእግዚአብሔር ታማኝነት ማረጋገጫ (4፥16-18)

*መደምደሚያ* (4፥19-22)

**ጸሓፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ብርቱ ጽናት*

**የተጻፈበት ጊዜ፤** *በ67 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

*ታሪካዊ ዳራ*

ይህ የጳውሎስ የመጨረሻ መልእክት ነው። መልእክቱ ሲጻፍ ንጉሥ ኔሮ አማኞችን በከፋ ሁኔታ በማሳደድ በሮም የክርስትና እምነት እንዳይስፋፋ ጥረት አድርጎ ነበር። ጳውሎስ በሮም ውስጥ በድጋሚ የንጉሡ እስረኛ ሆኖአል (1፥16)። እንደ ወንጀለኛ ተቈጥሮም መብቱን

ተገፍፎ ነበር (2፥9)፤ ብዙዎቹ …
የመሞቻ ጊዜውም እየተቃረበ …
ለማወቅና ታሪካዊ ዳራን በይበል…
ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ፣ "እው…
የወንጌል ሠራተኛ በማለት ይጽ…
ያለው የጠበቀ ትስስርና በእርሱ…
ሆኖ ታይቶአል፤ ስድስቱ መልእ…
ስም መጥቀሱ፣ በመጀመሪያ እስ…
ፊሞ 1፥1) እንዲሁም ጳውሎስ …
አይቀሬው የሞት ፍርድ አፍጥ…
ሁለት ጊዜ ጥያቄ አቀረበለት (…
በጻፈበት ጊዜ፣ ጢሞቴዎስ ገና …

**ዐላማ**

ጢሞቴዎስ ፍርሃት የገባውና ች…
ውጭና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ …
ስደት ሊደርስበት የሚችል መሆ…
ጥብቅና እንዲቆም፣ ቃሉን እንዲ…
ጳውሎስ አጥብቆ ይመክረዋል።

**ቅኝት**

በምዕራፍ 1 ላይ ጳውሎስ እሁን…
፣ ጢሞቴዎስ ሳያመቻምች (መ…
እውነትን በትጋት እንዲጠብቅ …
በምዕራፍ 2 ላይ ጳውሎስ፣ ወደ…
(2፥2)፣ ኀላፊነት ሊጣልባቸው …
እምነትን ይንከባከብ ዘንድ መን…
እንዲቋቋም (2፥3)፣ እግዚአብሔ…
እንዲይዝ (2፥15)፣ ከሐዋርያዊ …
በንጽሕና እንዲጠብቅ (2፥22)፣ …
ወጣቱን መጋቢ (ሐዋርያው) ይ…
በሚቀጥለው ምዕራፍ ጳውሎስ…
ግን በጽናት ለርስቱና ለቅዱሳት …
ለጢሞቴዎስ ይነግረዋል።
በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ቃ…
ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ዐደራ ይለ…
ዘንድ በማሳሰብ፣ ጳውሎስ ከሕይ…
ያለበትን ሁኔታ ለጢሞቴዎስ በ…

**ልዩ ገጽታ**

የሁለተኛ ጢሞቴዎስን መልእክት…
(1) በደማስቅ መንገድ ጳውሎስ …
ከሆነው በኋላ፣ በሮም ከተማ በኔ…
ሐሳቡን የያዘ መልእክት ነው። (…
ዐላማ በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ግ…
ክፍሎች አንዱ ነው (3፥16-17)፤
እንዳለበት አጽንዖት ያደርጋል (…
የእግዚአብሔር ቃል ዐደራ እንዲ…
በመልእክቱ ዳር እስከ ዳር ይገኛ…
(1፥6)፣ "አትፈር" (1፥8)፤ "ስለ …
ምሳሌ አድርገህ ያዝ" (1፥13)፤ "…
(2፥1)፤ "… ዐደራ ስጥ" (2፥2)፤ …
እንደሚያስረዳ … ትጋ" (2፥15)፤ …

ተገፍፎ ነበር (2፥9)፣ ብዙዎቹ ወዳጆቹ ትተውት ሄዱ (1፥15)፣ አገልግሎቱ እያከተመ፣ የመሞቻ ጊዜውም እየተቃረበ መሆኑን ተገንዝቦ ነበር (4፥6-8፡18፣ ስለ ጸሓፊው ማንነት ለማወቅና ታሪካዊ ዳራን በይበልጥ ለመረዳት፣ የጢሞቴዎስን አንደኛ መግቢያ ይመ)።

ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ፣ "እውነተኛ ልጄ" (1፥2)፣ ታማኝ የሆነና ከጐኔ የማይለይ የወንጌል ሠራተኛ በማለት ይጽፍለታል (ከሮሜ 16፥21 ጋር ያነጻጽሩ)። ከጢሞቴዎስ ጋር ያለው የጠበቀ ትስስርና በእርሱም ላይ እምነቱን መጣሉ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ግልጽ ሆኖ ታይቶአል፤ ስድስቱ መልእክቶች ሲላኩ እርሱም ላኪ መሆኑን በማሳየት የጢሞቴዎስን ስም መጥቀሱ፣ በመጀመሪያ እስራቱ ጢሞቴዎስ ከእርሱ ጋር መገኘቱ (ፊል 1፥1፤ ቈላ 1፥1፤ ፊሞ 1፥1) እንዲሁም ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ በግሉ በጻፋቸው ሁለት መልእክቶች። ጳውሎስ አይቀሬው የሞት ፍርድ አፍጥጦበት እያለ፣ ጢሞቴዎስ ከእርሱ ጋር በሮም ከተማ እንዲገኝ ሁለት ጊዜ ጥያቄ አቀረበለት (4፥9፡21)። ጳውሎስ ይህን ሁለተኛ መልእክት ለጢሞቴዎስ በጻፈበት ጊዜ፣ ጢሞቴዎስ ገና በኤፌሶን ይገኝ ነበር (1፥18፤ 4፥19)።

### ዐላማ

ጢሞቴዎስ ፍርሃት የገባውና ችግር የገጠመው መሆኑን፣ ወደፊትም ከቤተ ክርስቲያን ውጭና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚገኙ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ዘንድ ከባድ ስደት ሊደርስበት የሚችል መሆኑን ጳውሎስ ተረድቶአል፤ ስለዚህ ጢሞቴዎስ ለወንጌል ጥብቅና እንዲቆም፣ ቃሉን እንዲሰብክ፣ ችግርን እንዲቋቋምና የተሰጠውን ዐደራ እንዲፈጽም ጳውሎስ አጥብቆ ይመክረዋል።

### ቅኝት

በምዕራፍ 1 ላይ ጳውሎስ አሁንም ጢሞቴዎስን እንደሚወደውና እንደሚጸልይለት በማረጋገጥ፣ ጢሞቴዎስ ሳያመቻምች (መስሎ መኖርን በአሻፈረኝ በመሸሽ)፣ ለወንጌል ታማኝ እንዲሆን፣ እውነትን በትጋት እንዲጠብቅ የጳውሎስንም ምሳሌ እንዲከተል ያደፋፍረዋል።

በምዕራፍ 2 ላይ ጳውሎስ፣ ወደፊት እነርሱም በበኩላቸው ሌሎችን ለሚያስተምሩት (2፥2)፣ ኀላፊነት ሊጣልባቸው ለሚቻል ለእነዚሁ ሰዎች የእምነትን እውነት በማስተላለፍ እምነትን ይንከባከብ ዘንድ መንፈሳዊ ልጁን ዐደራ ይለዋል። እንደ ብርቱ ወታደር መከራን እንዲቋቋም (2፥3)፣ እግዚአብሔርን በትጋት እንዲያገለግልና የእውነትንም ቃል በትክክል እንዲይዝ (2፥15)፣ ከሐዋርያዊ እውነት ከተለዩት ራሱን እንዲያርቅ (2፥18-21)፣ ራሱን በንጽሕና እንዲጠብቅ (2፥22)፣ እንደ መልካም መምህር በትዕግሥት እንዲሠራ (2፥23-26) ወጣቱን መጋቢ (ሐዋርያው) ይመክረዋል።

በሚቀጥለው ምዕራፍ ጳውሎስ ክፋትና ክሕደት እየጨመረ እንደሚመጣ (3፥1-9)፣ እርሱ ግን በጽናት ለርስቱና ለቅዱሳት መጻሕፍት ታማኝ መሆን እንዳለበት (3፥10-17) ለጢሞቴዎስ ይነግረዋል።

በመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ቃሉን እንዲሰብክ፣ የአገልግሎቱንም ኀላፊነት ሁሉ እንዲወጣ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ዐደራ ይለዋል (4፥1-5)። ጢሞቴዎስ በፍጥነት ወደ እርሱ ይመጣ ዘንድ በማሳሰብ፣ ጳውሎስ ከሕይወቱ የመጨረሻ ሰዓት ላይ እየደረሰ ባለበት ወቅት አሁን ያለበትን ሁኔታ ለጢሞቴዎስ በመንገር መልእክቱን ይደመድማል (4፥6-22)።

### ልዩ ገጽታ

የሁለተኛ ጢሞቴዎስን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት አምስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በደማስቆ መንገድ ጳውሎስ ወደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመልሶ፣ 35 ዓመት ገደማ ከሆነው በኋላ፣ በሮም ከተማ በኔሮ ከመገደሉ ትንሽ ቀደም ብሎ የነበረውን የመጨረሻ ሐሳቡን የያዘ መልእክት ነው። (2) ስለ መለኮታዊ እስትንፋስና ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዐላማ በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚያስረዱ ዐረፍተ ነገሮችን ከያዙት ክፍሎች አንዱ ነው (3፥16-17)፤ ጳውሎስ የእግዚአብሔር ቃል በቃሉ አገልጋዮች መተንተን እንዳለበት አጽንዖት ያደርጋል (2፥15)፤ ሌሎችን ለማስተማር ችሎታ ላላቸው ሰዎችም የእግዚአብሔር ቃል ዐደራ እንዲሰጥ ያደፋፍራል (2፥2)። (3) ዕጥር ምጥን ያሉ ምክሮች በመልእክቱ ዳር እስከ ዳር ይገኛሉ፤ ለምሳሌ፣ "የእግዚአብሔርን ስጦታ እንድታቀጣጥል" (1፥6)፣ "አትፈር" (1፥8)፣ "ስለ ወንጌል ... መከራን ተቀበል" (1፥8)፣ "የጤናማ ትምህርት ምሳሌ አድርገህ ያዝ" (1፥13)፣ "መልካሙን ዐደራ ... ጠብቅ" (1፥14)፣ "ባለው ጸጋ በርታ" (2፥1)፣ "... ዐደራ ስጥ" (2፥2)፣ "መከራን ተቀበል" (2፥3)፣ "የእውነትን ቃል በትክክል እንደሚያስረዳ ... ትጋ" (2፥15)፣ "ራቅ" (2፥16)፣ "ሽሽ ... ተከታተል" (2፥22)፣ ሊመጣ

ተዉኝ ታውቃለህ፤ ከእነርሱም መካከል
ፊሎጎስና ሄርሞጌኔስ ይገኙበታል።
[16]ጌታ ለሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን
ይስጥ፤ ምክንያቱም ብዙ ጊዜ ብርታት
አድርጎልኛል፤ በታሰርሁበትም ሰንሰለት
አላፈረም። [17]እንዲያውም ወደ ሮም በመጣ
ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ። [18]በዚያች ቀን
ምሕረትን ከጌታ ያገኝ ዘንድ ጌታ ይስጠው፤
በኤፌሶንም የቱን ያህል እንዳገለገለኝ አንተ
በሚገባ ታውቃለህ።
2 እንግዲህ ልጄ ሆይ፤ አንተ በክርስቶስ
ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ። [2]በብዙ ምስክር
ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር
ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ።
[3]እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር፣
ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል። [4]በውትድርና
የሚያገለግል ሰው አዛዡን ለማስደሰት
ይጥራል እንጂ በሌላ ሥራ ራሱን አያጠላ
ልፍም። [5]እንደዚሁም በውድድር የሚሳተፍ
ሰው፣ የውድድሩን ሕግ ጠብቆ ካልተወዳደረ
የድሉን አክሊል አያገኝም። [6]ትጉህ ገበሬም
ከሰብሉ ለመጠቀም የመጀመሪያው ሊሆን
ይገባዋል። [7]እኔ የምለውን ልብ በል፤ ጌታ
በሁሉም ነገር ማስተዋልን ይሰጥሃልና።
[8]ከሙታን የተነሣውን፣ ከዳዊት ዘርም
የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤
የእኔም ወንጌል ይኸው ነው፤ [9]ለዚህም
እንደ ወንጀለኛ እስከ መታሰር ድረስ
መከራን እየ ተቀበልሁ ነው፤ የእግዚአብሔር
ቃል ግን አይታሰርም። [10]ስለዚህ በክርስቶስ
ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር
እነርሱም ያገኙ ዘንድ፣ ለተመረጡት ስል
ሁሉንም በትዕግሥ እጸናለሁ።
[11]እንዲህ የሚለው ቃል የታመነ ነው፤
ከእርሱ ጋር ከሞትን፣
  ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት
    እንኖራለን።
[12]ብንጸና፣
  ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን።
ብንክደው፣
  እርሱ ደግሞ ይክደናል፤
[13]ታማኞች ሆነን ባንገኝ
  እርሱ ታማኝ እንደ ሆነ ይኖራል፤
  ራሱን መካድ አይችልምና።

### እግዚአብሔር የተቀበለው ሠራተኛ

[14]ስለ እነዚህ ነገሮች ማሳሰብህን አትተው፤
በቃላት እንዳይነታረኩ በእግዚአብሔር ፊት
አስጠንቅቃቸው፤ ይህ ጥቅም የሌለው፣
የሚሰሙትንም የሚያፈርስ ነውና። [15]እንደ
ማያፍርና የእውነትን ቃል በትክክል እንደ
ሚያስረዳ የተመሰከረለት ሠራተኛ፤
ራስ ህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ
ትጋ። [16]ከእግዚአብሔር ከማያስከብር ከንቱ
ልፍለፋ ራቅ፤ በዚህ ነገር የተጠመዱ
ሰዎች ከእግዚአብሔር እየራቁ ይሄዳሉና።
[17]ትምህርታቸው እንደማይሽር ቍስል
ይሠራጫል፤ ከእነዚህም መካከል
ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ይገኛሉ፤ [18]እነዚህም

1፥18 ቍ12፤ ሐሥ18፥19፤ ዕብ6፥10
2፥1 ኤፌ6፥10፤ 1ጢሞ1፥2
2፥2 1ጢሞ6፥12፤ 2ጢሞ1፥13
2፥3 ቍ9፤ 1ጢሞ1፥18፤ 2ጢሞ1፥8፤ 4፥5
2፥5 1ቆሮ9፥25
2፥6 1ቆሮ9፥10
2፥8 ማቴ1፥1፤ ሐሥ2፥24፤ ሮሜ2፥16፤ 16፥25
2፥9 ሐሥ9፥16፤ 21፥33፤ ዕብ4፥12
2፥10 2ቆሮ1፥6፤ 4፥17፤ ቈላ1፥24፤ ቲቶ1፥1፤ 1ጴጥ5፥10
2፥11 ሮሜ6፥2-11፤ 1ጢሞ1፥15
2፥12 ማቴ10፥33፤ ሮሜ8፥17፤ 1ጴጥ4፥13
2፥13 ሮሜ3፥3፤ 1ቆሮ1፥9
2፥14 ቍ23፤ 1ጢሞ1፥4፤ 6፥4፤ ቲቶ3፥9
2፥15 ኤፌ1፥13፤ ቈላ1፥5፤ ያዕ1፥18
2፥16 1ጢሞ6፥20፤ ቲቶ3፥9
2፥17 1ጢሞ1፥20 2፥18 2ተሰ2፥2፤ 1ጢሞ1፥19፤ 6፥21

ከእርሱና በምሥራቅ በኩልም ከወንጌሉ እየሸሹ ናቸው፤ በዚህም ምክንያት፣ “በእስያ አውራጃ ያሉት ሁሉ እንደ ተዉኝ ታውቃለህ” (1፥15) ብሎአል።

(1) ይህ አስከፊ ፈተና ቢገጥመውም እንኳ፣ ጳውሎስ በእግዚአብሔር ላይ የነበረውን እምነት አጥብቆ እንደ ያዘ ነበር። ክርስቶስ እውነተኛውን ወንጌልና አገልግሎቱን እንደሚጠብቅ ማረጋገጫ ተሰጥቶታል (ቍ 12)፤ ወንጌልን የሚጠብቁና የሚሰብኩ እንደ ጢሞቴዎስ ያሉ ሰዎች ምንጊዜም እንደማይታጡ (ቍ 14፤ 2፥2)፣ ሲሞትም ጌታ በመልካም ሁኔታ ወደ ሰማያዊ መንግሥቱ እንደሚወስደውም እርግጠኛ እንዲሆን ተደርጎአል (4፥6፡8፡18)።

(2) የጳውሎስ አሳዛኝ ሥቃይ ከመጨረሻው ዘመን ታማኞች መካከል የብዙዎች ዕጣ ፈንታ ይሆናል። ብዙዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን መተዋቸውን ሲያዩ (ማቴ 24፥10፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)፣ በዚህ እየገነነ ከመጣው ክፉ ዘመን መንፈስ ጋር ለመስማማት በሚፈልጉት ዘንድ አገልግሎታቸው ተቀባይነት ሲያጣ፤ ለአዲስ ኪዳን ወንጌል ታማኝ የሆኑት እነዚህም ተመሳሳይ ሐዘን ይደርስባቸዋል (4፥3-4 እና ማብ ይመ)። ጳውሎስ በሥቃይ ውስጥ ሆኖ እንደ ተገነዘበው ሁሉ፤ ብዙዎች ለአዲስ ኪዳን ወንጌል ታማኝ የሆነውን እውነተኛውን የእግዚአብሔር ልጅ ይተዉታል።

2፥2 **ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ፤** ለክርስቲያኖች እምነትን ለማስተማር የቤተ ክርስቲያን ኀላፊነት የቱን ያህል እንደ ሆነ ለመረዳት፤ በገጽ 1937 ላይ፤ “*የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

2፥3 **መከራን ተቀበል፤** ለክርስቶስና ለወንጌሉ በታማኝነት የጸኑት የወንጌል አገልጋዮች መከራን ይቀበሉ ዘንድ ጥሪ ይደረግላቸዋል (ከ1፥8፤ 2፥9፤ ከ2ቆሮ 11፥23-29 ጋር ያነጻጽሩ)። እንደ ወታደሮች በችግርና በሥቃይ ውስጥ ለማለፍ፤ ለጌታም በሙሉ ልባቸው ታማኝ በመሆን መንፈሳዊ ጦርነትን ለመዋጋት ፈቃደኞች መሆን አለባቸው (ኤፌ 6፥10-18)፤ እንደ ሯጭ መሥዋዕትነትን መቀበል ይችሉ ዘንድ ጥብቅ ሥርዐትን የሚከተል ሕይወት ለመኖር ፈቃደኞች መሆን አለባቸው (ቍ 5)፤ እንደ ገበሬዎች ለከባድ ሥራና ለረጅም ሰዓት አገልግሎት ራሳቸውን የሰጡ መሆን አለባቸው (ቍ 6)።

2፥12 **ብንጸና፤** የሚጸኑትና (በግሪክ፤ “ሃፐሜኖ”) እስከ መጨረሻው በእምነት የሚበረቱት ይኖራሉ (ከ1፥ ከማቴ 10፥22፤ 24፥13 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ከክርስቶስም ጋር ይነግሣሉ (4፥18፤ ራእ 20፥4)። የማይጸኑትንና ክርስቶስን በቃል ወይም በተግባር ጌታቸው የማያደርጉትን በፍርድ ቀን ክርስቶስ የእኔ አይደላችሁም ይላቸዋል (ከማቴ 10፥33፤ 25፥1-12 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1962 ላይ፣ “*ክሕደት*” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

2፥13 **ታማኝ እንደ ሆነ ይኖራል፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ ጥርጥር ለእኛ የገባልንን ተስፋ ይፈጽምልናል (ከማቴ 10፥32 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ማስጠንቀቂያውንም ተግባራዊ ያደርጋል (ማቴ 10፥33)። መለኮታዊ ታማኝነት ቃሉን አክብረው ለሚኖሩት መጽናኛ ሲሆን (1ተሰ 5፥24፤ 2ተሰ 3፥3፤ ዕብ 10፥23)፣ ከእምነት ለሚርቁት ደግሞ ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው። እግዚአብሔር ለቃሉ ምንጊዜም ታማኝ ነው (2ሳሙ 7፥28፤ ኤር 10፥10፤ ቲቶ 1፥2፤ ራእ 3፥7)።

# የክርስቲያኖች

*2ጢሞ 2፥2 “በብዙ ምስ*
*ላላቸው ለታመኑ ሰዎች*

ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳት መ
ሐዋርያዊ አስተምህሮ ለመጠ
ኀላፊነት አለባት። ይህም በ
እንዳለበት በእንድምታ መልክ
(1) በቤት፣ በቤተ ክርስቲ
መለኮት ትምህርት ለምን መ
ያቀርባል፤
(ሀ) የክርስቶስን ወንጌል
ይኸውም ትክክለኛውን መጽ
የሆነውን መመዘኛ (ሮሜ 6፥
ኤር 2፥8 እና ማብ ይመ)፤ እ
ለማድረግ ነው (ሮሜ 6፥17 እ
(ለ) “ለቅዱሳን ለአንዴና ለ
ይመ) የቱን ያህል አስፈላጊ
ሥነ መለኮት እምነታቸውን የ
ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4
ላይ፤ “የሐሰት ትምህርት አስ
(ሐ) ተማሪዎችን፣ እውነተ
ረገድ ዘላቂ እድገት ይኖራቸ
ከመዝ 1፥2-3፤ 119፥97-100፤
እና ማብ፤ 4፥7፡16፤ ከ2ጢሞ
(መ) ተማሪዎች ሌሎችን
ዘንድ፣ ይኸውም የክርስቶስን
ውስጥ ያንጸባርቁ ዘንድ ለማስ
(ሠ) ተማሪዎች በምድር ላይ
ተሞክሮአቸውም እንዲያደርጉ፣
ሆነ እንዲረዱ ለማድረግ ነው (
መንግሥት” በሚል ርእስ የቀረ
(ረ) ለጠፉት በመንፈስ ቅ
ዘንድ (ማቴ 28፥18-20፤ ማር
ተማሪዎችን በዘላለማዊው የወን
(ሰ) ተማሪዎች በአዲስ ኪዳን
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስ
ጋር ያላቸውን ግላዊ ኅብረት፣
ስፋና ጥልቅ ተመክሮቻቸው እን
ያደረሙን የመንፈስ ቅዱስን
ይጠመቁ ዘንድ በማምጣትና
ቅዱስ መጠመቅ” በሚል ርእ
(ማቴ 6፥9 እና ማብ ይመ)፤
በማስተማር ነው።
(2) ከእነዚህ መጽሐፍ ቅዱ
መስጠት ያለበት ቅዱሳት
መሆናቸውን (2ጢሞ 1፥13-1
“መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔ
የትኩረት ጽሑፍ ይመ) በሚ

# የክርስቲያኖች የመጽሐፍ ቅዱስ ሥልጠና

*2ጢሞ 2፥2 "በብዙ ምስክር ፊት ከእኔ የሰማኸውን፣ ሌሎችን ለማስተማር ብቃት ላላቸው ለታመኑ ሰዎች ዐደራ ስጥ።"*

ቤተ ክርስቲያን በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኘውን እውነትና ከመጀመሪያ የተሰጠውን ሐዋርያዊ አስተምህሮ ለመጠበቅ፣ ያላንዳች ማመቻመችና ብክለት ለሌሎች ዐደራ የመስጠት ኀላፊነት አለባት። ይህም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት መኖር እንዳለበት በእንድምታ መልክ ያሳያል።

(1) በቤት፣ በቤተ ክርስቲያን ወይም በትምህርት ቤት የመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ሥነ መለኮት ትምህርት ለምን መስጠት እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ የሚከተሉትን ምክንያቶች ያቀርባል፤

(ሀ) የክርስቶስን ወንጌል ታማኝ ለሆኑ ክርስቲያኖች (አማኞች) ዐደራ ለመስጠት ነው፤ ይኸውም ትክክለኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትና (1ጢሞ 4፥6፡11፤ 2ጢሞ 2፥2) ጻድቅ የሆነውን መመዘኛ (ሮሜ 6፥17 እና ማብ፤ 1ጢሞ 6፥3) እንዲያውቁት (2ጢሞ 3፥15፤ ኤር 2፥8 እና ማብ ይመ)፣ እንዲጠብቁትና (2ጢሞ 1፥14 እና ማብ ይመ) እንዲያስተምሩት ለማድረግ ነው (ሮሜ 6፥17 እና ማብ፤ 1ጢሞ 6፥3 ይመ)።

(ለ) "ለቅዱሳን ለአንዴና ለመጨረሻ ስለ ተሰጠው እምነት" መጋደል (ይሁ 1፥3 እና ማብ ይመ) የቱን ያህል አስፈላጊ እንደ ሆነ ለተማሪዎች ለማሳየትና ከማንኛውም ዐይነት የሐሰት ሥነ መለኮት እምነታቸውን የሚከላከሉበትን መሣሪያ ለመስጠት ነው (ሐሥ 20፥31 እና ማብ፤ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ፤ 6፥3-4፤ ቲቶ 1፥9 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ "የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(ሐ) ተማሪዎችን፣ እውነተኛ መንፈሳዊነትን በሚያጐለብት ትምህርት አማካይነት፣ በጠባይ ረገድ ዘላቂ እድገት ይኖራቸው ዘንድ ለመምራት ነው (1ጢሞ 6፥3 ይመ፤ ከኢያ 1፥8፤ ከመዝ 1፥2-3፤ 119፥97-100፤ ከማቴ 28፥20፤ ከዮሐ 17፥14-18፤ ከ1ተሰ 4፥1፤ ከ1ጢሞ 1፥5 እና ማብ፤ 4፥7፡16፤ ከ2ጢሞ 3፥16 ጋር ያነጻጽሩ)።

(መ) ተማሪዎች ሌሎችን አማኞች ማበረታታትና ወደ እድገት ደረጃም ማምጣት ይችሉ ዘንድ፣ ይኸውም የክርስቶስን ምሳሌነት በቤት፣ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያንና በክርስቶስ አካል ውስጥ ያንጸባርቁ ዘንድ ለማስታጠቅ ነው (ኤፌ 4፥11-16)።

(ሠ) ተማሪዎች በምድር ላይ ያለችውን የእግዚአብሔር መንግሥት በጥልቀት እንዲያስተውሉና ተሞክሮአቸውም እንዲያደርጉ፣ ከሰይጣንም ጋር የምታደርገው ፍልሚያ የቱን ያህል ከባድ እንደ ሆነ እንዲረዱ ለማድረግ ነው (ኤፌ 6፥10-18 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1443 ላይ፣ "የእግዚአብሔር መንግሥት" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)።

(ረ) ለጠፉት በመንፈስ ቅዱስ ኀይል ወንጌልን ያደርሱና ለሕዝቡም ሁሉ ይሰብኩት ዘንድ (ማቴ 28፥18-20፤ ማር 16፥15-20)፣ ራሳቸውን በሙሉ በሙሉ አሳልፈው እንዲሰጡ ተማሪዎችን በዘላለማዊው የወንጌል እውነት አማካይነት ለማነሣሣት ነው።

(ሰ) ተማሪዎች በአዲስ ኪዳን ቅዱሳን መንፈሳዊ ሕይወት ጥልቀት ልክ (2ጢሞ 4፥8፤ ቲቶ 2፥13)፣ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን የክብር መገለጥ ሲናፍቁ ሳለ፣ የክርስቶስን ፍቅር፣ ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግላዊ ኅብረት፣ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታ (ዮሐ 17፥3፡21፡26፤ ኤፌ 3፥18-19) ሰፊና ጥልቅ ተመክሯቸው እንዲሆን ለማገዝ ነው፤ ይህም ሊሳካ የሚችለው፣ በእነርሱ ውስጥ ያደረውን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት እንዲከተሉ በማነሣሣት (ሮሜ 8፥14)፣ በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቁ ዘንድ በማምጣትና (ከሐሥ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1664 ላይ፣ "በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) እንዲሁም እንዲጸልዩ (ማቴ 6፥9 እና ማብ ይመ)፣ እንዲጾሙና (ማቴ 6፥16 እና ማብ ይመ)፣ እንዲያመልኩ በማስተማር ነው።

(2) ከእነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሥልጠና ዐላማዎች ለማየት እንደሚቻለው፣ ትምህርቱ መሰጠት ያለበት ቅዱሳት መጻሕፍት ሙሉ በሙሉ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለባቸው መሆናቸውን (2ጢሞ 1፥13-14፤ ዕዝ 7፥10 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1941 ላይ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ) በሚያምኑና ለመንፈስ ቅዱስ እንዲሁም ለእውነት፣ ለጽድቅና ለኀይል

አገልግሎቱ (1፥14) ታማኝ በሆኑ ወገኖች ብቻ መሆኑ የታወቀ ነው።

(3) ትክክለኛ የሆነው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥልጠና ግልብ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀት ወይም እውነት ይልቅ ትክክለኛ በሆነው ጽድቅ ላይ ትኩረት ያደርጋል (ይኸውም ማወቅ፣ መሆንና መፈጸም ነው)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተገለጡት ታላቅ አስተምህሮች ምሁራዊ ሳይሆኑ ቤዛዊ እውነቶች ናቸው። ከሕይወት ወይም ከሞት ጋር የተሳሰሩ ጉዳዮች እንደመሆናቸው መጠን፣ ከአስተማሪውም ሆነ ከተማሪዎች ግላዊ አጸፋንና ውሳኔን ይጠይቃሉ (ያዕ 2፥17 ይመ፡ ፊል 1፥9 እና ማብ ይመ)።

...ቀ ነው።
...ገልብ ከሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ...ላይ ትኩረት ያደርጋል (ይኸውም ...ተ የተገለጡት ታላቅ አስተምህሮች ...ይም ከሞት ጋር የተሳሰሩ ጉዳዮች ...ግላዊ አጸፋንና ውሳኔን ይጠይቃሉ



ከእውነት ርቀው የሚባዝኑ ናቸው። እነርሱም ትንሣኤ ሙታን ከዚህ በፊት ሆኖአል እያሉ የአንዳንዶቹን እምነት ይገለብጣሉ። 19ይሁን እንጂ፣ "ጌታ የእርሱ የሆኑትን ያውቃል፤" ደግሞም፣ "የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከክፋት ይራቅ" የሚል ማኅተም ያለበት የማይናቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል።

20በአንድ ትልቅ ቤት ውስጥ የወርቅና የብር ዕቃ ብቻ ሳይሆን፣ የዕንጨትና የሸክላ ዕቃም ይኖራል፤ ከእነዚህ አንዳንዶቹ ለክበረ፣ ሌሎቹም ላልከበረ አገልግሎት ይውላሉ። 21እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ከጠቀስኳቸው ነገሮች ቢያነጻ ለክቡር አገልግሎት የሚውል፣ የተቀደሰ፣ ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ ይሆናል።

22ከወጣትነት ክፉ ምኞት ሽሽ፤ በንጹሕ ልብ ጌታን ከሚጠሩት ጋርም ጽድቅን፣ እምነትን፣ ፍቅርንና ሰላምን ተከታተል። 23ከማይረባና ትርጒም የለሽ ከሆነ ክርክር ራቅ፤ ምክንያቱም እነዚህ ጠብን እንደሚያስከትሉ ታውቃለህ። 24የጌታም አገልጋይ ሊጣላ አይገባውም፤ ይልቁን ለሰው ሁሉ ገር፣ ለማስተማር ብቃት ያለው፣ ትዕግሥተ ኛም መሆን ይገባዋል፤ 25እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፣ እግዚአብሔር ንስሓን እንደሚ ሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቃና መሆን ይኖርበታል፤ 26ይኸውም ወደ አእምሮአቸው ይመለሳሉ፤ ፈቃዱን ሊያስፈጽማቸው ምርኮኛ አድርጎ ከያዛቸው ከዲያብሎስ ወጥመድም ያመልጣሉ በማለት ነው።

2፥19 ዘኁ16፥5፤ ኢሳ28፥16፤ ዮሐ10፥14፤ 1ቆሮ1፥2፤ 8፥3፤ ገላ4፥9
2፥20 ሮሜ9፥21
2፥21 2ቆሮ9፥8፤ ኤፌ2፥10፤ 2ጢሞ3፥17
2፥22 ሐሥ2፥21፤ 1ጢሞ1፥5፤14
2፥23 ቍ14
2፥24 1ጢሞ3፥2፤3
2፥25 1ጢሞ2፥4
2፥26 1ጢሞ3፥7
3፥1 1ጢሞ4፥1፤ 2ጴጥ3፥3
3፥2 ሮሜ1፥30፤ 1ጢሞ3፥3፤ 2ጴጥ2፥10-12

## ክሕደት በመጨረሻዎቹ ቀናት

3 ነገር ግን በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ እንደሚመጣ ይህን ዕወቅ። 2ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉ፤ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክሕተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ 3ፍቅር የሌላቸው፣ ለዕርቅ የማይሸነፉ፣ ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን

**2፥19 የማይናቃነቅ ... መሠረት ቆሞአል፤** ብዙዎች ከእውነት ርቀው የሚባዝኑ ቢሆኑም (ማቴ 24፥11)፣ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ገብተው ቢሸለኩሉም (ቍ 14-18)፣ እግዚአብሔር ለታማኞቹ ያለው ዐላማ አይደናቀፍም። «የማይናቃነቅ የእግዚአብሔር መሠረት» ይኸውም እውነተኛዋ ቤተ ክርስቲያን ልትጠፋ ከቶ አትችልም። የክርስቶስ ቤተ ክርስቲያን አባላት የሆኑትን በተመለከተ፣ በዚሁ መሠረት ላይ ሁለት እውነቶች ተጽፈዋል፤ (1) እግዚአብሔር ከመጀመሪያ ለሰጠው ወንጌል ታማኝ የሆኑትንና እውነቱን የሚያመቻምቹትን ያላንጻቸ ግድፈት ያውቃል (ከዘፍ 18፥19፤ ከዘፀ 33፥12፤17፤ ከዘኍ 16፥5፤ ከ1ቆሮ 8፥1-3 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ደግሞም (2) በእውነት የእግዚአብሔር የሆኑት ደግሞ ከክፋትና ከሐሰት ትምህርት ይርቃሉ (ከ1ጢሞ 6፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥21 ራሱን ... ቢያነጻ፤** በዐይነ ሥጋ በምትታየው፣ በምድርም ላይ በምትገኘው በእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ፣ «ዕቃዎች» ይገኛሉ። ለክበረ ዐላማ የቆሙ ይኸውም በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ መሠረት እውነተኛውን ወንጌል በርትተው የያዙ ከክፋው ራሳቸውን ያራቁ ታማኝ ክርስቲያኖች በአንድ በኩል ሲኖሩ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከእውነት ርቀው በመንከራተት፣ ራሳቸውን ለወራዳ ዐላማ አሳልፈው የሰጡ አስመሳይ አማኞችች ይገኛሉ (ቍ 14-19)። ታማኝ ከሆኑት መካከል ለጌታ ጠቃሚ ባሪያ ለመሆን የሚፈልጉ ሁሉ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር የማይጣጣመውን አስተምህሮ ዐቅፈው ከሚገኙት አማኞች ነን ባዮች ከማንኛውም ዐይነት እምነት ራሳቸውን ማራቅ አለባቸው (ቍ 19)። ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን አስተምህሮ ከያዙት ጋር ግንኙነት ሊኖር የሚችለው፣ በፍቅር እነርሱን ለማስተካከልና ንስሓ ገብተው ወደ እውነት እንዲመለሱ ለማድረግ ብቻ መሆን አለበት (ቍ 25)።

**3፥1 በመጨረሻው ዘመን የሚያስጨንቅ ጊዜ፤** የመጨረሻው ዘመን ሙሉውን የክርስትና ዘመን ያካትታል፤ ይሁን እንጂ ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ (ከ1ጢሞ 4፥1 ጋር ያነጻጽሩ)፣ የመጨረሻው ጊዜ እየተቃረበ ሲመጣ ነገሮች የባሰውን እየተበላሹ እንደሚመጡ ተንብዮአል (ከ2ጴጥ 3፥3፤ ከ1ዮሐ 2፥18፤ ከይሁ 1፥17-18 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) የመጨረሻው ዘመን በዓለም ውስጥ እየገነነ በሚሄድ ክፋት፣ በግብረገባዊ ዕብቃት መለኪያ እየዘቀጠ መምጣት፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ በሐሰተኛ አማኞችና በሐሰተኛ አብያተ ክርስቲያናት መበርከትና መስፋፋት ተለይቶ ይታወቃል (ማቴ 24፥11-12 ይመ፤ 1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1913 ላይ፣ «*የሐሰተኛው ክርስቶስ ዘመን*» በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። እነዚህ ወቅቶች ለእግዚአብሔር እውነተኛ ባሪያዎች በተለየ ሁኔታ አሳዛኝና ፈታኝ ይሆናሉ።

(2) ጳውሎስ እነዚህን ማስጠንቀቂያዎች የሰጠው ለክርስቶስና ለመገለጡ ታማኝ የሆኑትን አገልጋዮችንና አብያተ ክርስቲያናቸውን የማይበገሩ ምሽጎች ለማድረግ ነው። በክርስቶስ ሙሉ የሆነው የድኅነት በረከትና የመንፈስ ቅዱስ በኀይል መውረድ እውን የሚሆነው ለአዲስ ኪዳን እምነትና ልምምድ ምንጊዜም ታማኝ በመሆን ለጸኑት ነው። አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ክሕደት ውስጥ ገባች ማለት ለቅዱሳን ለተሰጠው የመጀመሪያ እምነት ታማኝ ሆነው ለጸኑት የላቀ ጸጋና ኀይል ይበዛላቸዋል ማለት ነው (ሐሥ 4፥33፤ ሮሜ 5፥20፤ ይሁ 1፥3)።

**3፥2 ራሳቸውን የሚወዱ፤** ራስን ከመውደድ የተነሣ የሚመነጨውን ኀጢአት ጳውሎስ ይዘረዝራል (ቍ 2-4)። ዛሬ አንዳንዶች ራስን አለመውደድ የኀጢአት ምንጭ ነው በማለት ያስተምራሉ፤ ሐዋርያዊ መገለጥ ግን የዚህን የተዛባ ትምህርት ተቃራኒ ያስተምራል።

**3፥3 ፍቅር የሌላቸው፤** አማኞች በመጨረሻው ዘመን ከማምት በላይ የሆነ ክሕደት ሊከሠት እንደሚችል በመገንዘብ ከወዲሁ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። (1) ሰይጣን በቤተ ሰብ ላይ ታላቅ ጥቃት እንደሚያመጣ ሐዋርያው ይተነብያል። ልጆች፣ «ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ» ይሆናሉ (ቍ 2)፤ ወንዶችና ሴቶችም ፍቅር አልባ ይሆናሉ፤ ይህ ሐሳብ በግሪክ ቋንቋ «አስቶርጎይ» በሚል ቃል የተቀመጠ ሲሆን፣ «የቤተ ሰብ ፍቅር የሌላቸው» ተብሎ ሊተረጐም ይችላል፤ ይኸውም ተፈጥሮአዊ

የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በከንቱ
በትዕቢት የተወጠሩ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ
ተድላን የሚወዱ ይሆናሉና። [5]ሃይማኖታዊ
ቲቶ 2፥11- መልክ አላቸው፤ ኀይሉን ግን ክደዋል።
12 ከእነዚህ ራቅ።

[6]እነርሱም በየቤቱ ሾልከው እየገቡ
የኀጢአት ብዛት የተጫናቸውን፣ በተለያየ
ክፉ ምኞት ውስጥ ገብተው የሚዋልሉ
መንፈሰ ደካማ ሴቶችን የሚያጠምዱ ናቸው፤
[7]እንደነዚህ ያሉ ሴቶች ሁልጊዜ ይማራሉ፤
ነገር ግን እውነትን ወደ ማወቅ ፈጽሞ
ሊደርሱ አይችሉም። [8]ኢያኔስና ኢያንበሬስ
ሙሴን እንደ ተቃወሙት፣ እነዚህም
አእምሮአቸው የጠፋባቸውና ከእምነት
የተጣሉ ሰዎች ደግሞ እውነትን ይቃወማሉ።
[9]ይሁን እንጂ አይሳካላቸውም፤ ምክንያቱም
የእነዚያ ሰዎች ሞኝነት እንደ ተገለጠ ሁሉ፣
የእነዚህም ለሁሉ ግልጽ ይሆናል።

### ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የሰጠው ዐደራ

[10]አንተ ግን ትምህርቴን፣ አካሄዴን፣
ዐላማዬን፣ እምነቴን፣ ትዕግሥቴን፣
ፍቅሬንና፣ ጽናቴን ሁሉ ታውቃለህ፤
[11]ስደቴንና መከራዬን፣ በአንጾኪያና
በኢቆንዮን፣ በልስጥራንም የደረሰብኝን
ሁሉ፣ የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤
ጌታ ግን ከእነዚህ ሁሉ አዳነኝ። [12]በርግጥም
በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ
ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።
[13]ክፉዎችና አታላዮች ግን እየሳቱና እየሳቱ፣
በክፋትም ላይ ክፋት እየጨመሩ ይሄዳሉ።
[14]አንተ ግን በተማርኸውና በተረዳኸው ጽና፤
ይህን ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤
[15]ከሕፃንነትህም ጀምረህ፣ በክርስቶስ ✝
ኢየሱስ በማመን መዳን የሚገኝበትን ጥበብ
ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን ቲቶ
በውቀሃል። [16]ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ 3፥5-7
የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤
ለማስተማር፣ ለመገሥጽ፣ ለማቅናት
በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤
[17]ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም
ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ" ነው።

3፥4 መዝ25፥3፤ 1ጢሞ3፥6፤ 6፥4
3፥5 ሮሜ16፥17፤ 1ጢሞ2፥2
3፥6 ይሁ1፥4
3፥7 1ጢሞ2፥4
3፥8 ዘፀ7፥11፤ ሐሥ13፥8፤ 1ጢሞ6፥5
3፥9 ዘፀ7፥12፤ 8፥18፤ 9፥11
3፥10 1ጢሞ4፥6
3፥11 መዝ34፥19፤ ሐሥ13፥14:51፤ 14፥6፤ ሮሜ15፥31፤ 2ቆሮ11፥23-27
3፥12 ሐ15፥20፤ ሐሥ14፥22
3፥13 ማር13፥5፤ 2ጢሞ2፥16
3፥14 2ጢሞ1፥13
3፥15 ዘዳ4፥6፤ መዝ119፥98:99፤ ዮሐ5፥39፤ 2ጢሞ1፥5
3፥16 ዘዳ29፥29፤ ሮሜ4፥23:24፤ 2ጴጥ1፥20
3፥17 1ጢሞ6፥11፤ 2ጢሞ2፥21

ርኅራኄንና ፍቅርን ማጣት ሲሆን፣ ቤተ ሰቡን ረስቶ በሚኖር አባት፣ ወይም ዕድሚ የተጫናቸውን ወላጆች መንከባከብን ችላ ባሉት ልጆች አማካይነት ጕልሕ ሆኖ ሊታይ ይችላል (ሉቃ 1፥17 እና ማብ ይመ)።

(2) ወንዶችና ሴቶች ገንዘብንና ደስታን የሚያሳድዱ በመሆን፣ ራስ ወዳድነት ያለበትን ስሜታቸውን ማርካት ዐላማቸው ያደርጋሉ (ቊ 2)። መሥዋዕትነት ያለበትን ፍቅርንና እንክብካቤን የሚጠይቀው ወላጅነት ከግዴታው ጋር የሚጠቅም ወይም የሚያስከብር ተግባር ተደርጎ ከእንግዲህ የማይቈጠር ይሆናል (ቊ 2-4)። ለልጅ ፍቅርን የሚያሳዩት ወላጆች ራሳቸውን በሚወዱ፣ በጨካኞች፣ ልጆቻቸውን ለችግር በሚዳርጉ ወላጆች ይተካሉ (ከመዝ 113፥9፤ 127፥3-5፤ ከምሳ 17፥6፤ ከቲቶ 2፥4-5 ጋር ያነጻጽሩ፤ 2ጢሞ 4፥3-4 እና ማብ ይመ)።

(3) ክርስቲያን ወላጆች ከመጨረሻው ዘመን አስቸጋሪ ወቅት ቤተ ሰቦቻቸውን ለማዳን ከፈለጉ፣ ከሚኖሩበት ኅብረተ ሰብ የተበከለ ዕሴት ይጠብቋቸው ዘንድ ግዴታ አለባቸው (ዮሐ 21፥15-17፤ ሐሥ 20፥28-30)፤ ልጆቻቸውን ከዓለም መንገድ መለየት ይኖርባቸዋል፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር አልባ የሆነውም ነገር በልጆቻቸው ሕይወት ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር የመጣር ግዴታ አለባቸው (ሐሥ 2፥40፤ ሮሜ 12፥1-2 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1826 ላይ፣ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። እግዚአብሔር ለዚያ ቤተ ሰብ ያለውን ዕቅድ መቀበልም ግዴታቸው ነው (ኤፌ 5፥21-25 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1894 ላይ፣ *"ወላጆችና ልጆች"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ ፈሪሀ እግዚአብሔር የሌላቸው ሰዎች እንደሚኖሩትም መኖር የለባቸውም (ዘሌ 18፥3-5፤ ኤፌ 4፥17)። እነርሱና ቤተ ሰቦቻቸው በምድር ላይ በርግጥ እንግዶችና መጻተኞች መሆን አለባቸው (ዕብ 11፥13-16)።

**3፥5 ሃይማኖታዊ መልክ አላቸው፤** ከዚህ ላይ ጳውሎስ የሚያመለክተው ከኀጢአት፣ ከራስ ወዳድነትና ከኢግብረገባዊነት ነጻ የሚያደርገውን የእግዚአብሔርን ኀይል የማያሳዩትን፣ ሆኖም ሃይማኖተኛ የሚመስሉትንና ክርስቲያን ነን የሚሉትን ሰዎች ነው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች በቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥ ኢግብረገባዊነትን ችላ ይላሉ፤ አንድ ሰው በቊ 2-4 የተዘረዘረውን ኀጢአት ሁሉ ቢፈጽምም፣ ድነትንና የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርስ ይችላል በማለት ያስተምራሉ (ከዮ 5-9፤ 4፥3-4፤ ከ2ጴጥ 3፥12-19 ጋር ያነጻጽሩ፤ 1ቆሮ 6፥9 እና ማብ ይመ)።

**3፥8 እውነትን ይቃወማሉ፤** የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙ ጊዜ ተለይተው የሚታወቁት፣ የወንጌልን ዐይነተኛ እውነት በመቃወማቸው ወይም ለዚሁ እውነት ደንታ ቢስ በመሆናቸው ነው (1ጢሞ 4፥1 እና ማብ ይመ)።

**3፥12 በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት ... ይሰደዳሉ፤** በክርስቶስ ኢየሱስ ሆነው በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ፣ በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ስደት ይደርስባቸዋል (ማቴ 5፥10-12፤ 10፥22፤ ሐሥ 14፥22፤ ፊል 1፥29፤ 1ጴጥ 4፥12፤ ማቴ 5፥10 እና ማብ ይመ)። ለክርስቶስ፣ ለእውነቱና ለጽድቅ መንገዱ ተገዥ መሆን፣ እምነታችንን ላለማመቻመች የዘወትር ቊርጠኝነትን ይጠይቃል፤ ወይም ከዓለም ጋር ተስማምተን እንድንኖር የሚጠራንና የቅዱሳት መጻሕፍትን እውነት ወደ ጐን እንድንተው የሚያስተጋባውን ድምፅ ንቆ መተውን ይፈልጋል። ታማኝ የሆኑት እውነተኛ የሆነውን መንፈሳዊ ሕይወት ስለሚለማመዱ፣ ሊያገኙት የሚገባቸውን ሰብአዊ መብት ያጣሉ፤ መገፊያ መሣለቂያም ይሆናሉ። እውነተኛው መንፈሳዊ ሕይወት በብዙኀኑ ሲተዉ ሐዘን ይገባቸዋል። እንግዲያውስ፣ "በእውነተኛ መንፈሳዊ አካሄድ በመሄዴ ስደት ደርሶብኛልን?" ወይም፣ "ሥቃይ ውስጥ አለመግባቴ፣ በስደት ሕይወት ውስጥ አለማለፌ፣ ክርስቶስ ለሞተለት ጽድቅ በጽኑ ባለመቆሜ ይሆን እንዴ?" ብለን ሁላችንም ራሳችንን መጠየቅ ይኖርብናል።

**3፥16-17 ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤** ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆንና ሥልጣን፣ ሰፊ ሐተታ ሰፍሮ የሚገኘው በገጽ 1941 ላይ፣ *"መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆንና ያለው ሥልጣን"* በሚለው ርእስ ሥር ነው።

## መጽሐፍ ቅዱ
## መሆኑና ያ

*2ጢሞ 3፥16-17 "ቅዱስ*
*ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለ*
*ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእ*
*እንዲገኝ ነው።"*

በ2ጢሞ 3፥16 ላይ፣ "ቅዱሳት
መጻሕፍት ነው (3፥15)። ይሁን
የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም፣ "የ
ተቈጥረው ነበር (1ጢሞ 5፥1
ለእኛ፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት" ሲ
መጻሕፍት የሚያመለክት ሲሆ
ነው። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍ
እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ለ
(1) ጳውሎስ ቅዱሳት መ
አረጋገጠ፤ (በግሪክ፤ "ቲዎኔወስ
የመጀመሪያው ቃል፣ "ቲዎስ"
ማለት ደግሞ፣ "እፍ ማለት"
የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው
ትንቢት ቃል ሕጸጽ አልባ፣ ፈ
ቅዱስ ትክክለኛ ሆኖ የሚገኘው
ሲናገር ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ሌላው
እንከን አልባ ነው (ከ2ጴጥ 1፥20
ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን
(2) የብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች
የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል
እንዲሁም በገጽ 1009 ላይ፣
ጽሑፍ ይመ)። ነቢያት ያቀረቡ
የሚለውን ሐረግ በተደጋጋሚ
(3) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራ
ር መንፈስ ያለበት መሆኑ አስተ
እውነት መሆኑን አረጋገጠ (ዮሐ
በኩል (ዮሐ 16፥13 ይመ፤ ከ
መገለጥም (ይኸውም በአዲስ ኪ
(4) መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በ
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
ዮሐ 10፥35) የመንፈስ ቅዱስን
የሐዋርያትን (2ጢሞ 3፥16፤ 2
በተጨማሪም ሕጸጽ አልባነቱ በ
ሥልጣን ላይ ጕዳት ማድረስ ማ
(5) እግዚአብሔር ሥራው
ሳይገፍ፣ ያለግድፈት ይጽፉ ዘንድ
1ቆሮ 2፥12-13 እና ማብ ይመ)
(6) የእግዚአብሔር መንፈስ
መገለጫ በመሆኑ፣ በክርስቶስ ለ
(ማቴ 4፥4፤ ዮሐ 6፥63፤ 2ጢሞ
(7) መጽሐፍ ቅዱስ ሕጸጽ አ

# መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር እስትንፋስ መሆኑና ያለው ሥልጣን

*2ጢሞ 3፥16-17 "ቅዱስ መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፥ ለማቅናት፤ በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፥ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።"*

---

በ2ጢሞ 3፥16 ላይ፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት" ሲባል በቀድሚያ የሚያመለክተው የብሉይ ኪዳንን መጻሕፍት ነው (3፥15)። ይሁን እንጂ ጳውሎስ ሁለተኛ ጢሞቴዎስን በጻፈበት ጊዜ አንዳንድ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትም፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸውና" ሥልጣን ያላቸው ተብለው ተቈጥረው ነበር (1ጢሞ 5፥18፥ ሉቃ 10፥7ን፣ 2ጴጥ 3፥15-16ን ይጠቅሳል)። ዛሬ ግን ለእኛ፣ "ቅዱሳት መጻሕፍት" ሲባል ሙሉ ሥልጣን ያላቸውን የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳንን መጻሕፍት የሚያመለክት ሲሆን፥ ይኸውም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ" በሚል ስም የሚታወቀውን ነው። እነዚህ ቅዱሳት መጻሕፍት ለሰው ከእግዚአብሔር በቀጥታ የተሰጡ መልእክት ናቸው፤ እግዚአብሔር ሰውን ለማዳን ለሚያከናውነው ተግባርም ሕጸጽ አልባ የሆኑ ምስክሮች ናቸው።

(1) ጳውሎስ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ "የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው" መሆናቸውን አረጋገጠ፥ (በግሪክ፣ "ቲዎኔወስቶስ" ነው፥ ይህም ቃል ከሁለት የግሪክ ቃላት የተገኘ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ቃል፣ "ቲዎስ" ነው፤ ትጒሙም "እግዚአብሔር" ማለት ሲሆን፣ "ኒዎ" ማለት ደግሞ፣ "እፍ ማለት" ነው)። ቅዱስ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚያሳይና የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው። ከመጀመሪያው፥ ቅዱስ መጽሐፍ ላይ የሚገኘው እያንዳንዱ ትንባት ቃል ሕጸጽ አልባ፣ ፈጽሞ እውነት የሆነ፥ አስተማማኝ እንከን አልባ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛ ሆኖ የሚገኘውም ስለ ድነት፣ ስለ ሥነ ምግባራዊ ዕሴትና ስለ ግብረገባዊነት ሲናገር ብቻ ሳይሆን፣ ስለ ሌላው ርእስ ጒዳይ ሁሉ ማለትም ስለ ታሪክና ስለ ዓለማት ሲናገርም እንከን አልባ ነው (ከ2ጴጥ 1፥20-21 ጋር ያነጻጽሩ፥ እንዲሁም መዝሙረኛው በመዝ 119 ላይ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ያለውን አመለካከት ይመ)።

(2) የብሉይ ኪዳን ጸሓፊዎች ለሕዝቡ የተናገሩትና በጽሑፍ ላይ ያሰፈሩት ሐሳብ ለሕዝቡ የተሰጠ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ተገንዝበው ነበር (ዘጸ 18፥18፥ 2ሳሙ 23፥2 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1009 ላይ፥ "ነቢይ በብሉይ ኪዳን" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። ነቢያት ያቀረቡትን የእግዚአብሔር ሐሳብ፣ "እግዚአብሔር የሚለው ይህ ነው" የሚለውን ሐረግ በተደጋጋሚ ቀዳሚ አድርገውት ይገኛል።

(3) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር ጒዳይ እንኳ ሳይቀር የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መሆኑ አስተምሯል (ማቴ 5፥18)። የተናገረውም ሁሉ ከአብ የተቀበለውና እውነት መሆኑን አረጋገጠ (ዮሐ 5፥19፡30-31፥ 7፥16፥ 8፥26)። ከመንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት በኩል (ዮሐ 16፥13 ይመ፥ ከ14፥16-17፤ 15፥26-27 ጋር ያነጻጽሩ) ወደፊት ስለሚመጣው መገለጥም (ይኸውም በአዲስ ኪዳን ላይ የተገለጠው እውነት ማለት ነው) አክሎ ተናገረ።

(4) መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መሆኑን መካድ ማለት የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን (ማቴ 5፥18፤ 15፥3-6፥ ሉቃ 16፥7፥ 24፥25-27፡44-45፥ ዮሐ 10፥35) የመንፈስ ቅዱስን (ዮሐ 15፥26፥ 16፥13፥ 1ቆሮ 2፥12-13፤ 1ጢሞ 4፥1) እና የሐዋርያትን (2ጢሞ 3፥16፥ 2ጴጥ 1፥20-21) ምስክርነት ወደ ጐን መተው ማለት ነው። በተጨማሪም ሕጸጽ አልባነቱ፥ በዐጭሩ መወሰን ወይም አቅልሎ ማየት ማለት በቃሉ መለኮታዊ ሥልጣን ላይ ጒዳት ማድረስ ማለት ነው።

(5) እግዚአብሔር ሥራው በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሲሠራ ሳለ፣ የጸሐፊዎችን ማንነት ሳይገፍ፣ ያለግድፈት ይጽፉ ዘንድ በእነርሱ ላይ ተንቀሳቀሰ (2ጢሞ 3፥16፥ 2ጴጥ 1፥20-21፤ 1ቆሮ 2፥12-13 እና ሚክ ይመ)።

(6) የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔር ጥበብና ባሕርይ መገለጫ በመሆኑ፥ በክርስቶስ ለሚያምኑ ሁሉ ጥበብንና መንፈሳዊ ሕይወትን መስጠት ይችላል (ማቴ 4፥4፥ ዮሐ 6፥63፥ 2ጢሞ 3፥15፥ 1ጴጥ 2፥2)።

(7) መጽሐፍ ቅዱስ ሕጸጽ አልባ የሆነ፣ እግዚአብሔር የሰውን ዘር በክርስቶስ ኢየሱስ ለማዳን

ለሚሠራው ሥራ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ምስክር ነው። በዚህም ምክንያት መጽሐፍ ቅዱስ ተወዳዳሪ የማይገኝለት፣ ለዘላለሙ ፍጻሜ ያገኘ፣ በተለየ ሁኔታ ሊታዘዙት የሚገባ መጽሐፍ ነው። ምንም ዐይነት የሰው ዘር ቃሎች ወይም የሃይማኖት ቤት ተቋማት ዐዋጆች ከእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን ጋር ከቶ ተተካካይ ሊሆኑ አይችሉም።

(8) አስተምህሮዎች፣ ትርጓሜዎች፣ ትንታኔዎች፣ ማብራሪያዎችና ወጎች ሁሉ በቅዱሳት መጻሕፍት ቃል መልእክት ሊመዘኑና ተቀባይነት ሊኖራቸው ይገባል (ዘዳ 13፥3 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1519 ላይ፣ "የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(9) ከሕይወትና ከእውነተኛ መንፈሳዊነት ጋር በተያያዘ ነገር ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ዋነኛ ባለሥልጣን ተደርጎ ተቀባይነት እንዲያገኝ፣ እንዲታመንና ትእዛዙ እንዲፈጸም ግዴታ ነው (ማቴ 5፥17-19፤ ዮሐ 14፥21፤ 15፥10፤ 2ጢሞ 3፥15-16 ይመ፤ ዘፀ 20፥3 እና ማብ ይመ)። ለማስተማር፣ ለመገሠጽ ለማስተካከልና በጽድቅ አኗኗር ረገድ ዕውቀትን ለማስጨበጥ ሁሉ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የመጨረሻ ባለሥልጣን መሆንና ሥራ ላይ መዋል አለበት (2ጢሞ 3፥16-17)። አንድ ክርስቲያን የመጨረሻ ባለሥልጣኚ ነው ብሎ ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ካልተገዛ በቀር፣ ለክርስቶስ ጌትነት ሊገዛ አይችልም (ዮሐ 8፥31-32፡37)።

(10) መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረውን መረዳት የምንችለው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ትክክለኛ የሆነ ግንኙነት ሲኖረን ብቻ ነው። ቃሉ የሚለው ምን ማለት እንደ ሆነ እንረዳ ዘንድ አእምሯችንን የሚከፍትልን፣ በውስጥ ሰውነታችንም የቃሉን ሥልጣን እንድንቀበል የሚያደርገው እርሱ ነው (1ቆሮ 2፥12 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1782 ላይ፣ "ሦስት ዐይነት ሰዎች" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(11) በሕይወታችን የሚገኘውን የኀጢአት ኀይል፣ ሰይጣንንና ዓለምን ለማሸነፍ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበትን ቃል መጠቀም ይኖርብናል (ማቴ 4፥4፤ ኤፌ 6፥12፡17፤ ያዕ 1፥21)።

(12) መጽሐፍ ቅዱስ ለጠፋውና በሞት አፋፍ ላይ ለሚገኘው ዓለም ብቸኛ እውነት አድርገው በሚያዩት በቤተ ክርስቲያን አባላት ሁሉ ዘንድ እንዲወደድ፣ ዋና ሀብት ተደርጎ እንዲቈጠርና ጥበቃ እንዲደረግለት ያስፈልጋል። ለሚሰጠው ትምህርት በታማኝነት በመገዛት፣ አዳኝ የሆነውን መልእክቱን በማወጅ፣ ታማኝ ለሆኑ ሰዎች እንዲያስተምሩ ዐደራ በመስጠት፣ ዘላለማዊ የሆነውን እውነቱን ከሚያጣምሙ ወይም ለማጥፋት ጥረት ከሚያደርጉ በመከላከል፣ አስተምህሮውን አክብረን መጠበቅ ይኖርብናል (ፊል 1፥16፤ 2ጢሞ 1፥13-14 እና ማብ፤ 2፥2፤ ይሁ 1፥3 ይመ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ማንም አንዳች ነገር ሊጨምር ወይም ከእርሱ ሊቀንስ አይችልም (ዘዳ 4፥2 እና ማብ፤ ራእ 22፥19 እና ማብ ይመ)።

(13) በመጨረሻም ሕጸጽ አልባ እስትንፋስ እግዚአብሔር ነው ሲባል የሚመለከተው የቅዱሳት መጻሕፍትን የመጀመሪያ ጽሑፍ ነው፤ ስለዚህ አንድ ሰው በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ስሕተት የሚመስል ነገር ቢያጋጥመው፣ ጸሐፊው የሠራው ስሕተት ነው ብሎ ከሚያስብ ይልቅ፣ ስሕተት መስሎ የታየው ነገር በሦስት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል ልብ ማለት ይኖርበታል፤ (ሀ) አሁን በእጅ የሚገኘው የመጀመሪያው ጽሑፍ ቅጅ ሙሉ በሙሉ ትክክል ላይሆን ይችላል፤ (ለ) የአሁኑ ዘመን የዕብራይስጥም ሆነ የግሪክ ትርጒም ጽሑፍ ስሕተት ሊሆን ይችላል፤ ወይም (ሐ) የአንድ ሰው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ ወይም አተረጓጐም ብቃት አልባ ወይም ትክክል ላይሆን ይችላል።

4 በእግዚአብሔር ፊት እንዲሁም በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ ባለው በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት፣ መገለጡንና መንግሥቱን በማሰብ ይህን ዐደራ እልሃለሁ፤ ²ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም። ³ምክንያቱም ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማ ይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል፤ ከዚህ ይልቅ ለገዛ ምኞቶቻቸው የሚስማማውን፣ የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ። ⁴እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ፤ ወደ ተረትም ዘወር ይላሉ። ⁵አንተ ግን በሁኔታዎች ሁሉ የረጋህ ሁን፤ መከራን ታገሥ፤ የወንጌል ሰባኪን ተግባር አከናውን፤ አገልግሎትህን ፈጽም።

⁶እኔ እንደ መጠጥ ቍርባን መሥዋዕት ለመፍሰስ ተቃርቤአለሁ፤ ተለይቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል። ⁷መልካሙን

4፥1 ቍ 8፡ ሐሥ 10፥42፡ 1ጢ.ሞ 5፥21፡ 6፥13፡14
4፥2 ገላ 6፥6፡ 1ጢ.ሞ 4፥13፡ 5፥20፡ ቲቶ 1፡ 13፡ 2፡ 15
4፥3 ኢሳ 30፥10፡ 1ጢ.ሞ 1፥10
4፥4 1ጢ.ሞ 1፥4
4፥5 ሐሥ 21፥8፡ ኤፌ 4፥11፡ 2ጢ.ሞ 1፥8፡ 2፥3
4፥6 ዘኍ 15፥1-12፡ 28፥7፡24፡ ፊል 1፥23፡ 2፥17
4፥7 ሐሥ 20፥24፡ 1ቆሮ 9፥24፡ 1ጢ.ሞ 1፥18

**4፥3-4 ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት፤** በቤተ ክርስቲያን የታሪክ ዘመን ሁሉ አንዳንዶች ትክክለኛ የሆነውን አስተምህሮ አክብሮ ለመያዝ ምንጊዜም እንቢተኞች ሆነዋል፤ የመጨረሻው ዘመን እየተቃረበ ሲመጣ ደግሞ ሁኔታው እየባሰበት ይሄዳል (ከ3፥1-5፡ ከ1ጢሞ 4፥1 ጋር ያነጻጽሩ)። (1) "ሰዎች ትክክለኛ የሆነውን ትምህርት የማይቀበሉበት ጊዜ ይመጣል" (ቍ 3)። ብዙዎች ክርስቲያኖች ነን ይላሉ፤ በቤተ ክርስቲያን ይሰበሰባሉ፡ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ይመስላሉ፡ ነገር ግን የመጀመሪያውን ሐዋርያዊ እምነት፣ ቅድስና ከሌላው ሕይወት እንዲለዩ የሚያዘውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግዴታ መቀበልና መጠበቅ አይፈልጉም (3፥5 ይመ፤ ከሮሜ 1፥16 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1826 ላይ፡ *"የአማኞች መለየት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

(2) "እውነትን ከመስማት ጆሮአቸውን ይመልሳሉ" (ቍ 4)፡ በእግዚአብሔር ሰው የሚቀርበው ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በብዙዎች ዘንድ ከእንግዲህ ሰሚ ጆሮ አያገኝም። ለእውነት ጆሮባቸውን የሰጡት ሰዎች፣ እውነተኛው ወንጌል ከሚጠይቀው ግዴታ አንሶ የሚገኘውን ስብከት ይሻሉ (ከ2፥18፡ 3፥7-8፤ ከ1ጢ.ሞ 6፥5፤ ከቲቶ 1፥14 ጋር ያነጻጽሩ)። የእግዚአብሔር ቃል ስለ ንስሓ፣ ስለ ኀጢአት፣ ስለ ኵነኔ የሚያስጠነቅቀውን እንዲሁም ስለ ቅድስናና ከዓለም ስለ መለየት አስፈላጊነት የሚናገረውን አሜን ብለው አይቀበሉትም (ከ3፥15-17፡ ከኤር 5፥31፤ ከሕዝ 33፥32 ጋር ያነጻጽሩ)።

(3) "የሚያሳክክ ጆሮአቸው ሊሰማ የሚፈልገውን እንዲነግሯቸው በዙሪያቸው ብዙ አስተማሪዎችን ይሰበስባሉ" (ቍ 3)፡ እነዚህ አማኞች ነን ባዮች የእግዚአብሔር ቃል በሚያዘው መሠረት መጋቢዎችን አይፈልጉም (ከ1፥13-14፤ ከ1ጢ.ሞ 3፥1-10 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ነገር ግን ከግል የልብ ፍላጎታቸውና ከዓለማዊ መሻታቸው ጋር የሚስማሙትን መጋቢዎች ይፈልጋሉ። የንግግር ስጦታና የማዝናናት ችሎታ ያላቸውን፣ ኀጢአተኛ ተፈጥሮ በሚሻቸው መሠረት እየኖሩ ሳለም፣ "የክርስትና ሕይወታችሁ እንከን አልባ ነው" (ከሮሜ 8፥4-13፤ ከ2ጴጥ 2 ጋር ያነጻጽሩ) ብለው የሚነግሯቸውን ሰባኪዎች ይመርጣሉ።

(4) ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆኑትንና ለቃሉም የሚገዙትን ሁሉ ከጽድቅ የተነሣ ስደትና ሥቃይ ሊደርስባቸው እንደሚችል መንፈስ ቅዱስ ያስጠነቅቃል (3፥10-12፡ ማቴ 5፥10-12)። ከዚህም በላይ በድንት ሬገድ የእግዚአብሔርን ኀይል ከማይቀበሉትና፣ ከዓለም ጋር አስማምቶ የሚኖር ሰላም ያለውን ስብከት ከሚሰብኩ ሰዎች፣ አብያተ ክርስቲያናትና ተቋማት ራሳቸውን መለየት አለባቸው (3፥5፡ ገላ 1፥9 እና ማብ፤ 1ጢ.ሞ 4፥1-2፡ 2ጴጥ 2፥1፡ ይሁ 1፥3፡ ራእ 2፥24)። ለአዲስ ኪዳን ወንጌልና ይህ ለሚሰብኩ የእግዚአብሔር ታማኝ አገልጋዮች ምንጊዜም ታዛዦች መሆን ይገባናል። ይህንኑ በማድረጋችን ከክርስቶስ ጋር የጠበቀ ኅብረት ሊኖረን እንደሚችል (ራእ 3፥20-22)፣ ከኬታም ዘንድ የመታደስ ወቅት ሊመጣልን እንደሚችል መተማመኛ ማግኘታችን አይቀርም (ሐሥ 3፥19-20)።

**4፥4 እውነትን፤** የተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል ለእውነትና ለልምምድ ዋነኛ ወይም ዐቢይ መመሪያችን መሆን አለበት። (1) በመንፈስ ቅዱስ የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ የምናምነውንና የምንፈጽመውን ለመመዘን በቂና ሙሉ መመሪያ አድርገን መጠቀም ይኖርብናል። (2) በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ አስተምህሮን፣ ልምምድን ወይም አዲስ እውነትን ጥብቅ በሆነ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጽደቂያ ሳያረጋግጡ፡ በስሜት ዐዘል ተመክሮ፣ በታምራት፣ በስኬት፣ ሰውን በአማከለ ዐሳብ ወይም በሰው ሠራሽ ትውፊ መሠረት ይበጅ ብሎ መያዝ፣ ሰይጣን በመጨረሻው የክሕደት ዘመን ከሚጠቀምባቸው ዐበይት የማታለያ መሣሪያዎች አንዱ ነው (ማቴ 24፥5፡11 እና ማብ፤ 2ተሰ 2፥11 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1471 ላይ፣ *"ታላቁ መከራ"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

**4፥7 መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤** ሐዋርያው ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ክብር ሲል አሳልፎ የሰጠውን ሕይወቱን ሲገመግም፣ ሞት አይቀሬ መሆኑን በመገንዘብ (ቍ 6)፡ ክርስቲያናዊ ሕይወቱን በሚከተሉት አገላለጾች ያቀርባል፡ (1) የክርስትና ሕይወትን ሊጋደሉለት የሚገባ ብቸኛ የተጋድሎ ሕይወት አድርጎ ይቈጥረዋል፡ ከሚከተሉትም ጋር ተዋግቶአል፤ ከሰይጣን ጋር (ኤፌ 6፥12)፣ ከአይሁድ እምነትና ከጣዖት አምልኮ መቍ ፎ ልማድ ጋር (ሐሥ 14፥19፤ 20፥19፤ ገላ 5፥1-6)፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካለ ሥራን ገድፎ በእምነት ላይ ከሚያተኩር ትምህርትና ከኢግብረገባዊ ትምህርት ጋር (3፥5፡ 4፥3፡ ሮሜ 6፤ 1ቆሮ 5፥1፤ 6፥9-10፤ 2ቆሮ 12፥20-21)፣ ከሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ጋር (ቍ 3-5፤ ሐሥ 20፥28-31፡ ሮሜ 16፥17-18)፣ ወንጌልን አጣመው ከሚያቀርቡት ጋር (ገላ 1፥6-12)፡ ከዓለማዊነት ጋር (ሮሜ 12፥2)፡ እንዲሁም ከኀጢአት ጋር (ሮሜ 6፡ 8፥13፤ 1ቆሮ 9፥24-27)። (2) በከባድ ፈተናና ውጥረት ውስጥ በማለፍ ሩጫውን ጨርሶአል፤ ከሕይወት ዘመኑም ጌታውና አዳኙ ለሆነው ለኢየሱስ ክርስቶስ በታማኝነቱ ጸንቶአል (ከ2፥12፤ ከዕብ 10፥23፤ 11፡ 12፥1-2 ጋር ያነጻጽሩ)። (3) ወዳጆቹ ብቻውን ትተውትና የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ተቃውመውት ከባድ ፈተና፣ ከዐቅም በላይ የሆነ ተስፋ መቍረጥና ችግር ቢደርስበትም እንኳ፡ ከእምነቱ

ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤
ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ። 8ወደ ፊት
የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፤ ይህንም
ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያ ቀን ለእኔ
ይሰጠኛል፤ ደግሞም ለእኔ ብቻ ሳይሆን፣ ቲቶ
የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ ነው። 2፥13

### የጳውሎስ ማሳሰቢያ

9ቶሎ ወደ እኔ ለመምጣት የተቻለህን
ሁሉ አድርግ፤ 10ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ፣
ትቶኝ ወደ ተሰሎንቄ ሄዶአልና። ቄርቂስ
ወደ ገላትያ፣ ቲቶ ወደ ድልማጥያ ሄደዋል፤
11ከእኔ ጋር ያለው ሉቃስ ብቻ ነው። ማርቆስ
በአገልግሎቴ ስለሚረዳኝ ከአንተ ጋር ይዘኸው
ና። 12ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ልኬዋለሁ።
13ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ
የተውሁትን በርኖስ፣ ጥቅልል መጻሕፍቱን
በተለይም የብራና መጻሕፍቱን አምጣልኝ።
14አንጥረኛው እስክንድሮስ ብዙ ጉዳት
አድርሶብኛል፤ ጌታ ግን የእጁን ይሰጠዋል።
15መልእክታችንን እጅግ ተቃውሞአልና፣
አንተም ከእርሱ ተጠንቀቅ።
16በተከሰስሁበት ነገር የመጀመሪያ
መከላከያዬን ሳቀርብ ማንም ሊያግዘኝ
አልመጣም፤ ነገር ግን ሁሉ ትተውኝ
ሄዱ። ይህንም አይቍጠርባቸው። 17ነገር
ግን መልእክቱ በእኔ አማካይነት በሙላት
እንዲሰበክና አሕዛብ ሁሉ እንዲሰሙት
ጌታ በአጠገቤ ቆሞ አበረታኝ፤ ከአንበሳም
መንጋጋ አዳነኝ። 18ጌታ ከክፉ ነገር ሁሉ
ያድነኛል፤ ወደ ሰማያዊው መንግሥቱም
በሰላም ያደርሰኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ
ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

### የስንብት ሰላምታ

19ለጵርስቅላና[u] ለአቂላ፣ ለሄኔሲፎሩም
ቤተ ሰዎች ሰላምታ አቅርብልኝ። 20ኤርስጦስ
በቆሮንቶስ ቀርቶአል፤ ጥሮፊሞስም ስለ
ታመመ በሚሊጢን ትቼዋለሁ። 21ከክረምት
በፊት እዚህ ለመምጣት የተቻለህን አድርግ።
ኤውግሎስና ጱዴስ እንዲሁም ሊኖስ፣
ቅላውዲያና ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ
ያቀርቡልሃል።
22ጌታ ከመንፈስህ ጋር ይሁን። ጸጋ
ከእናንተ ጋር ይሁን።

4፥8 1ቆሮ9፥25፤ ቈላ1፥5፤ 1ጢሞ6፥14፤ 2ጢሞ1፥12፤ 1ጴጥ1፥4
4፥9 ቍ21፤ ቲቶ3፥12
4፥10 ሐሥ16፥6፤ 17፥1፤ 2ቆሮ2፥13፤ ቈላ4፥14፤ ፊሞ1፥24፤ 1ዮሐ2፥15
4፥11 ሐሥ12፥12፤ ቈላ4፥14፤ ፊሞ1፥24፤ 2ጢሞ1፥15
4፥12 ሐሥ18፥19፤ 20፥4
4፥13 ሐሥ16፥8
4፥14 መዝ28፥4፤ 109፥20፤ ሐሥ19፥33፤ ሮሜ2፥6፤ 12፥19፤ 1ጢሞ1፥20
4፥16 ሐሥ7፥60
4፥17 1ሳሙ17፥37፤ መዝ22፥21፤ ዳን6፥22፤ ሐሥ9፥15፤ 23፥11፤ 1ቆሮ15፥32፤
4፥17 ፊል4፥13 4፥18 ቍ1፤ መዝ121፥7፤ ሮሜ11፥36፤ 2ጴጥ2፥9 4፥19 ሐሥ18፥2፤ 2ጢሞ1፥16
4፥20 ሐሥ19፥22፤ 20፥4፣15፣17፤ 21-29
4፥21 ቍ9፤ ቲቶ3፥12 4፥22 ገላ6፥18፤ ቈላ4፥18

[u]4፥19 ግሪኩ «ርስ» ይላል።

አልተነቃነቀም። ከእግዚአብሔር ከመጀመሪያው የተሰጠውን የወንጌልን እውነት ከቶ ለድርድር አላቀረበም (1፥13-14፤ 2፥2፤ 3፥14-16፤ 1ጢሞ 6፥12)።

**4፥8 የጽድቅ አክሊል፤** ጳውሎስ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስና ፀደራ ለተሰጠው ወንጌል ታማኝ ሆኖ በመጽናቱ፣ የእግዚአብሔር ፍቅር የተሞላበት "የጽድቅ አክሊል" በሰማይ የተዘጋጀለት መሆኑን መንፈስ ቅዱስ ራሱ መሰከረለት። እምነትን በጽድቅ ለጠበቁት ሁሉ እግዚአብሔር በሰማይ ሽልማትን አዘጋጅቶላቸዋል (ከማቴ 19፥27-29፣ ከ2ቆሮ 5፥10 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥8 የእርሱን መገለጥ ለናፈቁ ሁሉ፤** የአዲስ ኪዳን ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስ ከዚህ ምድራዊ ሕይወት አላቆ ከእርሱ ጋር ለዘላለም ያኖራቸው ዘንድ ተመልሶ ለመምጣቱ ከፍተኛ ናፍቆት አላቸው (1ተሰ 4፥13-18 ይመ፤ ከፊል 3፥20-21፤ ከቲቶ 2፥13 ጋር ያነጻጽሩ፤ በገጽ 1907 ላይ፣ "*ንጥቀት*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)። የእግዚአብሔር ሰዎች በዚህ ዓለም እስካሉ ድረስ ይህን ዓለም ቤቴ ነው ብለው አለመኖራቸውና ሰማያዊ ቤታቸውን በናፍቆት መጠባበቃቸው ጉልሕ መታወቂያቸው ነው (ዕብ 11፥13-16)።

**4፥17 ጌታ በአጠገቤ ቆሞ፤** በክርስቲያኖች ላይ በሮም ከተማ ውስጥ የከፋ ስደት ደርሶ ስለ ነበር፣ በታማኝነቱ ከጸናው ከታወቀው ሐዋርያ ጋር (ቍ 16)፣ አንድ አካል ሆኖ ለመታየት የሚፈልግ ሰው አልነበረም። ጳውሎስ በእጅጉ ተስፋ ቈርጦና የመገለል ስሜት ደርሶበት ነበር። ነገር ግን በዚህ ወቅት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ ሲያበረታታው የጌታን ህልዎት ተመክሮው አደረገ (ከሐሥ 23፥11፤ 27፥23፤ ከሮሜ 4፥20፤ ከ2ቆሮ 1፥3-5፤ ከኤፌ 6፥10፤ ከፊል 4፥13 ጋር ያነጻጽሩ)።

**4፥22 ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፤** ጳውሎስ በሮም እስር ቤት ውስጥ ሆኖ ሰማእትነትን ለመቀበል በሚጠባበቅበት ጊዜ፣ የተናገራቸው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ተመዝግበው የሚገኙት የመጨረሻ ቃላቱ እነዚህ ናቸው። ከዓለም እይታ አንጻር ሲታይ፣ የጳውሎስ ሕይወት አሳዛኝ በሆነ ኢስኬታማነት ሊደመደም ተቃርቦአል፤ (1) ለሠላሳ ዓመት ሙሉ ለክርስቶስ ሲል ሁሉን ነገር ትቶአል፤ የዚህ ዓለም ኑሮ አልተሳካለትም ነበር ማለት ነው። በገዛ ወገኖቹ እንዲሰደድና እንዲጠላ ከመሆን በቀር የተረፈው ምድራዊ ነገር ቢኖር እጅግ ጥቂት ነው። የእርሱ ስብከት አያሌ አብያተ ክርስቲያናት እንዲመሠረቱ አድርጎአል፤ ይሁን እንጂ ከእነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ብዙዎቹ ለእርሱና ለሐዋርያት እምነት ታማኝነታቸውን እያጐደሉ ነበር (1፥15)። በዚህ ጊዜ ደግሞ ከሉቃስ በቀር ሁሉም ወዳጆቹ ትተውት ሄደው በእስር ቤት ሆኖ (ቍ 11፡16)፣ ሞትን በመጠባበቅ ላይ ነው። እነዚህ ሁኔታዎች ተደማምረው ሲታዩ፣ በአሕዛብ ዘንድ የነበረው የወንጌል አገልግሎት ከንቱ ሆኖ የቀረ ያስመስላሉ። ነገር ግን ለመስቀሉ ሲል በአያሌ መንፈሳዊ ጦርነት ውስጥ ያለፈውና ብዙ የተጋደሎ ጠባሳ ያለበት ሐዋርያ፣ ለጌታ ሲል ሕይወቱን ለመስጠት በዝግጅት ላይ ሳለም ምንም ፀፀት አይሰማውም ነበር።

(2) ዛሬ 200.000 ዓመት በኋላ የጳውሎስ የወንጌል ሥራ አስተዋፅኦ፣ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ከነበሩት የእግዚአብሔር ባሪያዎች አስተዋፅኦ ሁሉ የላቀ ነው። የእርሱ ጽሑፎች ወሳኝ የሆኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ናቸው፤ ስፍር ቍጥር የሌላቸውን ወገኖችንም በክርስቶስ ያምኑ ዘንድ አብቅተዋል። ለክርስቶስ ታማኝ ሆኖ የጸና ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ሲል ያከናወነው ነገር ትንሽ መስሎ ቢታይም፤ የሥራውን ፍሬ ሞት በፀጭና አስቀርቶታል ብሎ ማሰብ የለበትም። እግዚአብሔር ታማኝ ባሪያው ያከናወነውን ሥራ ወስዶ እኛ ልናስበው ከምንችለው በላይ ወይም ተስፋ ካደረግነው በላይ ዕጥፍ ድርብ ያደርገዋል። ያልተሳካልን የመሰለው ነገር እንኳ፣ ወደፊት ሌሎች በብዛት የሚያጭዱት የመኸር ዘር ሊሆን ይችላል (ዮሐ 4፥37-38)።

# የሐዋር…

# መልእ…

*አስተዋፅኦ*


*መግቢያ* (1፥1-4)
I. ሽማግሌዎችን ስለ …
(ሀ) በየከተማው ሽ…
(ለ) ሽማግሌዎችን …
1. በግል ሕይ…
(ሀ)
(ለ)
(ሐ)
(መ)
(ሠ)
(ረ)
(ሰ)
(ሸ)
(ቀ)
(በ)
(ተ)
(ቸ)
(ኀ)
(ነ)
(ኘ)
2. በቤተ ሰብ …
(ሀ)
(ለ)
(ሐ)
II. የሐሰት ትምህርት …
(ሀ) ጠባያቸው (1፥10…
(ለ) ባሕርያቸው (1፥1…
(ሐ) መስተካከያቸው …
III. በአብያተ ክርስቲያናት …
(2፥1-15)
(ሀ) የትምህርቱ ስፋት…
(ለ) የትምህርቱ …
(ሐ) የቲቶ ኀላፊነት (…
IV. መልካም ሥራን በተ…
(ሀ) ለሌሎች መታየት…
(ለ) ለእኛ የተገለጠ…
(ሐ) የሚጠቅመውንና …
*መደምደሚያ* (3፥12-15)


**ጸሐፊ፤ ጳውሎስ**

**ዋና ሐሳብ፤ ጤናማ …**

# የሐዋርያው የጳውሎስ መልእክት ወደ ቲቶ

*አስተዋፅኦ*

*መግቢያ* (1፥1-4)

I. ሽማግሌዎችን ስለ መሾም የተሰጠ መመሪያ (1፥5-9)
- (ሀ) በየከተማው ሽማግሌዎችን መሾም (1፥5)
- (ለ) ሽማግሌዎችን ለመሾም የተሰጡ ልዩ ልዩ መንቀሻዎች (1፥6-9)
  1. በግል ሕይወት ረገድ
     - (ሀ) ነቀፋ የሌለበት (1፥6)
     - (ለ) እምነት የሚጣልበት ኤጲስ ቆጶስ (1፥7)
     - (ሐ) የማይነቀፍ (1፥7)
     - (መ) ግልፍተኛ ያልሆነ (1፥7)
     - (ሠ) ሰካራም ያልሆነ (1፥7)
     - (ረ) የማይጨቃጨቅ (1፥7)
     - (ሰ) ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የማይሮጥ (1፥7)
     - (ሸ) እንግዳ ተቀባይ (1፥8)
     - (ቀ) በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ (1፥8)
     - (በ) ራሱን የሚገዛ (1፥8)
     - (ተ) ቅን (1፥8)
     - (ቸ) ቅዱስና ጠንቃቃ (1፥8)
     - (ኀ) በታመነ ቃል የሚጸና (1፥9)
     - (ነ) ሌሎችን የሚያበረታታ (1፥9)
     - (ኘ) ጤናማውን ትምህርት የሚቃወሙትን ሊወቅስ የሚችል (1፥9)
  2. በቤተ ሰብ ረገድ
     - (ሀ) የአንዲት ሚስት ባል (1፥6)
     - (ለ) አማኞች የሆኑ ልጆች ያሉት (1፥6)
     - (ሐ) ልጆቹ በመዳራት ወይም ባለመታዘዝ ስማቸው የማይነሣ (1፥6)

II. የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን በተመለከተ የተሰጠ መመሪያ (1፥10-16)
- (ሀ) ጠባያቸው (1፥10)
- (ለ) ባሕርያቸው (1፥11-12)
- (ሐ) መስተካከያቸው ምን እንደ ሆነ (1፥13-16)

III. በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ስለሚገኙት ልዩ ልዩ ወገኖች የተሰጠ መመሪያ (2፥1-15)
- (ሀ) የትምህርቱ ስፋት (2፥1-10)
- (ለ) የትምህርቱ መሠረት (2፥11-14)
- (ሐ) የቲቶ ኀላፊነት (2፥15)

IV. መልካም ሥራን በተመለከተ የተሰጠ ምክር (3፥1-11)
- (ሀ) ለሌሎች መታየት ያለበት የእኛ ጠባይ (3፥1-2)
- (ለ) ለእኛ የተገለጠው የእግዚአብሔር ምሕረት (3፥3-7)
- (ሐ) የሚጠቅመውንና የማይጠቅመውን መለየት (3፥8-11)

*መደምደሚያ* (3፥12-15)

**ጸሐፊ፤** *ጳውሎስ*

**ዋና ሐሳብ፤** *ጤናማ አስተምህሮና መልካም ሥራ*

**የተጻፈት ጊዜ፣** *65/66 ዓ.ም. ሳይሆን አይቀርም*

***ታሪካዊ ዳራ፣***

እንደ አንደኛ ጢሞቴዎስና እንደ ሁለተኛ ጢሞቴዎስ መልእክት የቲቶ መልእክትም፡ ጳወሎስ ከወጣት ረዳቶቹ መካከል አንዱ ለሆነው ለቲቶ የላከው የግል መልእክት ነው። መልእክቱ "መልክታተ ምጋቤ" ይባላል፣ ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያንን ሥርዐትና አገልግሎት የሚመለከት ነውና። ከአሕዛብነት ወደ ክርስትና እምነት የመጣው ቲቶ (ገላ 2፥3)፣ በሐዋርያዊ አገልግሎት ወቅት የጳውሎስ የቅርብ ረዳት ሆነ። ቲቶ በሐዋርያት ሥራ ላይ በስም ባይጠቀስም እንኳ (ምናልባት የሉቃስ ወንድም በመሆኑ ሳይሆን አይቀርም)፣ ለሐዋርያው ጳውሎስ የቱን ያህል ቅርብ እንደ ሆነ በሚከተሉት ማስረጃዎች ተገልጾአል፡ (1) በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ስለ ቲቶ ዐሥራ ሦስት ጊዜ መጠቀሱ፣ (2) እንደ ጢሞቴዎስ በአገልግሎት ውስጥ በጳውሎስ አማካይነት ከዳኑት ሰዎችና ከጳውሎስ መንፈሳዊ ልጆች መካከል አንዱ በመሆኑና (1፥4) እምነት የሚጣልበት የሥራ አጋር በመሆኑ (2ቆሮ 8፥23)፣ (3) በጳውሎስ ሦስተኛ ሚሲዮናዊ ጕዞ ወቅት ቢደንስ ቢያንስ በቆሮንቶስ በተካሄደ በአንድ ዋና የተልእኮ ተግባር ላይ የጳውሎስ ተወካይ መሆኑ (2ቆሮ 2፥12-13፤ 7፥6-15፤ 8፥6፡16-24)፣ (4) በቀርጤስ የጳውሎስ የሥራ አጋር ሆኖ መሥራቱ (1፥5)።

ጳውሎስ በሮም መንግሥት ለመጀመሪያና ለሁለተኛ ጊዜ በታሰረበት መካከል፣ ጳውሎስና ቲቶ ለዐጭር ጊዜ በቀርጤስ ደሴት (በሜድትራንያን ባሕር በደቡብ ምዕራብ በትንሹ እስያ ውስጥ የምትገኝ) በአንድ ላይ ሆነው ሠሩ (የአንደኛ ጢሞቴዎስን መግቢያ ይመ)። ጳውሎስ ወደ መቄዶንያ በተጓዘበት ወቅት (ከ1ጢሞ 1፥3 ጋር ያነጻጽሩ)፥ ቲቶ ከቀርጤሳውያን ጋር መሥራቱን እንዲቀጥል ጳውሎስ ዐደራ ሰጠው (1፥5)። ዐደራውን ተቀብሎ ጥቂት ጊዜ ካለፈ በኋላ፣ ሁለቱ የጀመሩትን ሥራ ቲቶ ይፈጽም ዘንድ መመሪያ በመስጠት ጳውሎስ ይህን መልእክት ለእርሱ ጻፈለት። ምናልባት ጳውሎስ ይህን መልእክት በቀርጤስ በኩል ሲጓዙ በነበሩት በዜማስና በአጵሎስ እጅ ሳይልከው አልቀረም (3፥13)።

ጳውሎስ በዚህ መልእክት ላይ ቲቶን ይተኩት ዘንድ አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ለመላክ ያለውን ዕቅድ ይገልጻል፡ በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ጳውሎስ ክረምቱን ለማሳለፍ ባቀደው ቦታ ማለትም ኒቆጵልዮን በተባለ አውራጃ (በግሪክ ውስጥ) (3፥12)፣ ቲቶ ከሐዋርያው ጋር መገናኘት ነበረበት። ይህ የተከናወነ መሆኑን የምናውቀውም ከጊዜ በኋላ ጳውሎስ ቲቶን በድልማጥያ (የአሁኗ ዩጎዝላቪያ) እንደ ገና በመመደቡ ነው (2ጢሞ 4፥10)።

**ዐላማ**

ጳውሎስ ይህን መልእክት እንዲጽፍ ያደረገው የመጀመሪያ ዐላማ የጻፈው ቲቶ ላለበት የሥራ ኀላፊነት መመሪያ ለመስጠት ነው፤ መመሪያውም የሚከተሉትን ጉዳዮች ይመለከታል፡ ይኸውም (1) በቀርጤስ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ጳውሎስ ጀምሮት ሳያጠናቅቀው የቀረውን ተግባር ሥርዐት ማስያዝን ሲሆን፣ ይህም ሽማግሌዎችን መሾምን ያካትታል (1፥5)፤ (2) አብያተ ክርስቲያናት በእምነት፣ እውነትን በማወቅና በእውነተኛ መንፈሳዊነት እንዲያድጉ ማገዝን፡ (3) የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችን ዝም ማሰኘትን (1፥11)፤ እና (4) አርጢሞን ወይም ቲኪቆስ ቦታውን ከሸፈኑለት በኋላ (3፥12)፣ የቲቶን ወደ ጳውሎስ መምጣትን።

**ቅኝት**

ጳውሎስ አራት ዐበይት ጉዳዮችን በዚህ መልእክት ውስጥ ይገልጻል፡ (1) በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚመረጡት ሽማግሌዎች (ኤጲስ ቆጶሳት) ማሟላት ስላለባቸው የጠባይና የመንፈሳዊ ብቃት መለኪያ ለቲቶ መመሪያ ይሰጠዋል፡ ሽማግሌዎች ቤተ ሰባቸውን በብቃት በመምራት ረገድ (1፥5-9) የተመሰከረላቸው እውነተኛ መንፈሳዊ ሰዎች መሆን አለባቸው። (2) ጤናማ የሆነውን አስተምህሮ እንዲያስተምር፣ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎችንም እንዲገሥጽና ዝም እንዲያሰኝ ጳውሎስ ለቲቶ መመሪያ ይሰጠዋል (1፥10—2፥1)። በመልእክቱ ውስጥ ጳውሎስ ግልጽ በሆነና በተመጠነ ሁኔታ የተቀመጠውን የጤናማ አስተምህሮ ዕጥርጥርታ ያቀርባል (2፥11-14፤ 3፥4-7)። (3) ጳውሎስ ለቲቶ የሚከተሉትን ወገኖች ተገቢ ሚና ቍልጭ አድርጎ ያቀርባል (ከ1ጢሞ 5፥1—6፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ይኸውም የአረጋውያንን (2፥1-2)፣ የአሮጊቶችን (2፥3-4)፣ የወጣት ሴቶችን (2፥4-5)፣ የወጣት ወንዶችንና (2፥6-8) የባሪያዎችን (2፥9-10) ነው። (4) በመጨረሻም መልካም ሥራና የጽድቅ ሕይወት፣

ከእውነተኛ እምነት የሚፈለጉ
2፥7፡14፤ 3፥1፡8፡14 ይመ፤ ከ

**ልዩ ገጽታ**

የቲቶን መልእክት ልዩ የሚያደ
በክርስቶስ ኢየሱስ እውን የሚ
አይሽሬ ዕጥርጥርታዎችን አቅ
አገልግሎቷ ጠንካራ በሆነ መን
መመሥረት እንዳለባቸው አጽን
ብቃት መለኪያዎች ምን ምን
ከሚገኙት ሁለት ክፍሎች ውስ
ያነጻጽሩ)።

**ወደ ቲቶ የተላከውን**

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐ
መልእክት ከዚህ በታች ባለው
❏ 1—2 ❏ 3

ከእውነተኛ እምነት የሚፈለጉ ፍሬዎች መሆናቸውን ጳውሎስ በትኩረት ይገልጻል (1፥16፤ 2፥7፡14፤ 3፥1:8:14 ይመ፤ ከያዕ 2፥14-26 ጋር ያነጻጽሩ)።

### ልዩ ገጽታ

የቲቶን መልእክት ልዩ የሚያደርጉት ሦስት ዋና ዋና ገጽታዎች ናቸው፤ (1) በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ እውን የሚሆነልንን ድነት ትክክለኛ ባሕርይ አስመልክቶ ሁለት ዘመን አይሽሬ ዕጥርጥርታዎችን አቅፎ ይገኛል (2፥11-14፤ 3፥4-7)፤ (2) ቤተ ክርስቲያንና አገልግሎቷ ጠንካራ በሆነ መንፈሳዊ ሥነ መለኮታዊና ሥነ ምግባራዊ መሠረት ላይ መመሥረት እንዳለባቸው አጽንዖት ያደርጋል፤ (3) በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የመሪነት ብቃት መለኪያዎች ምን ምን እንደ ሆኑ በዝርዝር ከሚያሳዩት በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከሚገኙት ሁለት ክፍሎች ውስጥ አንዱን ይዞ ይገኛል (1፥5-9 ይመ፤ ከ1ጢሞ 3፥1-13 ጋር ያነጻጽሩ)።

### ወደ ቲቶ የተላከውን መልእክት ማንበብ

ሙሉውን የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአንድ ዓመት ማንበብ ከተፈለገ፣ ወደ ቲቶ የተላከው መልእክት ከዚህ በታች ባለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት በሁለት ቀን መነበብ ይኖርበታል፤
❑ 1—2 ❑ 3

*ማስታወሻ*

1 የእግዚአብሔርን ምርጦች እምነትና ወደ
እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚመራውን
የእውነት ዕውቀት ለማሳደግ የእግዚአብሔር
ባሪያና የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ
የሆነው ጳውሎስ፤ [2]እምነቱና ዕውቀቱ
የተመሠረቱትም የማይዋሸው አምላክ
ከዘመናት በፊት በገባው የዘላለም ሕይወት
ተስፋ ላይ ነው። [3]እርሱ በወሰነውም ጊዜ
በአዳኛችን በእግዚአብሔር ትእዛዝ ለእኔ በአደራ
በተሰጠ ስብከት በኩል ቃሉን ይፋ አደረገ።
[4]የጋራችን በሆነው እውነተኛ እምነት
ልጄ ለሆነው ለቲቶ፤
ከእግዚአብሔር አብ፣ ከአዳኛችንም
ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ሰላም ይሁን።

## ቲቶ በቀርጤስ የነበረው ኀላፊነት

[5]አንተን በቀርጤስ የተውሁህ ገና
ያልተስተካከለውን ነገር እንድታስተካክልና
ባዘዝሁህ መሠረት በየከተማው ሽማግሌዎችን
እንድትሾም ነው። [6]ሽማግሌ ነቀፋ የሌለበት፣
የአንዲት ሚስት ባል፣ ልጆቹም አማኞችና
በመዳራት ወይም ባለ መታዘዝ ስማቸው
የማይነሣ ይሁን። [7]ኤጲስቆጶስ የእግዚአብሔር
ሥራ ባለ አደራ እንደ መሆኑ የማይነቀፍ
ሊሆን ይገባል፤ ይኸውም ትምክሕተኛ፣ ግል
ፍተኛ፣ ሰካራም፣ ጨቅጫቃና ተገቢ ባልሆነ
መንገድ ለጥቅም የሚሮጥ ሊሆን አይገባም።
[8]ከዚህ ይልቅ እንግዳ ተቀባይ፣ በጎ የሆነውን
ነገር የሚወድ፣ ራሱን የሚገዛ፣ ቅን፣ ቅዱስና
ጠንቃቃ ሊሆን ይገባል። [9]ሌሎችን ትክክል
በሆነው ትምህርት እንዲያበረታታና ይህንኑ
ትምህርት የሚቃወሙትን ይወቅስ ዘንድ
እንደ ተማረው በታመነ ቃል የሚጸና መሆን
አለበት።
[10]ዐመፀኞች፣ ለፍላፊዎችና አታላዮች
የሆኑ ብዙ ሰዎች አሉና፤ በተለይም እነዚህ
ከተገረዙት ወገን ናቸው። [11]እነዚህን
ዝም ማሰኘት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም
ትክክል ባልሆነ መንገድ ጥቅም ለማግኘት
ሲሉ ማስተማር የማይገባቸውን ነገር
በማስተማር ቤት ሰብን ሁሉ በመበከል
ላይ ናቸውና። [12]ከራሳቸው ነቢያት አንዱ
ስለ እነርሱ ሲናገር፣ "የቀርጤስ ሰዎች
ዘወትር ውሸታሞች፣ ክፉ አውሬዎችና

1፥1 ሮሜ1፥1፤ 1ቆሮ1፥1፤ 1ጢሞ2፥2፡4፤ ያዕ1፥1
1፥2 ዘኍ23፥19፤ 2ጢሞ1፥1፡9፤ ቲቶ3፥7፤ ዕብ6፥18
1፥3 ሉቃ1፥47፤ 2ቆሮ1፥1፤ 1ሞ1፥11፤ 2፥6፤ 6፥15፤ 2ጢሞ1፥10
1፥4 ሮሜ1፥7፤ 2ቆሮ2፥13፤ 1ጢሞ1፥2
1፥5 ሐዋ11፥30፤ 27፥7
1፥6 1ተሰ3፥13፤ 1ጢሞ3፥2
1፥7 1ቆሮ4፥1፤ 1ጢሞ3፥1፡3፡8
1፥8 ሮሜ12፥13፤ 2ጢሞ3፥3፤ ቲቶ2፥2፡5፡6፡12
1፥9 1ቆሮ16፥13፤ 1ጢሞ1፥10፡19፤ 2ጢሞ1፥13፤ 3፥14
1፥10 ሐዋ10፥45፤ 11፥2፤ 1ጢሞ1፥6
1፥11 1ጢሞ5፥13 1፥12 ሐዋ2፥11፤ 17፥28

**1፥1 ወደ እውነተኛ መንፈሳዊነት የሚመራውን የእውነት ዕውቀት፤** እውነተኛውን ወንጌል ሲሰብኩ የሚሉ ሁሉ፥ መልእክታቸው በተቀባይ ወገኖች ዘንድ፣ "የቱን ያህል እውነተኛ መንፈሳዊነትን አስገኝቷል?" በሚለው ይመዘን ዘንድ መዘጋጀት አለባቸው። ያ መልእክት ተከታዮቹን ወደ እውነተኛ መንፈሳዊነት ካልመራ (ቍ. 16 እና ማብ፤ 1ጢሞ 6፥3፡ ዕብ 1፥9፤ 1ቆሮ 13፥1 እና ማብ ይመ)፥ መልእክቱ ወይም አስተምህሮው ከሐዋርያት፣ "ጤናማ አስተምህሮ" ወይም "ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጤናማ ትምህርት (1ጢሞ 6፥3) ጋር ይስማማል ብሎ የመናገር መብት ሊኖረው የሚችል አንድም ቤተ ክርስቲያን ወይም ቤተ እምነት አይኖርም (ቍ. 9፡ 2ጢሞ 1፥11-14፤ 2፥2፡ 3፥10-12)።

**1፥2 የማይዋሸው አምላክ፤** ዕብ 6፥18 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**1፥5 ባዘዝሁህ መሠረት … ሽማግሌዎችን እንድትሾም፤** የመጋቢነት አገልግሎቶች ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን መልእክት ማለትም በሐዋርያት የተገለጸውን መነሻ አድርገው፥ ይህንኑ የክርስቶስ መልእክት መለስ ብለው መቃኘትና ማየትና በዚሁ ላይ መመሥረት አለባቸው፥ ይህም በቍ 5-9 እና በ1ጢሞ 3፥1-7 ላይ እንደ ተገለጸው፣ በሐዋርያዊ እውነት ላይ በመመሥረት ሥር መያዝ ማለት ነው። እንዲህ ያለው አገልግሎት ዋጋ የሚኖረው በአዲስ ኪዳን ትምህርት፣ አገልግሎትና በተጻፈው ቃል መሠረት የታመነውን ቃል በጽናት ሲይዝ ነው (ቍ. 9፤ ሐዋ 14፥23፤ ኤፌ 2፥20 እና ማብ ይመ)።

**1፥6 ነቀፋ የሌለበት፣ የአንዲት ሚስት ባል፤** በገጽ 1925 ላይ፣ *"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥7 ኤጲስ ቆጶስ፤** "ሽማግሌ" (በግሪክ፣ ፕሬስቡተሮስ ቍ 6) እና "ኤጲስ ቆጶስ" (በግሪክ "ኤጲስ ቆጶስ" ቍ 7 የሚለው ቃል) ተወራራሾች ናቸው፤ የሚያመለክቱትም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድን ዐይነት የኀላፊነት ቢሮ ነው፤ የመጀመሪያው የሚያመለክተው ለኀላፊነቱ የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ብቃትና ክብር ነው፤ ሁለተኛው ወይም ቀጥሎ ያለው የሚያመለክተው ደግሞ አንድ አማኝ የእግዚአብሔር ቤት መጋቢ በመሆን የሚወጣውን የኀላፊነት ተግባር ነው።

**1፥7 የማይነቀፍ ሊሆን ይገባል፤** እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚያገለግሉት ኤጲስ ቆጶሳት ከፍተኛውን ግብረ ገባዊ ብቃት ይፈልጋል፥ መሪዎች ነቀፋ የማይገኝባቸው ካልሆኑ በቀር፣ በአርአያነት መታየት ከሚገባው እውነተኛ መንፈሳዊነት ጉድለት የተነሣ፣ ቤተ ክርስቲያን ከጽድቅ ትለያለች። ይህን ጉዳይ በይበልጥ ለመረዳት በገጽ 1925 ላይ፣ *"የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**1፥9 በታመነ ቃል የሚጸና መሆን አለበት፤** ሽማግሌዎች በቍ 6-8 ላይ የተመለከቱትን ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ ብቃት ማሟላት ብቻ ሳይሆን፥ ስለ ጌታ ኢየሱስ የማዳን ሥራ የተሰጠውን የመጀመሪያ ሐዋርያዊ ምስክርነት በጽናት መያዝ፣ በብርቱ ማፍቀር፣ ማወቅ፥ ሕይወታቸውንም ስለዚሁ አሳልፈው መስጠት አለባቸው። ይህ ዐይነቱ ዐልፎ መስጠት በሁለት ምክንያቶች እጅግ አስፈላጊ ነው፤ (1) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ልብና አእምሮ ለክርስቶስ፣ ለእውነትና ለጽድቅ ፈጽሞ ወደ መስጠት ለመምራት (ከ2ጢሞ 4፥2 ጋር ያነጻጽሩ)፣ ከእግዚአብሔር ቃል ለማስተማር፣ ለማበረታታትና ለመምከር ብቁ መሆን አለባቸው፥ (2) ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚቃረነውን ትምህርት የሚያስተምሩትን ወደ እውነት ለመምራትና (2ጢሞ 2፥24-26)፣ ትክክለኛውን ሬር ለማስያዝ ብቁ ሊሆኑ ይገባል፥ የሐሰት ትምህርቱን የተቀበሉት መታረምን የማይቀበሉ ከሆነም ስለዚሁ የስሕተት ትምህርት ሌሎችን አማኞች ማስገንዘብና እውነቱን ማሳመን አለባቸው (በገጽ 1866 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን የአገልግሎት ስጦታዎች"* በሚል ርእስና በገጽ 1716 ላይ፣ *"የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ተግባራዊ ኀላፊነታቸው"* በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ)።

ሰነፍ ሆዳሞች ናቸው" ብሎአል። [13]ይህ ምስክርነት እውነት ነው፤ ስለዚህ አጥብቀህ ገሥጻቸው፤ ይኸውም ትክክለኛ እምነት እንዲኖራቸውና [14]የአይሁድን ተረት ወይም ከእውነት የራቁትን ሰዎች ትእዛዝ እንዳያዳምጡ ነው። [15]ለንጹሓን ሁሉም ነገር ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም ነገር የለም፤ እንዲያውም አእምሮአቸውና ኅሊናቸው የረከሰ ነው። [16]እግዚአብሔርን እናውቃለን ይላሉ፤ ዳሩ ግን በተግባራቸው ይክዱታል፤ አስጸያፊዎች፣ የማይታዘዙና ለበጎ ሥራ የማይበቁ ናቸው።

2 አንተ ግን ከትክክለኛው ትምህርት ጋር ተስማሚ የሆነውን አስተምር። [2]አረጋውያን ጭምቶች፣ የተከበሩ፣ ራሳቸውን የሚገዙና በእምነት፣ በፍቅርና በትዕግሥት ጤናማነት ያላቸው እንዲሆኑ ምከራቸው።

[3]እንዲሁም አሮጊቶች በአኗኗራቸው የተከበሩ እንዲሆኑ፣ በጎ የሆነውን የሚያስተምሩ እንጂ የሰው ስም የሚያጠፉ ወይም በወይን ጠጅ ሱስ የተጠመዱ እንዳይሆኑ አስተምራቸው፤ [4]እንዲህ ከሆኑ፣ ወጣት ሴቶች ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲወዱ ማስተማር ይችላሉ፤ [5]የእግዚአብሔር

1፥13 1ጢሞ5፥20፤ ቲቶ2፥2
1፥14 ቈላ2፥22፤ 1ጢሞ1፥4፤ 2ጢሞ4፥4
1፥15 መዝ18፥26፤ ማቴ15፥10፡11፤ ማር14-19፤ ሐሥ10፥9-16፡28፤ ሮሜ14፥14፡23፤ ቈላ2፥20-22፤ 1ጢሞ6፥5
1፥16 ኤር5፥2፤ 12፥2፤ ሆሴ8፥2፡3፤ 1ዮሐ2፥4
2፥1 1ጢሞ1፥10
2፥2 ቍ5፡6፡12፤
2፥2 1ጢሞ3፥2፤ 5፥1፤ ቲቶ1፥1፡8፡13 2፥3 1ጢሞ3፥8፡11
2፥4 1ጢሞ5፥2 2፥5 ቍ2፡6፡12፤ ኤፌ5፥22፤ 1ጢሞ5፥14፤ 6፥1፤ ቲቶ1፥8፤ ዕብ4፥12

**1፥15 ሁሉም ነገር ንጹሕ ነው፤** ምናልባት ጳውሎስ ከዚህ ላይ ስለ አይሁድ የምግብ ደንብ ሥርዐታዊ ንጽሕና ሳይናገር አልቀረም (ከማቴ 15፥10-11፤ ከማር 7፥15፤ ከ1ጢሞ 4፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ)። አንዳንድ መምህራን ሥርዐቱን በጥብቅ መከተል ለእውነተኛ ጽድቅ አስፈላጊ ነው በማለት ንጹሕና ንጹሕ ባልሆነ ምግብ መካከል ባለው ልዩነት ላይ ይጨነቁ ነበር። እውነተኛ ግብረ ገባዊ ባሕርይን፣ የውስጥ ንጽሕናንና በውጭም መታየት የሚገባውን ጽድቅ ችላ አሉ (ቍ 16)። የአንድ ሰው ግብረገባዊ ሁኔታ ንጹሕ ከሆነ፣ ንጹሕ በሆነና ንጽሕና በጐደለው ምግብ መካከል የሚኖረው ልዩነት ለጳውሎስ ለእርሱ ግብረገባዊ ትርጕም አያመጣም። ከዚህ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው በግብረገብ ረገድ ትክክል ስላልሆነ ነገር ወይም ተግባር ሳይሆን፣ ሥርዐታዊ ስለ ሆነው ንጽሕና ነው።

**1፥16 እናውቃለን ይላሉ፤ ... ይክዱታል፤** በእግዚአብሔር ዐይን ፊት አስጸያፊ ከሆኑት ነገሮች አንዱ፣ ለእርሱና ለቃሉ ዐመፀኛ ተሁኖ እየተኖረ ሳለ፣ "ክርስቶስን እከተላለሁ፤ የዘላለምም ሕይወት አለኝ" (ቍ 2) እያሉ ተደላድሎ መኖር ነው (ከሉቃ 6፥46፤ ዮሐ 14፥12፤ 15፥10-14፤ ከ1ዮሐ 2፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥2 አረጋውያን ጭምቶች፤** የዚህ ጥቅስ ሙሉ ሐሳብ አረጋውያን የሚያሰክር የወይን ጠጅ ሳይጠጡ፣ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ሕያው መሥዋዕት አድርገው በማቅረብ ለአማኞች ሁሉ ምሳሌ እንዲሆኑ ነው (ይህ ጥቅስ ፓስተሮችንና ሴቶችን የሚመለከት ስለ መሆኑ 1ጢሞ 3፥2፡11 ይመ)። ይህም ቀጥሎ ባሉት ጭብጦች የተደገፈ ነው፦

(1) "ጭምቶች" (ግክ ኔፋሊዮስ) በአዲስ ኪዳን የግሪክ መዝገበ ቃላት ውስጥ "ከወይን ጠጅ መታቀብ" የሚል ቀዳሚ ትርጕም ተሰጥቶታል። የሚከተሉትን ተመሳሳይ ትርጕሞች ለአጽንዖት ያህል ልብ ማለት ተገቢ ነው፤ "ቃሉ በመጀመሪያ ደረጃ የሚያመለክተው ከአልኮል መራቅን ነው" (ሬይንከርና ሮጀርስ)፤ "የወይን ጠጅ የማይጠጣ ሰው" (የባይዛንቲስ ግሪክ ዲክሽነሪ፤ አቴንስ፤ 1839)፤ "የወይን ጠጅ አልባ፣ የወይን ጠጅ የሌለው" (ሊደልና ስኮት)፤ "ከማንኛውም ዐይነት የወይን ጠጅ ጋር ንክኪ የሌለው" (ሞልቶን-ሚሊጋን)፤ "የወይን ጠጅ ያልያዘ" (ኪተልና ፍሬደሪክ)፤ "ከወይን ጠጅ ጋር ያልተደባለቀ" (አቦትና ስሚዝ)፣ ቃል በቃል ሲተረጐምም፣ "ከወይን ጠጅ የመራቅ ሁኔታ" ማለት ነው (ብራውን፣ ዲክሽነሪ ኦፍ ኒው ቴስታመንት፤ ቮል፡1)። ብራውን በማከል፣ "ኔፋሊዮስ የሚገኘው በመልእክታተ ምጋቢ ብቻ ነው፤ የሚያመለክተውም ከጳጳሳት (1ጢሞ 3፥2)፣ ከሴቶች (1ጢሞ 3፥11)፣ እና ከአረጋውያን (ቲቶ 2፥2) አኗኗር ላይ ጐድሎ የሚገኘውን የሕይወት ዘይቤ ነው።" አር ለየርድ ሃሪስም በበኩሉ፣ "በዘመን አይሽሬ ደራሲያን ዘንድ ተዘውትሮ የሚጠጣ ሲሆን ከማንኛውም ዐይነት የሚያሰክር የወይን ጠጅ ነጻ ነው" (ዘ ባይብል ቱዴይ፤ ገጽ 139) በማለት ይገልጻል።

(2) ጳውሎስና ጴጥሮስ በነበሩበት ዘመን የነበሩት የአይሁድ ጸሓፊዎች፤ በቀዳሚ ደረጃ የሚገኘውን ትርጕም ያጸናሉ። ዮሴፈስ ስለ አይሁድ ካህናት ሲገልጽ፣ "የክህነት ልብሳቸውን ለብሰው ሳሉ የወይን ጠጅ እንዳይጠጡ የተከለከሉ፣ በማንኛውም ረገድ ንጹሕ የሆኑና ከመጠጥ የራቁ ሰዎች ነበሩ" (አንቲኩይቲስ 3፡12፡2) ይላል። ፋይሎ ደግሞ፣ "ዳግም ልደትን ያገኘች ነፍስ፣ "በሕይወት ዘመኗ ሁሉ ዘወትር ከመጠጥ የራቀች ናት" ይላል (ድራንክድነስ፤ 37)።

(3) ከዚህ ቀደም ከተጠቀሰው አንጻር ይህ ጕዳይ ሲታይ፣ ጳውሎስ ይህን ቃል የሐሳብ መግለጫ በማድረግ የተጠቀመው በቀዳሚ ደረጃ የሚገኘውን ትርጕም ሳይገነዘብ ነው ብሎ አሳማኝ የሆነ ሐሳብ ማቅረብ ያስቸግራል (ከ1ተሰ 5፥6 እና ማብ ጋር ያነጻጽሩ)።

**2፥3 በወይን ጠጅ ሱስ የተጠመዱ እንዳይሆኑ፤** 1ጢሞ 3፥8 እና ማብራሪያውን ይመልከቱ።

**2፥4-5 ሴቶች ባሎቻቸውንና ልጆቻቸውን እንዲወዱ፤** ቤተ ሰብን፣ ቤትንና እናትነትን አስመልክቶ እግዚአብሔር ልዩ የሆነ ሀሳብ ለሴት ዐቅዶአል፤ (1) ለአንዲት ሚስትና እናት የእግዚአብሔር ፍላጎት ሙሉ ሐሳቧና ልቧ በቤቱ ሰቢ ላይ እንዲሆን ነው፤ የአንዲት ክርስቲያን እናት ዓለም ቤቷ፣ ባለቤቷና ልጆቿ መሆን አለባቸው፤ የእግዚአብሔርን ቃል ታከብር ዘንድ ከእግዚአብሔር የተወሰነላት መንገድ ይኸው ነው (ከዘዳ 6፥7፤ ከምሳ 31፥27፤ ከ1ጢሞ 5፥14 ጋር ያነጻጽሩ)።

(2) ከቤተ ሰብ ጋር በተያያዘ መልኩ አንዲት ሴት ከእግዚብሔር የተሰጧት ተግባሮች የሚከተሉትንም ያካትታሉ፤ (ሀ) ጌታን በማገልገል ረገድ (መዝ 127፥3፤ ማቴ 18፥5፤ ሉቃ 9፥48)፣ እግዚአብሔር በዐደራ የሰጣትን ልጆች መንከባከብን (ቍ 4፤ 1ጢሞ 5፥14)፤ (ለ) ለባሏ ረዳትና ታማኝ የኑሮ ጓደኛ መሆንን (ቍ 4-5፤ ዘፍ 2፥18 እና ማብ ይመ)፤ (ሐ) የተባረከ ጠባይ፣ መተዳደሪያ የሚሆን ተግባራዊ የሆነ ሙያም ልጆች ይኖራቸው ዘንድ አባት ልጆቹን በሚያሠለጥንበት ጊዜ የእርሱ አጋዥ መሆንን (ዘዳ 6፥7፤ ምሳ 1፥8-9፤ ቈላ 3፥20፤ 1ጢሞ 5፥10 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1894 ላይ፣ "*ወላጆችና ልጆች*" በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፤ (መ) እንግዳን በአግባቡ ማስተናገድን (ኢሳ 58፥6-8፤ ሉቃ 14፥12-14፤ 1ጢሞ 5፥10)፤ (ሠ) የቤቷን ፍላጎት

ቃል በማንም ዘንድ እንዳይሰደብ ራሳቸውን
የሚገዙና ንጹሓን፣ በቤት ውስጥ በሥራ
የተጠመዱ፣ ቸሮች፣ ለባሎቻቸው የሚገዙ
እንዲሆኑ ያስተምሯቸው።
⁶እንዲሁም ወጣት ወንዶች ራሳቸውን
እንዲገዙ ምከራቸው። ⁷በማንኛውም
ነገር መልካም የሆነውን ነገር በማድረግ
ራስህን አርአያ አድርገህ አቅርብላቸው።
በምታስተምራቸውም ትምህርት
ታማኝነትን፣ ቁም ነገረኛነትን፣
⁸የማይነቀፍ ጤናማ አነጋገር አሳይ፤
ይኸውም ተቃዋሚ ስለ እኛ የሚናገረውን
መጥፎ ነገር በማጣት እንዲያፍር ነው።
⁹ባሮች ለጌቶቻቸው በማንኛውም ነገር
እንዲገዙ፣ ደስ እንዲያሰኟቸው፣ የአጸፋ
ቃል እንዳይመልሱላቸው አስተምር፤
¹⁰አይስረቁ፤ ይኸውም በሁሉም መንገድ
የአዳኛችን የእግዚአብሔር ትምህርት
ይወደድ ዘንድ ፍጹም ታማኝ መሆናቸውን
እንዲያስመሰ ክሩ ነው።
¹¹ድነት የሚገኝበት የእግዚአብሔር ጸጋ
ለሰዎች ሁሉ ተገልጦአልና፤ ¹²ይህም ጸጋ
በኃጢአት መኖርንና ዓለማዊ ምኞትን
ዕብ 11፥13-16 ክደን፣ በአሁኑ ዘመን ራሳችንን በመግዛት
በጽድቅ፣ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት
እንድንኖር ያስተምረናል፤ ¹³ይህም የተባረከ
ተስፋችን የሆነውን የታላቁን የአምላካችንንና
የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ዕብ 9፥28
መገለጥ በመጠባበቅ ነው፤ ¹⁴እርሱም ከክፋት
ሊቤዠን መልካም የሆነውን ለማድረግ
የሚተጋውን የእርሱ የሆነውን ሕዝብ ለራሱ
ያነጻ ዘንድ ራሱን ስለ እኛ ሰጥቶአል።
¹⁵እንግዲህ ልታስተምር የሚገባህ
እነዚህን ነው፤ በሙሉ ሥልጣን ምከር፤
ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።

## በጎ የሆነውን ማድረግ

3 ሰዎች ለገዦችና ለባለ ሥልጣናት
እን ዲገዙ፣ እንዲታዘዙና መልካም
የሆነውን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ እንዲሆኑ
አሳስ ባቸው። ²እንዲሁም በማንም ላይ
ክፉ እንዳይናገሩ፣ ሰላማውያን እንዲሆኑ፣
ለሰዎችም ሁሉ ከልብ የመነጨ ትሕትና
እንዲያሳዩ አስገንዝባቸው።
³ቀድሞ ሲል እኛ ራሳችን ማስተዋል
የጐደለን፣ የማንታዘዝ፣ የተታለልን፣
ለተለያየ ምኞትና ምኞት ባሪያ ሆነን
የተገዛን ነበርን፤ እየተጣላንና እርስ በርስ
እየተጠላላን በክፋትና በምቀኝነት እንኖር
ነበር። ⁴ዳሩ ግን የአዳኛችን የእግዚአብሔር
ቸርነትና ፍቅር በተገለጠ ጊዜ፣ ⁵ስላደረግነው

2፥6 ቀ 2፡5፡12፤ 1ጢሞ 5፥1፤ ቲቶ 1፥8
2፥7 ቀ 14፤ 1ጢሞ 4፥12
2፥8 1ጴጥ 2፥12
2፥9 ኤፌ 6፥5
2፥10 ማቴ 5፥16፤ ሉቃ 1፥47
2፥11 ሮሜ 3፥24፤ 1ጢሞ 2፥4፤ 2ጢሞ 1፥10
2፥12 ቀ 2፡5፡6፤ 2ጢሞ 3፥12፤ ቲቶ 1፥8፤ 3፥3
2፥13 1ቆሮ 1፥7፤ 1ጢሞ 6፥14፤ 2ጴጥ 1፥1
2፥14 ቀ 7፤ ዘፀ 19፥5፤ ዘዳ 4፥20፤ 14፥2፤ መዝ 135፥4፤ ምሳ 16፥7፤ ሚል 3፥17፤ ማቴ 1፥21፤ 5፥16፤ 20፥28፤ 2ቆሮ 8፥21፤ ኤፌ 2፥10፤ ቲቶ 3፥1፤ 8፡14፤ ዕብ 1፥3፤ 1ጴጥ 2፥9፡12፡15፤ 3፥13፤ 1ዮሐ 1፥7
3፥1 ሮሜ 13፥1፤ 2ጢሞ 2፥21፤
3፥1 ቲቶ 2፥14፤ 1ጴጥ 2፥13፡14 3፥2 ኤፌ 4፥31
3፥3 ኤፌ 2፥2 3፥4 ሉቃ 1፥47፤ ኤፌ 2፥7፤ ቲቶ 2፥11
3፥5 ሐሥ 22፥16፤ ሮሜ 11፥14፤ 12፥2፤ ኤፌ 2፥9፤ 1ጴጥ 1፥3

ለማሟላት የሙያ ችሎታዋን መጠቀሟን (ምሳ 31፥13፡15-16፡18-19፡22፡24)፤ (ሬ) አረጋውያን የሆኑትን ወላጆች በቤቷ መንከባከብን (1ጢሞ 5፥8፤ ያዕ 1፥27)።

(3) ለሕይወታቸውና ለቤተሰባቸው እግዚአብሔር ያቀደላቸውን ዕቅድ ለመፈጸም ፈልገው ሳለ፣ ግን ከገንዘብ ዕጦት የተነሣ ከልጆቻቸው ርቀው ሥራ ለመሥራት የሚገደዱ እናቶች፣ ጌታ የሰጣቸውን ኀላፊነትና ተግባር ከልጆቻቸው ጋር በመሆን ይፈጽሙ ዘንድ በሚጸልዩበት ጊዜ፣ ያሉበትን ሁኔታ ለጌታ አሳልፈው መስጠት ይኖርባቸዋል (ምሳ 3፥5-6፤ 1ጢሞ 5፥3 ይመ፤ እንዲሁም ኤፌ 5፥21-23 እና ማብ ይመ)።

**2፥7 አርአያ አድርገህ አቅርብላቸው፤** በገጽ 1925 ላይ፣ “***የመሪዎች መንፈሳዊ ብቃት***” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመልከቱ።

**2፥11 የእግዚአብሔር ጸጋ፤** ከቍ 11-14 ድረስ ያለው ክፍል የእግዚአብሔርን የማዳን ጸጋ ባሕርይና ዐላማ ይገልጻል፤ ጳውሎስ በጻፈው መሠረት ድነት የሚገኝበት ጸጋ፣ (1) ርኩስ የሆነውን የዘመኑን ፍትወት፣ ደስታና ሐሴት ፈጽሞ በመጥላት አስጸያፊ አድርገው እንዲቈጥሩት አማኞችን ይመክራቸዋል (ቍ 12 ይመ፤ ከሮሜ 1፥18-32፤ ከ2ጢሞ 2፥22፤ ከ1ዮሐ 2፥15-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) እንዲሁም የተከበረውን ተስፋና የጌታ ኢየሱስን ዳግም ምጽአት በናፍቆት እየተጠባበቅን ሳለን (ቍ 13፤ ገላ 5፥5፤ ፊል 1፥5፤ 2ጢሞ 4፥8 ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1746 ላይ፣ “***እምነትና ጸጋ***” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)፣ “ራሳችንን በመግዛትና በጽድቅ … እንድንኖር” (ቍ 12) እኛን አማኞችን ያስተምረናል፤ በኀይልም ያስታጥቀናል።

**2፥13 የተባረከ ተስፋችን፤** ማንኛውም ክርስቲያን መናፈቅ ያለበት፣ “የተባረከ ተስፋችን” የተባለውን፣ “የታላቁን የአምላካችንንና የአዳኛችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር” መገለጥና ለዘላለም ከእርሱ ጋር መሆናችንን ነው (ዮሐ 14፥3 እና ማብ ይመ፤ እንዲሁም በገጽ 1907 ላይ፣ “***ንጥቀት***” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኵረት ጽሑፍ ይመ)። ይህ ተስፋ በማንኛውም ሰዓት እውን ሊሆን ይችላል (ከማቴ 24፥42፤ ከሉቃ 12፥36-40፤ ከያዕ 5፥7-9 ጋር ያነጻጽሩ)። ስለዚህ ክርስቲያኖች ዛሬ መለከት ሊነፋ ይችላል፤ ጌታም ዳግም ሊመጣ ይችላል የሚለውን በጸሎት መንፈስ የሚጠብቀውን ተስፋ ክፉ ችላ ማለት የለባቸውም።

**2፥14 ራሱን ስለ እኛ ሰጥቶአል፤** ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ደሙን ያፈሰሰው (1ጴጥ 1፥18-19)፣ (1) እኛን ከማንኛውም ክፋት እንዲሁም የእግዚአብሔርን ሕግና ጻድቅ መንገዱን ከመተላለፍ ሊቤዠን ነው (ከ1ዮሐ 3፥4 ጋር ያነጻጽሩ)፤ (2) ከኃጢአትና ከዓለም ተለይተን ቅዱስ ሕዝብና የእግዚአብሔር ልዩ ርስት እንድንሆን ነው። ከኃጢአትና ከሰይጣን ኀይል ጋር በመታገል ላይ የሚገኙት፣ ክርስቶስ ሊቤዣቸው ከሞተላቸው፥ በኃጢአትና በክፋት ኀይል ላይ ድል አድራጊዎች ሆነው እንዲኖሩ፣ አሸናፊውን ጸጋንማ የቱን ያህል ሊሰጣቸው እንደሚችል ማወቅ አለባቸው (ሮሜ 5፥9-11)።

**3፥1 ለገዦችና … እንዲገዙ፤** በመካሄድ ላይ ያለው ምስክርነት እንዲቀጥልና ወንጌል በሰፊው እንዲሰበክ አማኞች ለመንግሥትና ለባለሥልጣናቱ መገዛት፣ ለመንግሥት ሕግ መታዘዝ፣ እንዲሁም መልካም ዜጎችና የተከበሩ ጎረቤቶች መሆን ይገባቸዋል (ከማቴ 17፥24-27፤ 22፥15-23፤ ከሮሜ 13፥1-7፤ ከ1ጴጥ 2፥13-17 ጋር ያነጻጽሩ)፤ ከላይ የተጠቀሰው ክፍ የሚይቻል የሚሆነውም የመንግሥት ሕግ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር ሲጋጭ ብቻ ነው (ከሐሥ 5፥29 ጋር ያነጻጽሩ)።

**3፥5 ዳግም ልደት በሆነው መታጠብና፤** በክርስቲያናዊ ጥምቀት በትእምርት መልክ ሥዕላዊ

የጽድቅ ሥራ ሳይሆን፣ ከምሕረቱ የተነሣ
አዳነን። ያዳነንም ዳግም ልደት በሆነው
መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ መታደስ ነው፤
6ይህንም መንፈስ እግዚአብሔር በአዳኛችን
በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእኛ ላይ
አትረፍርፎ አፈሰሰው፤ 7ይኸውም በጸጋው
ጸድቀን የዘላለምን ሕይወት ተስፋ ይዘን
ወራሾች እንድንሆን ነው። 8ይህም የታመነ
ቃል ነው። በእግዚአብሔር የሚያምኑ መልካሙን
ነገር ለማድረግ ራሳቸውን እሳ ልፈው
ይሰጡ ዘንድ እነዚህን ነገሮች አስረግጠህ
እንድትናገር እፈልጋለሁ። ይህ መልካምና
ለማንኛውም ሰው የሚጠቅም ነው።
9ነገር ግን ከንቱ ከሆነ ክርክርና
ከትውልድ ሐረግ ቆጠራ ከጭቅጭቅና
ስለ ሕግ ከሚነሣ ጠብ ራቅ፤ ይህ ዋጋ ቢስና
ከንቱ ነውና። 10መከፋፈል የሚያመጣን
ሰው አንድ ጊዜ ምከረው፤ ለሁለተኛ ጊዜ
አስጠንቅቀው፤ ከዚያ ካለፈ ከእርሱ ጋር
አንዳች ነገር አይኑርህ። 11እንዲህ ዐይነቱ
ሰው የሳተና ኀጢአተኛ ነው፤ ራሱንም

3፥6 ሮሜ5፥5
3፥7 ማቴ25፥46፤ ሮሜ3፥24፤ 8፥17፡ 24፤ ቲቶ1፥2
3፥8 1ጢሞ1፥15፤ ቲቶ2፥14
3፥9 2ጢሞ2፥14፤ 16፤ ቲቶ1፥10-16
3፥10 ሮሜ16፥17
3፥12 ሐሥ20፥4፤ 2ጢሞ4፥9፡21
3፥13 ሐሥ18፥24
3፥14 ቲቶ2፥14
3፥15 ቆላ4፥18፤ 1ጢሞ1፥2

እንደሚኰንን ዕወቅ።

### የመጨረሻ ምክር

12አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን
ወደ አንተ እንደ ላክሁ እኔ ወዳለሁበት
ወደ ኒቆጵልዮን ለመምጣት የተቻለህን
ሁሉ አድርግ፤ ክረምቱን በዚያ ላሳልፍ
ወስኛለሁ። 13ሕግ ዐዋቂውን ዜማስንና
አጵሎስን በጒዞአቸው ለመርዳት የተቻለህን
ሁሉ አድርግ፤ የሚያስፈልጋቸውንም
ሁሉ አሟላላቸው። 14ከእኛ ወገን ለሆኑት
ለዕለት የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገኙና
ኑሮአቸውም ፍሬ የሌለው እንዳይሆን
ለመልካም ሥራ መትጋትን ይማሩ ዘንድ
ይገባቸዋል።
15ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል። ከእምነት የተነሣ
ለሚወዱን ሰላምታ አቅርቡልን።
ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።

---

በሆነ መንገድ የተገለጠው ጒዳይ የሚያመለክተው፣ የአማኞችን አዲስ ልደት ነው (በገጽ 1606 ላይ፣ “ዳግም ልደት” በሚል ርእስ የቀረበውን የትኩረት ጽሑፍ ይመ):: “በመንፈስ ቅዱስ መታደስ” የሚለው ሐሳብ የሚያመለክተው ደግሞ አማኞች ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር አሳልፈው በሰጡ ቍጥር፣ ዘወትር ከላይ የሚመጣላቸውን መለኮታዊ ሕይወት ነው (ከሮሜ 12፥2 ጋር ያነጻጽሩ)::

**3፥6 በእኛ ላይ አትረፍርፎ አፈሰሰው፤** ጳውሎስ ስለ መንፈስ ቅዱስ ሥራ የጠቀሰው በጰንጠቆስጤ ቀንና ከዚያም በኋላ እውን የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ መውረድ ወደ ኋላ መለስ ብሎ የሚያመለክት ነው (ከሐሥ 2፥33፤ 11፥15 ጋር ያነጻጽሩ):: እግዚአብሔር ከአዲስ ልደትና መንፈስ ቅዱስ በእኛ ሕይወት ላይ ከፈጸመው ሥራ የተነሣ ጸጋውንና ኀይሉን አትረፍርፎ ይሰጣል::

**3፥10 መከፋፈል የሚያመጣን ሰው … ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር አይኑርህ፤** ከዚህ ላይ የሚከፋፍሉ ሰዎች የተባሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የሌላቸውን ሐሳቦችና አስተምህሮዎች የሚያስተምሩ የሐሰት ትምህርት አስተማሪዎች ናቸው:: ሁለት ጊዜ ሙሉ ምክር ተሰጥቶአቸው የማይሰሙ ሆነው ከተገኙ እንዲገለሉ፣ ማለትም ከቤተ ክርስቲያን እንዲወገዱ ያስፈልጋል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነትን ትተው የራሳቸውን ሐሳብና አመለካከት የሚተኩ ሁሉ ስሑታንና ኀጥኣን ናቸው (ቍ 11)::

**3፥14 ለመልካም ሥራ መትጋትን፤** “ለመልካም ሥራ መትጋትን” ሲባል አንድ አማኝ አዲስ ሰው የመሆኑና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት የማግኘቱ ውጤት እንደ ሆነ ጳውሎስ በአጽንዖት ያስገነዝባል (ቍ 4-8):: አማኞች፣ “መልካም የሆነውን በማድረግ” ራሳቸውን “አርአያ” አድርገው ማቅረብ አለባቸው (2፥7)፤ “መልካም የሆነውን ለማድረግም” ትጉዎች (2፥14)፣ “መልካም የሆነውን ለማድረግ ዝግጁ” (ቍ 1) እንዲሁም፣ “መልካሙን ነገር ለማድረግ ራሳቸውን አሳልፈው” የሰጡ መሆን አለባቸው (ቍ 8)::